# ነገረ-ኢትዮጵያ

ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እንናገራለን!

ቅፅ 1 ቁጥር 4 | አርብ መጋቢት 5 2006 ዓ.ም. | ዋጋ 8.00 ብር



አምጽ . . . ሐገርህን አስመልስ! 3

በፖለቲካውም ማለባበስ ይቁም 12

እድገት፣ ልማት፣ ጥራት... 11


## የፖሊሱ <<መንግስት>> 5





4

## <<እኛን ካልመረጣችሁ ኢህአዴግን ምረጡ የሚሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገጥመውናል>>

ትልቅ ስራ ሰራን ብለን ልንኮፈስ አንችልም፣ ትልቅ ስራ ብንሰራ ኖሮማ አሁን በየወረዳው እየዞርን አናደራጅም ነበር

ብርሃኑ ተ/ያሬድ የሰማያዊ ፓርቲ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ

## የሰማያዊ አመራሮችና አባላት ዛሬ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ



አዲስ አበባ፡- ባለፈው ዕሁድ ማርች-8 የሴቶች ቀንን ምክንያት በማድረግ በተካሄደው የሴቶች የጎዳና ሩጫ ላይ በተሳተፉበት ወቅት በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉት የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮችና አባላት ዛሬ መጋቢት 5 ቀን 2006 ዓ.ም ፍርድ ቤት ይቀርባሉ፡፡

አመራሮቹና አባላቱ ለእስር የተዳረጉት ከጎዳና ሩጫው ዋና ዓላማ በተለየ ሌሎች ያልተገቡ ድርጊቶችን አሳይታችኋል በሚል ነበር፡፡ አመራሮቹና አባላቱ ባለፈው ሰኞ ፍርድ ቤት በቀርቡበት ወቅት ፖሊስ መረጃ ለመሰብሰብ የ14 ቀን ጊዜ የጠየቀ ሲሆን፣ ታሳሪዎቹ በበኩላቸው መደበኛ ስራ ላይ የተሰማሩና ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ በዋስ እንዲለቀቁና ከውጭ ሆነው ሂደቱን እንዲከታተሉ ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ሰምቶ የአምስት ቀናት ቀጠሮ በመስጠት ለዛሬ መጋቢት 5 በድጋሜ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ማስተላለፉ ይታወሳል፡፡

በዕለቱ ታሳሪዎቹ በቁጥጥር ስር ከመዋላቸው ቀደም ብለው የተለያዩ የእኩልነትና የፍትህ ጥያቄዎችን ሲያስተጋቡ እንደነበርና ያላግባብ ታስረዋል ያሏቸውን የህሊና እስረኞች ይፈቱ ዘንድ ይጠይቁ እንደነበር ተጠቅሷል፡፡

‹‹ፍትህ ናፈቀን! ርዕዮት ዓለሙና ሌሎች የህሊና እስረኞች ይፈቱ! ውሃ ናፈቀን! መብራት ናፈቀን!...›› እና ሌሎችንም የነጻነትና የፍትህ ጥያቄዎችን ያነገቡ መፈክሮችን ሲያሰሙ እንደነበር ተገልጹዋል፡፡ በሩጫው ከተሳተፉ ሴት ታሳሪዎች ውጭ በዕለቱ በአካባቢው የነበሩት የሰማያዊ ፓርቲ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ አቶ ጌታነህ ባልቻ እና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው አቶ ብርሃኑ ተክለያሬድ ይገኙበታል፡፡ በአጠቃላይ ቁጥራቸው ዘጠኝ መሆኑንም ከፓርቲው የህግ ጉዳዮች ኃላፊ አቶ ይድነቃቸው ከበደ ለመረዳት ተችሏል፡፡


ሰማያዊ በአርባ ምንጭ ህዝባዊ ስብሰባ ያካሂዳል 6

የህዝብ የአገልግሎት ጥያቄ አስቸኳይ ምላሽ ያሻል! 2

# ርዕሰ አንቀጽ

## የህዝብ የአገልግሎት ጥያቄ አስቸኳይ ምላሽ ያሻል!

የነጻ ኢኮኖሚ ስርዓትን ባሰፈኑ አገራት ከመንግስት ይልቅ ባለሃብቱ ተወዳድሮ ተገቢና ፈጣን አገልግሎትን ለህዝብ ያቀርባል፡፡ ህዝብም በዋጋም ሆነ በጥራት የተሻለውን አገልግሎት አማርጦ ይገዛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መንግስት ኢኮኖሚውን በቀጥታም ሆነ በእጃዙር በተቆጣጠረባቸው አገራት መሰረታዊ አገልግሎትን ለህዝብ ማዳረስ ዋነኛው የመንግስት ስራ ይሆናል፡፡ በአገራችን ኢኮኖሚው ከመንግስትም ወርዶ በገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ስር ከዋለ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ገዥው ፓርቲ የስልጣን መከታ ያደረገውን የአገሪቱን ኢኮኖሚና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን ለግል ባለሃብቶች ለመልቀቅ ፈቃደኛ አለመሆኑ ህዝብ ተገቢውን አገልግሎት እንዳያገኝ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡

መንግስት ኢኮኖሚውን እመራለሁ በሚልባቸው ሌሎች አገራት የግል ባለሀብቶች እንደ መብራት፣ ውሃና ቴሌኮሚኒኬሽን ያሉትን አገልግሎቶች ከግል ባለሃብቶች አሊያም ከራሱ ከመንግስት ጋር በመወዳደር ለህዝብ ያቀርባሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እነዚህ ቁልፍ የህዝብ አገልግሎቶች በመንግስት ቁጥጥር ስር ብቻ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን አገልግሎቶች ሞጭጮ የያዘው መንግስት ህዝብ ከአመት አመት የተሻለ የመብራት፣ የውሃና የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት እንደሚያገኝ ቃል ከመግባት ባይቆጠብም አገልግሎቶቹ ግን አመት አመት ህዝብን እያማረሩ ቀጥለዋል፡፡

በተደጋጋሚ የኃይል ማመንጫዎች እንደተሰሩና እየተሰሩ እንደሆነ ቢነገርም መብራት እስካሁን ከነበረውም በባሰ አዲስ አበባን ጨምሮ በመላ አገሪቱ በአንዴ ጠፍቶ እያደረ ስለመሆኑ ሰሞነኛ ክስተት ነው፡፡ ህዝብ ጨለማ ውስጥ በሚኖርበት በአሁኑ ወቅት ጂቡቲን ጨምሮ ለጎረቤት ሀገራት መብራት እየተሸጠ መሆኑ የመንግስትን ግድ የለሽነት የሚያሳይ ነው፡፡ ህዝብ ጨለማ ውስጥ ሆኖ በቀጣይ የተሻለ መብራት እንደሚያገኝ ቃል ለመግባት የማይታክተው መንግስት አሁንም ለአባይ ግድብ የመንግስት ሰራተኞች፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ተማሪዎች ላይ ገንዘብ እየሰበሰበ ይገኛል፡፡ ከዚህም ባሻገር በመብራትና በሌሎች አገልግሎቶች መቆራረጥና መጥፋት ምክንያት ንግድ ቤቶች እየተዘጉ ነው፡፡

በውሃ እጥረት ምክንያት ተማሪዎችና አዛውንቶች ካለ አቅማቸው ከሰፈር ሰፈር እየተንከራተቱ በጀርባቸው ለመሸከም ተገደዋል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣው የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ምክንያት ህዝብ ስልክና ኢንተርኔት መጠቀም አልቻለም፡፡ ባልታቀዱ ግንባታዎች ምክንያት የሚፈራርሱት መንገዶች ህዝብ በሰዓት ወዳሰበበት ቦታ እንዳይደርስ አድርገዋል፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች የሰማይ ያህል በራቁበት ወቅት ሙስና፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ ህዝብ ሊያገኘው በሚገባው አገልግሎት ላይ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆነውበታል፡፡

ያለ መብራት፣ ውሃና ቴሌኮሚኒኬሽን ህዝብ ሰርቶ ለማትረፍ ይቅርና የራሱን ህይወት ለማሰንበትም እየተቸገረ ነው፡፡ ተግባሩን በሚገባ የማይወጣው መንግስትና ደካማ ተቋማቱ ህዝብ ለእነዚህ የሚቆራረጡና የሚጠፉ አገልግሎቶች ክፍያ አንድና ሁለት ቀን ዘግይቶ ሲከፍል ተገቢ ያልሆነ ቅጣት ይጥላሉ፡፡ ሃይ ባይ ያጣው መንግስትና ተቋማቱ የህዝብን አገልግሎት ሲያቆራርጡና ሲያጠፉ ግን ህዝብ ምንም አይነት ካሳ እያገኘ አይደለም፡፡

ደንበኞች የአገልግሎት ክፍያ የሚከፍሉት በሚሰጣቸው አገልግሎት ሳይረኩና አንዳንዴም ጭራሽ አገልግሎቱን ሳይጠቀሙ ነው፡፡ ይህም መንግስት ያለምንም ሌላ አማራጭ ብቸኛ የአገልግሎት ሰጭ ተቋማቱ ተቆጣጣሪና ባለቤት በመሆኑ ነው፡፡ ህዝብ አማራጭ ተነፍጎታል፡፡ የውሃ ያለህ እያለ ነው! የመብራት ያለህ እያለ ነው! የስልክ ያለህ እያለ ነው! በአጠቃላይ የአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ህዝብ እየጮኸ ነው፡፡ በተለያየ መልኩም እሮሮውን እያሰማ ነው፡፡ መንግስት ግን ለዚህ የህዝብ ጩኸት ምላሽ መስጠት ተስኖታል፡፡

ነገረ-ኢትዮጵያ ህዝብ እያለቀሰ መቀጠል የለበትም ትላለች፡፡ ስለሆነም መንግስት ለህዝብ ጩኸት ጆሮ መስጠትና በተደጋጋሚ ህዝቡ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች አስቸኳይ ምላሽ መስጠት እንዳለበት አበክራ ታሳስባለች!

## እንዲህም ተብሏል

‹‹እውነት ምን ያህል ትቢያ ላይ ብትጣል ትቢያዋን አራግፋ በድል የምንቆምበት የመኸር ዘመን ይመጣል፡፡ ያን ጊዜም የነጻነት ብርሃን እንደ ማለዳ ፀሐይ የሚፈነጥቅ ይሆናል፡፡››

አንዱዓለም አራጌ፣ ያልተሄደበት መንገድ

‹‹ደርግ የሚፈልገውን በጠራራ ፀሐይ ደጃፍ ላይ ገድሎ ‹‹የፍየል ወጠጤን......›› እያስዘፈን ይፎክራል፣ ኢህአዴግ የሚፈልገውን ጨለማ ውስጥ በስውር ገድሎ ይቀብርና ጧት ‹‹እከልዬን ምን ነካብኝ ኧረ የት ገባ ኑ አፋልጉኝ እስኪ ይላል፡፡››

ሻምበል አስረስ ገላነህ፣ የካድሬው ማስታወሻ

‹‹እኔ የእናንተን ሞት አያለሁ፤ እናንተ ግን የእኔን ሞት አታዩም፡፡››

ፕሬዚዳንት መንግስቱ ኃ/ማርያም

‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ በሌላው ዓለም የሌለ ትልቅ ትዕግስት አሳይቷል፡፡ ይህ ህዝብ የታገሰውም ከቀን ወደ ቀን መሻሻል ይኖር ይሆናል በሚል ነበር፡፡›› አልጋ ወራሽ ልዑል አስፋው ወሰን

አንደኛ ዓመት ቅጽ 1. ቁጥር 4

ነገረ-ኢትዮጵያ ጋዜጣ ጥር 2006 ዓ.ም ተመሰረተች፡፡ ነገረ-ኢትዮጵያ በሰማያዊ ፓርቲ አሳታሚነት የምትታተም ፖለቲካዊ፣ ወቅታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የምትዳስስ በየሳምንቱ አርብ የምትወጣ ጋዜጣ ናት፡፡

ጋዜጣዋ ሚዛናዊና ነጻ ሆና የማገልገል መርህ አላት፤ ማንኛውም ሀሳብ በነጻነት የሚስተናገድባትና የሚንሸራሸርባት እንድትሆን እንፈልጋለን፡፡ ገዥው ፓርቲም ቢሆን አቋሙንና ፖሊሲውን ለመግለጽ ቢፈልግ የሰፌ ሚዲያ ባለቤት ነው ብለን ዕድሉን አንነፍገውም፤ በራችን ለሁሉም ክፍት ነው፡፡

የአሳታሚ አድራሻ:- የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/10
ቤት ቁ.460
E-mail:- info@semayawiparty.org
P.O.Box: 180298

ዋና አዘጋጅ
ጌታቸው ሺፈራው
የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02
ቤት ቁ. 07/859/14
E-mail:-gecholink@gmail.com
ስልክ ቁጥር:- 09-10-45-99-32

ምክትል ዋና አዘጋጅ
በላይ ማናዬ
የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02
ቤት ቁ.099
E-mail:- belaymb@gmail.com
ስልክ ቁጥር:-09-20-19-09-72

አምደኞች
ፕ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም
ታዴዎስ ታንቱ
ታምራት ታረቀኝ
አፈወርቅ በደዊ
እያስፔድ ተስፋዬ

አታሚ፡ ኪሃራኢ ህትመትና ማስታወቂያ
0921881755

# አምጽ . . . ሐገርህን አስመልስ !



በላይ ማናዬ

የአንተ ጊዜ አሁን ነው! አትፍዘዝ። በዳዮችህ እንድትፈዝ ስለፈለጉ አንተ ፈዘህ እኩይ ዓላማቸውን እንዲያሳኩ አትተባበር። ጊዜው ያንተ አይደለም ሲሉህ አትስማቸው። ይህ ፈጽሞ ልክ አይደለም። አታውቅም ሲሉህ አውቃለሁ በላቸው፤ እንደምታውቅ አሳያቸው። አንገትህን መድፋት ለሚያስደስታቸው በዳዮችህ ልግምተኛና አበያ እንጂ ቀና አትሁን። አምጽ! አዎ አምጽ! እምቢ በል። ‹‹የነገ ሐገር ተረካቢ...›› ምናምን... ዝባዝንኪ እያሉ ሲነግዱብህ እምቢ ስለሐገሬ በል። አንተ የነገ ሳይሆን የዛሬ ሐገር ተረካቢ ነህ። ነገማ እንደማነኛውም ፍጡር ታልፋለህ። ከማለፍህ በፊት ግን የማያልፍ ስራ አከናውን፤ ታሪክ የሚያስታውስህ ‹‹የነገ ሐገር ተረካቢ....›› ስለተባልክ ሳይሆን የሚታወስ ጉልህ ተግባር ዛሬ ላይ ስትሰራ መሆኑን ልብ በል። ይህን ሐቅ ግን ገዥዎችህ እያወቁ ሲክዱህ ዝም አትበላቸው።

ስለሆነም አምጽ!

ለሁሉም ጊዜ አለው...‹‹ጊዜ ለኩሉ›› ይላል ታላቁ መጽሐፍ። ልክ ነው ለሁሉም ጊዜ አለው። ይህ ጊዜ ግን ነገ አይደለም፤ ዛሬ ነው። ገዥዎችህ ያንተ ጊዜ ነገ ነው...ዛሬ እኛ የምንልህን ብቻ ስማ፣ የምናዝዝህን ፈጽም፣ ለሁሉም ነገር እኛ እናውቅልሃለን ሲሉህ አትስማቸው። ስለአንተ እነሱ አድራጊ ፈጣሪ ሲሆኑብህ አትታገሳቸው። ጊዜው የአንተ ነው! አይደለም የሚሉህ ካሉ በኃይል እንደተሳሳቱ መልሰህ ለራሳቸው ንገራቸው።

ያንተ ጊዜ አሁን ነው። አንተ በትናንት ብቻ የምትኖር፣ በነገ ብቻ የምትጽናና ሳትሆን ዛሬን ያንተ ማድረግ የምትችል ብቁ ነህ። አዎ ገዥዎችህ ዛሬ ላይ ሆነው የነገ ሐገር ተረካቢ ይሉሃል። ግን ደግሞ ትናንትም የነገ ሐገር ተረካቢ ተብለህ እንደነበር አስታውስ። እነዚህ ሙሰኛ ገዥዎችህ ነገም ሳያፍሩ የነገ ሐገር ተረካቢ ነህ ይሉሃል። ታዲያ ያንተ ጊዜ...ሐገር የምትረከበው መቼ ነው!? መልሱ ከራስህ ነው፤ እሱም ዛሬ የሚል ነው። ይህን ሐቅ ግን በኃይል ተክደሃል።

ስለሆነም አምጽ!

አምጽ...ሐገርህንም አስመልስ። ይህቺ ሐገር ኢትዮጵያ ናት። እሷም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ናት። ደግሜ ላስታውስህ፣ ይህ ሐቅ አሁን በቦታው የለም። ተዛንፏል። አንተ ሐገርህን ተነጥቀሃል። ኢትዮጵያ ያንተ መሆን ሲገባት የባዕዳንና የ‹‹ወገን ሌቦች›› መነሐሪያ ሆናለች። ኢትዮጵያ ዛሬ ያንተ ብትሆን ኖሮ ከአንድ ቻይናዊ የበታች ሆነህ ባልታየህ ነበር። አሁን አሁን በሐገርህ ቻይናዊ ሲደበድብህ ዝም እንድትል ተፈርዶብሃል። የሐገርህን ሐብት አንተ እንድትጠቀምበት ሳይሆን ቻይና እንዲመዘብረው ተመቻችቷል። ለዚህ መድሃኒቱ ማመጽ ነው። እምቢ ማለት ይህኔ ነው።

እስኪ ዙሪያህን ተመልከት! ከተማው እኮ አንተን አይመስልም። መልኩ ይለያል። ብዙሃኑ በችጋር እየተሰቃዩ ጥቂቶች በበዛ ቅንጦት ሲንደላቀቁ ነው የምትመለከተው። የሐገርህ ንብረት ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ ካልዋለ ሐገርህን ተነጥቀሃልና ለማስመለስ ተነስ። አምጽ! ሐገሬ የምትላት እኮ በድንህን ብቻ ይዘህ ስለምትዞርባት አይደለም። ሐገርህን ሐገሬ የምትላት የምር ሐገርህ ስትሆን ነው። ሐገርህ ሰው ሰው ካልሸተተችህ ያለኸው የባዕድ ሐገር ውስጥ ነው ማለት ነው። አንተ ሐገርህን፣ ሐገርህ ደግሞ አንተን ካልመሰለች ወስደውብሃል ማለት ነው። ሐገር ደግሞ ዝም ተብሎ አይሰጥም። እናም አምጽ... ሐገርህን አስመልስ።

በዙሪያህ ጥቂት ሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች ቢገነቡ ገብተህ ስታያቸው ያንተ አይደሉም። አዎ ለአንተ ቦታ የላቸውም። ምክንያቱም ከተማው የአንተን ቀለም አልያዘም። አንተን ዘንግቶ በጥቂቶች ቁሳዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተና ለእነሱ ስጋ ፈርስኪ ማርኪያ የተቀየደ ነው። አንተማ ሐገርህን ተነጥቀሃል። የጥቅሙ ተጋሪ እንድትሆን አልተፈለገም። የአንተ የኢኮኖሚና የመንፈስ ከፍታ መኖር ለሙሰኛ ገዥዎችህ እንደማይበጅ ያውቃሉና የበይ ተመልካች እንድትሆን ብቻ ነው የሚፈልጉት። አንተ ግን የእነሱን ፍላጎት ብቻ የምትከተል አትሁን ነው እያልኩህ ያለሁት።

በቃ አምጽ! ይህ ኢትዮጵያ ነው! በሐገርህ እየኖርክ ባይተዋር አትሁን። አምባገነኖች ስልጣን እንጂ አንተ ትዝ አትላቸውም። እንዲሁ ዝም ስላልካቸው ነገ ስልጣኑን ያስረክቡኛል ብለህ አትስብ። መቼም ስልጣናቸውን ለማስረከብ ዝግጁዎች አይደሉም። (ሞት ብቻ ነው እነሱን ከስልጣናቸው ላይ ሲያነሳቸው ያየነው!) ስለዚህ ነው አምጽ የምልህ። ለምንስ ከእነሱ እንደ ችሮታ ስልጣኑ እስኪሰጥህ ትጠብቃለህ! አንተ በብቃትህ ውሰድ! በቃ ሐገርህን አስመልስ።

ደግሞ ከስራቸው ሆነው ፍርፋሪ የሚለቅሙትን የዕድሜ ዕኩዮችህን እየጠቀሱ ‹‹በመልካምነታቸው መጠቀምክን›› ሊነግሩህ ይሞክራሉ። ዳሩ እነዚህ ዕኩዮችህ ቁጥራቸውን አታጣውም። ስለምን ከእግር ስር ሆነው ፍርፋሪ እንደሚለቅሙ እነሱ ይወቁት። ግን አንድ ነገር አለ... በሐገርህ ላይ ከእግር ስር ሆነህ ፍርፋሪ እየለቀምክ አፍክን ዘግተህ ተቀመጥ ስትባል እሺ ካልክ መንቃት አለብህ። ጠይቅ...ለምን በሐገሬ ላይ ፍርፋሪ ብቻ የምለቅም እሆናለሁ ብለህ ጠይቅ! መልሱ የምትኖረው በባዕድ ሐገር ነው የሚል ይሆናል። ምክንያቱም ሐገርህ ተወስዳለች። አንተ በቦታህ፣ በሐገርህ መሬት ላይ እያለህ ሐገርህን ቦርቡረው ወስደዋታል። እናም አምጽ... ሐገርህን አስመልስ! አትሰደድ! ለማን ብለህ ትሸሻለህ....ስለምን የአባቶችህን ውርስ ርስትህን ለሆድ-አደሮች ትተህላቸው ትሄዳለህ!? አንተ ትተኸው የምትሸሸውን ጭቆና ማን እንዲያስወግድልህ ትፈልጋለህ። ማንም ሌላ አካል የለም! እርግጠኛ ሁን....አንተ ነህ መድሃኒቱ!

እርግጥ ነው ይህን ስታደርግ የሚፈሩ ይኖራሉ። አመጹን የሚፈሩ ወገኖች ግን ሌቦች መሆን አለባቸው። ነገር ግን አትስጋ! ሲጀመር የአንተ አመጽ በእነዚህ ሌቦች ላይ ነውና። አንተ እየተሰቃየህ እሱ በጋራ የሐገርህ ሐብት ላይ የሚንደላቀቀው ማን ስለሆነ ነው...? የእነሱን ባዶ የተስፋ ወሬ ብቻ እየሰማህ እስከመቼ ትረገጣለህ? እስኪ ዓለምን ለአንድ አፍታ አስባት...በጣም ተለውጣለች! የሰዎች ኑሮ እየተለወጠ ነው። የተሻለ ነጻነት እየታየ ነው። አንተ ግን ዛሬም ‹‹የነገ...›› እየተባልክ አለህ። የቀደምክ እንዳልነበርክ ዛሬ እጅግ የኋላ ጭራ ለመሆን በቅተሃል። እስኪ ደግሜ ልጠይቅህ....ግን እስከመቼ?

ምናልባት አንተን ሁሌም ‹‹የነገ...›› የሚሉህ ገና አልበሰለም ብለው ነው ብለህ ልታስብ ትችላለህ። ይህ ግን ፈጽሞ ልክ አይደለም። አንተ ወጣት ነህ! ትችላለህ! በደንብ ትችላለህ። ስንቶቹ በወጣትነት ዕድሜያቸው ዓለምን የሚለውጥና የለወጠ ተግባርን እንዳከናወኑ አስታውሳቸው። ዛሬ አንተን ረግጠው የያዙህ ሰዎች ሳይቀር ወጣትነታቸውን ‹‹በነገ...›› አልተሸነገሉበትም። ለዚህ ነው የአንተ ጊዜ ዛሬ ነው የምልህ። አንተ በአዕምሮም በአካልም ጎምርተሃል። ገናም እየጎመራህ ትሄዳለህ! በሴረኞች የተሰለበው ወኔህን አስመልስ። ሐገርህን አስመልስ። አንተ ትችላለህ!

ደግሞ እኮ በዕድሜ አርጅተው አፍግተው ሳለ ከአንተ በታች ገና ጨቅላዎች መኖራቸውን አትርሳ። አካላቸው ቢገዝፍም አዕምሯቸው ገና ጨቅላ የሆኑ ሰዎች አሉ። ገዥዎችህ ሁሉ የበሰሉ ይመስሉሃል? ስንት አሉ ቦርጫቸው ገፍቶ ሳለ አስተሳሰባቸው ሾጣጣ ሆኖ ሐገር የሚያወድሙት? ስንት አሉ የባለ አቅሙን ሰው ቦታ ያለ አቅማቸው ይዘው ወገንን የሚያስለቅሱት? ስንት አሉ ከዕድሜያቸው እጅጉን ዘግይተው በልጅነት ዕቃ ዕቃ ጨዋታ የሚያንጨባርቁት? እና እነዚህ ሰዎች አንተን ‹‹ዛሬ አትችልም...የነገ ሐገር ተረካቢ ነህ...›› እያሉ ሊሸነግሉህ ሲሞክሩ ዝም ትላቸዋለህ? ዝም አትበላቸው። አምጽባቸው! ከላይ ቡድን ሰርተው የነጠቁህን ሐገር አስመልሰህ ለአንተም ለወገንህም የለውጥ ብርሃን ፈንጥቅላቸው። ዛሬ የአንተ ጊዜ ነው። ለውጡን አምጣው። ደግሞ ትችላለህ!

አምጽ! ማመጽ ስልህ መልኩ ብዙ ነው። አይነቱ ሰፊ ነው። በዚህም አለ በዚያ ግን ሐገርህን የቀማ ስርዓት ላይ ለማመጽ ቁረጥ። ለጨቋኝ አገዛዝ አትተባበር። ዝምታህ ፍርሃት ነው ወይስ ትዕግስት? ግፍን መታገስ ለምን? በስንቱ ተበድለህ ዝም ትላለህ? ውሃ እየጠማህ ዝም! ጨለማ እየዋጠህ ዝም! (በነገርህ ላይ ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የመብራት መቆራረጥ ችግር ማብቃቱን ከነገሩህ ዓመታት ተቆጠሩ። ‹ከእንግዲህ ሻማ የምትገዙት ለልደታችሁ ማክበሪያ ብቻ ነው› ብለውህ ነበር። ግና ችግሩ ሲብስ እንጂ ሲሻል አላየንም። ምክንያቱም ሰዎቹ አቅም የላቸውም! እናም ዛሬም የመብራት ብልጭ ድርግሙ ቀጥሏል። አንተ ይህን ሁኔታ መቀየር ትችላለህ ነው የምልህ!) ስልክህ ተቋርጦ ዝም! ባንክ ቤት ሄደህ ኔትወርክ የለም ተብለህ ገንዘብህን ሳይሰጡህ ሲቀሩም ዝም! መንገድህ ተዘግቶ ዝም! የምትበላው እየቸገረህም ዝም!... ለሶስተኛ ጊዜ ልጠይቅህ....ግን እስከመቼ? በቃ አምጽ! እምቢ በል። ካልደፈረሰ አይጠራም ይሉ የለ አበው። ሐገርህ በግፈኛ ገዥዎችህ በኩል አንተን ባይተዋር ስታደርግህ ዝም ማለት ይብቃህ።

ደግሞ እኮ ለማመጽ ምቹ ነው። አትሸነፍ! ለውጥ ላይመጣ ነገር እያልክ ራስህን አትሸንግል። አንተ የለውጡ ሐዋርያ እንጂ የዳር ተመልካች አይደለህም። ግባና ታገል! ከአማራጭ የዴሞክራሲ ኃይሎች ጋር ስለሐገርህና ወገንህ ስትል ጨቋኞችን ለመታገል ተነስ። ካሻህም ራሱ ገዥው ውስጥ ግባና ወገን የሚያጭድበት ሆዱን ቦርቡረው። እዚህ ጋር የዘንዶውንና የአንተን መሳይ ወጣት ታሪክ ላውሳልህ።

ዘንዶው እጅግ በጣም ግዙፍ ይመስላል። እውነትም ሲታይ ግዙፍ ነበር። በማናለብኝነት የሚጀባነን አይነት ትልቅ ዘንዶ ነበር። አንድ ቀን እንደለመደው ለፈርሱ ማርኪያ የሚበላ ነገር ሊቃርም ሲወጣ አንድ በአጭር የታጠቀ ቆፍጣና ወጣት በአጠገቡ ያያል። ወጣቱም ወዲያው ዘንዶውን አይቶት ኖሮ ዞር ከማለቱ ዘንዶው ተጥመልምሎ ይጠመጠምበታል። ወጣቱ ልበ-ሙሉ ነበር። ሳይደናገጥ ታገለው። ግን ዘንዶው ብልጫ የወሰደ መሰለ። ዘንዶውም ወጣቱን ጨርሶ ለማሸነፍ እየሞከረ ለመዋጥ ቋምጦ ወጣቱን እያመቻቸው ሄደ። በዚህ ጊዜ ወጣቱ በእጁ የያዘውን ነገር አስታወሰ። እናም ዘንዶው ለመዋጥ ወጣቱን ወደ ሆዱ ሲገፋ ወጣቱ በበኩሉ በያዘው ስለት ነገር የዘንዶውን ሆድ እየቀደደ ትግሉን በየፊናቸው ተያያዙት። ዘንዶው ተሸነፈ። ከርቀት ሮጦ ለማምለጥ ያልቻለው ወጣት ቀርቦ ሆዱን በመቦርቦር አሸነፈው።

አንተን ጨቋኙ ውስጥ ሰርገህ ገብተህ ቦርቡረው የምልህ እንዲህ አድርገህ ነው። ትችላለህ! ለይስሙላህ በገዥዎችህ የተመሰረቱ ማህበራትና አደረጃጀቶችን ለእንዲህ አይነት ትግል ልትጠቀምባቸው ብትችል ማን ይከለክልሃል! አትፍራ! ግባና በሐሳብ ልዕልና እንዳለህ አሳያቸው። የሐሳብ ተጋሪዎችህን አፍራ። ከእነሱም ውስጥ መንገዱ የጠፋባቸው ቢኖሩ አሳያቸው። በቃ ጨቋኙ ስርዓት ራሱን እንዲበላ ከማድረግ የሚከለክልህ ፍረሃትህ ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል...ምክንያቱም አንተ ትችላለህ። አንድ አብዮተኛ ግብጻዊ ወጣት ሆስኒ ሙባረክን ለመታገል ቆርጦ በተነሳበት ወቅት እንዴት እንዳልፈራ ሲናገር ምን እንዳለ ታውቃለህ...‹‹I lost my fear!›› ነበር ያለው። ልክ ነው! አምባገነኖችን ስትታገል ፍርሃት የሚባል ነገር ስለመኖሩ እንኳ ማሰብ አይኖርብህም። ብዙ ወገንህ



ወደ ገፅ 6 ይዞራል

# ‹‹እኛን ካልመረጣችሁ ኢህአዴግን ምረጡ የሚሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገጥመውናል››

## ትልቅ ስራ ሰራን ብለን ልንኮፈስ አንችልም፣ ትልቅ ስራ ብንሰራ ኖሮማ አሁን በየወረዳው እየዞርን አናደራጅም ነበር

ብርሃኑ ተ/ያሬድ የሰማያዊ ፓርቲ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ

ነገረ-ኢት፡- የፓርቲያችሁ የልዑካን ቡድን በየክፍለ ሀገራቱ የመስክ ጉብኝት አድርጓል፡፡ የጉብኝቱ አላማ ምንድን ነበር?

አቶ ብርሃኑ፡- የሰማያዊ ፓርቲ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ክፍላተ-አገራት ላይ መዋቅሮችን በማጠናከር ነው ሲንቀሳቀስ የነበረው፡፡ ዋናው የጉዞው አላማ የነበረው የእያንዳንዱ አካባቢዎች ላይ ያሉንን መዋቅሮች ላይ የደከሙ መዋቅሮችን የማጠናከር ስራ የመስራት፤ ጠንካራ የምንላቸው ዞኖችን ደግሞ እንደ ልምድ ልውውጥ ለሌሎቹ ልምድ የሚሆንበትን መንገድ በማሳየት፣ እንደዚሁም ደግሞ ከዚህ ቁጭ ብለን ከዚህ ጠንካራ መዋቅር አለን፣ ከዚህ የተለየ ነገር አለን የሚለውን አመራር በተግባር ወርዶ ምን ያህል ሰው አደራጅተናል፣ ምን ያህል ሰው የአላማችን ደጋፊ ነው፣ ምን ያህል ሰው የእውነት አላማችንና ፕሮግራማችን አውቆ በእውቀት ይደግፈናል የሚለውን ለማወቅ ነበር የጉዞው ዋና አላማ፡፡

ነገረ-ኢት፡- የትኞቹን የአገሪቱን ክፍሎች ነበር ያዳረሳችሁት?

አቶ ብርሃኑ፡- እንግዲህ ጉዞውን በሁለት ክፍል ነው የከፈልነው፡፡ አሁን የወጣንባቸው መስመሮች ክፍል አንድ ነው፡፡ ክፍል ሁለት የሚቀጥለው ነው የሚሆነው፡፡ አሁን በወጣንበት ጉዞ 200 ወረዳዎችን አዳርሰናል፡፡ ከዚህም በሶስት ቡድን ተከፍለን የመጀመሪያው (ቡድን አንድ) ደጀን፣ በደብረ ማርቆስ፣ ባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ወረታ...እነዚህን አካባቢዎች እየጎበኘ የሄደ ቡድን ነው፡፡ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ከአዲስ አበባ ተነስቶ፤ ደብረ ብርሃን፣ ሸዋ ሮቢት፣ ሰሜን ሸዋ ጅሩ አካባቢ፣ ደሴ፣ ወልደያ፣ እንደዚሁም ደቡብ ወሎ አካባቢ የሚገኙ ቦታዎች ነው ጉብኝት ያደረገው፡፡ ቡድን ሶስት ደግሞ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ሀድያ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ሲዳማና እዛው አካባቢ የሚገኙ የቡርጂ አካባቢ ዞኖችን እንዲጠናከሩ የማድረግ ስራ ሰርቷል፡፡

ይህ አሁን የጨረስነው የመጀመሪያ ዙር ነው፡፡ ሁለተኛው ዙር ደግሞ የሚሆነው አሁን ስራ አስፈጻሚዎች የሚሳተፉበት በጅማ በኩል ያለው ጅማ፣ በደሌ፣ ሮቤና የመሳሰሉትን አካባቢዎች አንድ ቡድን ጉዞ ያደርጋል፡፡ በአንጻሩ ቤንሻንጉልንና አካባቢውን ደግሞ ሌላ ቡድን፣ ያላዳራሳቸውን አካባቢዎች በሙሉ ማለትም ወደ ሀረርጌ መስመር፣ ድሬዳዋ፣ ጅጅጋ፣ ትግራይ መስመርን ጨምሮ ሌሎች ቡድኖች ጉዞ እንደሚያደርጉ እንጠብቃለን፡፡ ለጊዜው ባደረግነው ጉዞ ግን 200 ወረዳዎችን ያዳረሰ ጉዞ ነው ያደረግነው፡፡ በእነዚህ ጉዞዎች ከ200 አካባቢ ወረዳ የመጡ የዞን ማዕከላት (ለምሳሌ የሀድያ ዞን ሆሳና ላይ፣ የወላይታ ሶዶ ላይ፣ የጋሞጎፋ ዞን አርባ ምንጭ ላይ) እያንዳንዱን ወረዳ ተወካዮች አግኝተን አወያይተናል፡፡

ነገረ-ኢት፡- ለእነዚህ አካባቢዎች ቅድሚያ የሠጣችሁበት መነሻ ምንድን ነው?

አቶ ብርሃኑ፡- እነዚህን አካባቢዎች ቅድሚያ ስንሰጥ አሁን የተንቀሳቀንባቸው አካባቢዎች በፓርቲያችን ምስረታ ወቅት መስራች አባላት የነበሩበት፣ ፊርማ ያሰባሰብንበትና የተሻለ የእኛ መዋቅር ገብቶበት እየተንቀሳቀሰ ያለበትና በርካታ የእኛ አባላት ያሉበት የተሻለ የተባለ አካባቢ የተባለውን ነው ለመጎብኘት ጥረት ያደረግነው፡፡ በሙሉ ኃይላችን ገብተን እንደ አዲስ የምንሰራበት አይደለም፡፡ የተጠናከረ የነበረ ነው፡፡ ቢሮ ያልተከፈተበት ቦታ ላይ ቢሮ የመክፈት፣ አንዳንድ ችግሮች ያሉበት ቦታ ላይ ችግሮችን መፍታት እንደ ቅድሚያ የሠጠነው ስራ ነበር፡፡

ነገረ-ኢት፡- በእነዚህ አካባቢዎች ስትሄዱ የገጠማችሁ ችግር ምንድን ነበር?

አቶ ብርሃኑ፡- አዎ! እንግዲህ በየአካባቢው ስንሄድ ሊገጥመን የሚችል ነገር እንዳለ እናውቃለን፡፡ በተለይም ደግሞ ሰማያዊ ፓርቲ ሲባል በየዞኑ ያሉ የኢህአዴግ አባላትና አንዳንድ ደግሞ የገኘው ፓርቲ አጃቢ ፓርቲዎች ጭምር ሊከፋብን እንደሚችሉ እናምናለን፡፡ ለምሳሌ ወላይታ ላይ ችግር ገጥሞናል፡፡ ወላይታ ላይ ከ16 ወረዳዎች የመጡ ተወካዮችን አግኝተናል፡፡ ከአንድ አባላችን ቤት ስብሰባ አድርገን ነበር፡፡ ስብሰባው አልቆ ወደ አርባ ምንጭ ጉዞአችን ለመቀጠል መነሃሪያ ላይ መኪና ውስጥ ገብተን ወደ አርባ ምንጭ ጉዞ በጀመርንበት ወቅት መንገድ ላይ ሶስት ሰዎች ገቡ፡፡ እነዚህ ሶስት ሰዎች መኪናው ከከተማ ሊወጣ ባለበት ሰዓት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተመልሶ እንዲያዞር አደረጉትና ‹‹ውረዱ ትፈለጋላችሁ!›› አሉን፣ ‹‹አንወርድም እኛ ከዚህ ሁሉ ተለይተን ለምን እንፈለጋለን?›› የሚል ጥያቄ አነሳን፡፡ ትንሽ ሽብር ነበር የተፈጠረ የሚመስለው፡፡ በፖሊስና በሞተር መኪናውን ከበው፣ ህዝቡን አስወርደው፣ መኪናውን ፈትሸው እንድንወርድ አደረጉን፡፡ ወርደን ፖሊስ ጣቢያ ስንገባ መጀመሪያ ያነሱልን ጉዳይ ‹‹ወላይታ ስትገቡ አላስፈቀዳችሁም!›› የሚል ነበር፡፡ ‹‹ክልላችን ስትገቡ እንዲህ አይት ነገር ልንሰራ ገብተናል! ብላችሁ ማሳወቅ ነበረባችሁ›› የሚል ነው፡፡ እኛ ደግሞ ‹‹አገራችን ነው፣ የትም ለመግባት ማስፈቀድ አይጠበቅብንም፡፡ ከእኛ መዋቅር ጋር የመገናኘት እንጅ ከእናንተ ጋር ማስፈቀድ ግዴታ የለብንም፡፡›› የሚል ምልሽ ሰጠናቸው፡፡ በዛው ጎን ለጎንም ‹‹ህገ ወጥ መሳሪያ በማዘዋወር ጠርጥረናችኋል፣ ሽብርተኞች ናችሁ!›› የሚል ነገር አነሱ፡፡ ልክ እንደ ትልቅና የሚያስፈራ አካል ሻንጣችን ቀምተውና መሬት ላይ ዘርግተው ፍተሻ አደረጉ፡፡ በእርግጥ ያንን ለመጠርጠር የሚያበቃ ነገር አልነበራቸውም፡፡ ምክንያቱም እስር ቤት እንደ ጓደኛ ተያይዘን ነው የገባነው፡፡ መቼም መሳሪያ የያዘ ኃይል እንዲህ ይያዛል ብዬ አላምንም፡፡



ሻንጣችንን ፈተሹ፤ ውጭ እንድንቆይ ከተደረግን በኋላ ከምሽቱ አንድ ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት አካባቢ ዝናብ እያስመቱ ነው ያስመሹን፡፡

በዛው ጎን ለጎን ደግሞ ለምን አመራሮቻችን ታሰሩ ብለው የመጡ አቶ ወጨፎ ሳዳሞ የተባለውን የወላይታ ዞን ምክትል ሰብሳቢያችንና አቶ ታደመ የተባለ የወላይታ ዞን የድርጅት ጉዳይ ኃላፊያችንን አስረዋቸዋል፡፡ እነሱን እስር ቤት አስገብተው እኛን ዝናብ ለይ አቁመው ሲያስደበድቡን ካመሹ በኋላ ከምሽቱ አካባቢ ጠርተውን አንዳንድ በጣም አስቂኝ ንግግሮችን መናገር ጀመሩ፡፡ ‹‹ለምንድን ነው ከመንግስት ጋር ተስማምታችሁ የማትሰሩት? ህዝቡ አልመረረውም መታገል አይፈልግም፡፡›› በተለይ ደግሞ አስገራሚ የሚያደርገው ‹‹በጠቅላይ ሚኒስትሩ የትውልድ መንደር መጥታችሁ ለመቃወም መሞከራችሁ አስቂኝ ነው፡፡ ዳግም እንዳትሞክሩት፡፡ ስልጣን ወደ ደቡብ የገባበት ወቅት ነው፡፡ የአካባቢው ህዝብ ስልጣን ይዞ አገሪቱን እያስተዳደረ ባለበት ወቅት በአካባቢው መጥታችሁ ለመቃወም መሞከራችሁ ትክክል አይደለም፡፡ የሚል ነገር ነው ያነሱልን፡፡ እዚህ ላይ ከፖሊስ የማልጠብቀውን ብዙ ነገር አይቻለሁ፡፡ ለምሳሌ ከአንድ ፓርቲ መሪ በሚጠበቅ መልኩ ‹‹የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ ስለሌላችሁበት አሸባሪዎች ናችሁ!›› ብለውናል፡፡ የጋራ ምክር ቤት ያሉትን በስም እየጠሩ እነሱ ብቻ በአካባቢው መንቀሳቀስ እንደሚችሉ ነግረውናል፡፡

አንድ ክፍል አስገብተው ካሳደሩን በኋላ ጠዋት አራት ሰዓት ላይ ስልካችንንና ሻንጣዎቻችንን ሲመልሱልን ሀድያና ወላይታ ላይ ማስታወሻና ቃለ ጉባኤ የያዝንባቸውን ሰነዶች አልመለሱልንም፡፡ የከተማው ፖሊስ አዛዥ የሆነው ሻለቃ ሌሊሽ ሰንዶቻችንን እንዲሰጠን ስንጠይቀው ‹‹የደኢህዴን ሰዎች ወስደውብኛል፡፡ መመለስ አልችልም፡፡›› የሚል ምላሽ ነው የሰጠን፡፡ እነዚህ ሰነዶች አሁንም ድረስ አልተመለሱልንም፡፡ ፓርቲያችን የሚበትነው ብሮሸር፣ ሀድያና ወላይታ ላይ የያዝናቸው ቃለ ጉባኤዎች፣ ማስታወሻዎች፣ የፓርቲያችን ጋዜጣዎች፣ የአባላቶቻችን ስም ዝርዝር ወስደው አልመለሱልንም፡፡

ከሌላ አንጻር ስናየው ደግሞ በጣም ሚያስገርመው ሁኔታ ተቃዋሚ ፓርቲ ነን የሚሉ ሰዎች፣ በግልጽ ለመናገር ደቡብ ህብረት ‹‹ህብረትን ካልመረጣችሁ ኢህአዴግን ብትመርጡ ይሻላል›› የሚል ቅስቀሳ እያደረጉ መሆኑን ከአባላቶቻችንና ከአካባቢው ሰው ማወቅ ችለናል፡፡ በተመሳሳይ ኢህአዴግም ‹‹ተቃዋሚ ነን የምትሉ ከሆነ ከህብረት ጋር መሆን አለባችሁ፡፡ ሰማያዊ ፓርቲ ጋር መሆን የለባችሁም፡፡ አሸባሪ ነው›› የመሳሰሉትን ቅስቀሳዎች ሲያደርጉ እንደነበር በደንብ አይተናል፡፡ ይህን ያየነው ሀድያ፣ ወላይታ፣ ጋሞ ጎፋ፣ አርባ ምንጭ ላይም እንዲህ አይነት ቅስቀሳዎችን አይተናል፡፡

ነገረ-ኢት፡- የጉዞው ውጤት በአጠቃላይ ስኬታማ ነበር ማለት ይቻላል?

አቶ ብርሃኑ፡- አንደኛ ነገር አልተለመደም፡፡ ከአባላቶቻችን እንደተረዳነው በአካባቢው የፓርቲ መሪዎች ለሆነ ስብሰባ ሄደው ሆቴል ውስጥ ቁጭ ብለው የተወሰኑ ሰዎችን አነጋግረው የሚመለሱበት ልምድ ነው የነበረው፡፡ አሁን ስለ ፓርቲያችን ብዙ ነገር ማወቅ የሚፈልግ ሰው አግኝተናል፡፡ በዚህ ስኬታማነቱን እናያለን፡፡ ከዚህ በፊት ደግሞ ሌሎች ፓርቲዎች ያደረሱበት ጠባሳም አለ፡፡ ስለዚህ ፓርቲያችንን አምኖ ለመታገል፣ ደጋፊ፣ አባል፣ አመራር ለመሆን ፈራ ተባ እያለ የነበረ ህዝብ ነበር እዛ አካባቢ የነበረው፡፡ የእኛን መሄድ ስኬታማ ነበር የምንለው በማህራዊ ሚዲያ ጨምሮ ‹‹ሰማያዊዎች እዚህ ደረሱ!›› ሲባል የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ መምህራንና የአካባቢው ህዝብ እኛን ለማግኘት ጥረት አድርገዋል፡፡ ስለ ፓርቲያችን ለማወቅ የሚፈልጉትን ነገር በሙሉ ጠይቀውን እያንዳንዱን ነገር አስረድተናቸዋል፡፡ እነሱም ከፓርቲያችን ጎን ቆመው መታገል እንደፈሚፈልጉ ነግረውናል፡፡ ሌላው አሁን ወላይታ ላይ እንዳደረግነው፤ ህዝቡ ኢህአዴግ ሰማያዊን ምን ያህል አጥብቆ እንደሚፈራው፣ ሰማያዊ ደግሞ ከተለጣፊ ፓርቲዎች የሚለይ እውነተኛ የህዝብ ልጅ መሆኑን አሳይቷል፡፡ በብዛት ያነሱልን የነበረው ጥያቄ ‹‹ከዚህ በፊት እንደነበሩት ተለጣፊ ፓርቲዎች ላለመሆናችሁ ምን ማረጋገጫ አለን?›› የሚል ነበር፡፡ በዚህ በነበረን ቆይታም ታማኝ የህዝብ ፓርቲ እንደሆነ ማረጋገጥ ችለናል፡፡ ይህም ሌላኛው ስኬት ነው፡፡

ሶስተኛውና ዋናው ስኬት ግን መዋቅሮቻችን በአግባቡ መገምገማችን ነው፡፡ ምን ያህል መዋቅር አለን? የትኛው አካባቢ ያሉ መዋቅሮችንን ነው ማጠናከር ያለብን? የትኛው አካባቢ ነው የተሻለ? የትኛውስ አካባቢ የሰማያዊ አላማና ፕሮግራም አምኖ እየታገለ ያለው? የትኛውን አካባቢ ነው በደንብ ማሳመን ያለብን? ህዝባዊ ስብሰባዎች፣ ሌሎች ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችስ ማድረግ ያለብን

ወደ ገፅ 13 ይዞራል

# የፖሊሱ <<መንግስት>>



ጌታቸው ሺፈራው

የፖሊስ ዋነኛው ተግባር የሰውን ህይወት፣ ነጻነት፣ ፍትህ፣ ሀብትና ንብረት ሰብአዊ መብትና ክብር ማስከበር ነው፡፡ ይህም አንድ በማህበረሰብ ውስጥ የደህንነት ስሜትን ለመፍጠርና ለማስቀጠል ያስችላል፡፡ በእነዚህ መርሆች የሚሰራው ፖሊስ የአገርና የህዝብ ፖሊስ ነው፡፡ ፖሊስ በተግባሩ የሚከታተለው ማህበረሰቡን የሚጎዱ ህገ-ወጦችን ነው፡፡ ሆኖም ይህን የህዝብ አገልጋይ የፖለቲካ ቡድኖች በተለይም መንግስታት መጠቀሚያ ሲያደርጉት ይስተዋላል፡፡ ፖሊስ የመንግስት (ፓርቲ) መገልገያ ከሆነ ህዝብን ሳይሆን በስልጣን ላይ ያሉትን አካላት ነው የሚያገለግለው፡፡ ተግባሩም ማህበረሰቡን የሚጎዱ ድርጊቶችን በመከታተል የህዝብንና የአገርን ደህንነት ከማስጠበቅ ይልቅ ገዥው አካል ከራሱ ስልጣን አንጻር ህገ ወጥ የሚላቸውን ‹‹ህገ ወጦች›› ማደን ይሆናል፡፡ በተቃራኒው ለህዝብ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ይቀንሳሉ፡፡ ህዝብ በፖሊስ ተግባራት የደህንነት ዋስትና ስሜት ከመጠበቁ በተቃራኒ በፖሊስ ክትትልና ተግባራቱ ፍርሃት ውስጥ ይገባል፡፡ ገዥዎች ደግሞ የመግዛትና በስልጣን ላይ የመኖር ዋስትናቸውን ያገኛሉ፡፡ ይህ በሆነበት ስልጣን ላይ ያለው የፖለቲካ ቡድን ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ በማስመሰል ለራሱ አገልግሎት ይጠቀምበታል፡፡ የህዝብን ጆሮ ከሚጠባ፣ ለመንግስት ሲል መብቱንና ክብሩን ከሚረግጥ፣ መብቶቹን ከሚጥስ ፖሊስ ውጭ በስልጣን ላይ የማይኖር ያህል ይታሰባል፡፡ ፖሊስን ህዝቡን እንዲቆጣጠር የሚያደርገው ይህ መንግስት ፖሊስና ሌሎች ተቋማት በህዝብ ላይ (ለገዥዎች ጥቅም) በየትኛውም ጉዳይ ላይ ፖሊሳዊ የክትትል ተግባርን ይተገብራሉ፡፡ በዚህ ፖሊስና ሌሎች ተቋማት ህዝብን የሚሰልሉበት ስርዓት ውስጥ ገዥ የሆነው የፖለቲካ ስርዓት የሚያስተዳድረው ጠርናፊ ስርዓትም ‹‹የፖሊስ መንግስት›› ይባላል፡፡

የፖሊስ መንግስት የፖሊስን የመከታተል ተግባር በሞዴልነት በስፋት በህዝብ ላይ ለሚተገብር ስርዓት የተሰጠ መጠሪያ ነው፡፡ የፖለስ መንግስት ከሚገባው በላይ፣ ከህግ ይልቅ ወታደራዊና የደህንነት አቅሙን ተጠቅሞ የህዝብን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ የመቆጣጠር የፖለቲካ ስርዓት መግለጫ ነው፡፡ ይህ አይነት ስርዓት ውስጥ ህግ የይስሙላህና ማህበረሰቡን መግዢያ መሳሪያ እንጅ ሰነድ ላይ በተቀመጠው መልኩ አይጠቀምበትም፡፡ በማህበረሰቡ ህይወት ላይ ቁጥጥር የሚደረገው በኃይልና በግትርነት ነው፡፡ የፖሊስ መንግስት የግለሰቦችን ነጻነት ለብሄራዊ ደህንነት ሲል መገደብ የተለመደ ነው፡፡ የወጡ ህጎችና አዋጆችን የህዝብን ነጻነትና መብት ይጨፈልቃል፡፡ የእነዚህ መንግስታት መሰረታዊ ባህሪ በአብዛኛው የሚቀዳው ከግራ ዘመም፣ ህዝባዊ መሰረት ከሌለውና ከግለሰባዊና የፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት ባህሪ ነው፡፡

በአንጻራዊነት ይለያይ እንጅ በየትኛውም አገር ሌባ፣ ቀማኛና ገዳይ ይኖራል፡፡ የፖሊስ ተግባር ህዝብን ከእነዚህ ህገ ወጦች መከላከልና ድርጊቶቹ ሲፈጸሙ ለፍትህ ማቅረብ ቢሆንም የመንግስት መዋቅርና ተቋማት ሚና ፖሊሳዊ ‹‹ሞዴል›› በያዘበት ስርዓት ‹‹መንግስት›› ከሌባና ቀማኞች ይልቅ የሚያሳድደው፣ ራሱ ከሳሽና ፈራጅ በሆነበት ተቋም የሚወስነው በተቃናቃኞቹና ከእነሱ ጎን ይቆማል ባለው አካል (ህዝብም) ላይ ነው፡፡ የፖሊስ መንግስትም ለቁጥጥሩ እንደ መነሻ የሚወስዳቸው እነዚህን ‹‹ህገ-ወጦችና›› በእነዚህም ስም ህጋዊ ዜጎችን ህገ ወጥ አስመስሎ ነው፡፡ ይሁንና በእነዚህ ስም የሚሰለሉት፣ መንግስት በፖሊስና መከላከያ እንዲሁም ደህንነቱ የሚያስፈራራቸው ዜጎች ከህገ ወጦቹ ይልቅ መንግስትን ይፈራሉ፡፡ ህገ-ወጦቹ ከሚያደርጉት በላይ በመንግስት ይሰቃያሉ፡፡ በመንግስት ይመዘበራሉ፡፡ ይሸበራሉ፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት ቴክኖሎጅ መልካም አጋጣሚ ቢፈጥርም በሌላ በኩል ከእያንዳንዱ ግለሰብና ድርጅት በተሻለ ቴክኖሎኖጅኝ የመግዛትና የመጠቀም፣ እንዲሁም እያንዳንዱን እንቅስቃሴ የመጠቀም አቅም ባለው መንግስት መቆጣጠሪያ መሳሪያ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ በተለይ ማህበራዊ ሚደያና ሌሎቹን በመቆጣጠር ዜጎችን መሰለል የተለመደ ሆኗል፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ አገሪቱ በማትችለው ወጭ ኢንተርኔትን ከመቆጣጠርም አልፎ በማገድ ከሚከሰሱት በጣት የሚቆጠሩ የፖሊስ መንግስታት መካከል ቀዳሚው ለመሆን በቅቷል፡፡

ራሱን ህዝብን በመቆጣጠር ሚና ላይ ባሰለፈ መንግስት ውስጥ ስልጣንን ለማስጠበቅ ሲባል መርህ፣ ህግ የሚባለው ከይስሙላህ ያለፈ በተግባር አይሰራም፡፡ ከዚህ ይልቅ ለስርዓቱ ቅርበት ያላቸው አካላት ከህግ በላይ ይከበራሉ፡፡ ራሳቸው ህግን ጥሰው ህዝብን ይሰልላሉ፡፡ ይቆጣጠራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የጌታና የሎሌ ግንኙነት እንጅ የተቋማትና የህግ ሚና ይጠፋል፡፡ በዚህም መሰረት ስራውን በአግባቡ የሚያከናውን ተቋምና አካል ይጠፋል፡፡ ስለሆነም ፖሊስ፣ ደህንነትና መከላከያ በህገ መንስቱ ለየስሙላህ ከሰፈረለት አገርና ህዝብን የመጠበቅ ሚና ይልቅ ስርዓቱን በመጠበቅ ላይ ጊዜና ገንዘብ ያባክናል፡፡ ስርዓቱ በሚፈልገው መንገድ ፖሊስና የመከላከያን፣ የመከላከያ የደህንነትን፣ ፖሊስ የደህንነትን ስራ ሊያከናውን ይችላል፡፡ በዚህም መሰረት ተለይቶ የተሰጠ፣ በህግ የተከለለ፣ ግዴታና መብት ያለው፣ ቢያጠፋ የሚያስከስስ ሚና ሊኖራቸው አይችልም፡፡ የተደበላለቀ ነው፡፡

ልዩ ሀይልና ታማኝ አካላትን በመጠቀም ህዝብን ይገዛል፡፡ በፖሊስ መንግስት ስርዓት በአካል ከሚታየው በላይ ስነ ልቦናዊ ጫና ህዝብን ያስሸብራል፡፡ በአገራችን አንድ ለአምስት ዋነኛው ህዝብን ጸጥ ረጭ አድርጎ የመግዢያ መንገድ ነው፡፡ ህዝብ መንግስት በየ ጓዳና ስርቻው፣ በየ ጎረቤቱ ሹክሹክታና ሀሜትን ሁሉ የሚሰማ ያህል አድርጎ እንዲፈራው፣ ከጌታውና ከእርኩስ መንፈስም ባልተናነሰ ከጎኑ የማይጠፋና የማይርቅ አድርጎ እንዲፈራው አሊያም እንዲያከብረው ይፈልጋል፡፡ በተለይ በኤሌክትሪኒክስ ሚዲያው፣ በስልክ ጠለፋና በመሳሰሉት እነዚህ ነገሮች በስፋት ይስተዋላሉ፡፡ ህዝብ ስልኩን ዘግቶም ቢሆን የሚጠለፍበት እስኪመስለው ወይንም እንደሚጠለፍበት የሚታመንበት ዘመን ላይ ተደርሷል፡፡ በእርግጥ በበርካታ አገራት መንግስት ዜጎቹን ለብሄራዊ ደህንነት ሲል መሰለሉ የተለመደ ነው፡፡ ሆኖም በተለይ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት እነዚህ ዜጎች የህግና የተቋማት ከለላ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አምባገነን ስርዓት በነገሰባቸው አገራት ግን ዜጎች የሚቆምላቸው አካል ስለማያገኙ በስርዓቱ ቁጥጥር ስር ከመገዛት ውጭ አማራጭ እንደሌላቸው አድርገው እንዲያስቡ ይገደዳሉ፡፡

እንደ ኢትዮጵያ በአምባገነን ስርዓት ስር በሚገኙ አገራት መከላከያ፣ ፖሊስና ደህንነት የስርዓቱ ታማኝ አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን ስርዓቱን እስካልጎዳ ድረስ ብዙም ጫና ሲደርስበት አይስተዋልም፡፡ ከዚህ ይልቅ ከስርዓቱ ቀጥሎ ለራሱ ጥቅምና በራሱ አመለካከት ህዝብን ሲበድል ማየት የተለመደ ነው፡፡ ከስርዓቱ ቀጥሎ ለራሱ ዜጎችን ያንገላታል፡፡ ይህ ከስርዓቱ የወሰደው ልምድና ትምህርት ነው፡፡ በመሆኑም ስርዓቱ ለራሱ ስልጣን በቀጥታ ከፈቀደው ባሻገር ፖሊስ፣ መከላከያና ደህንነት ከስርዓቱ ባገኘው ይሁንታም ይሁን ተቋማትና ህግ በአግባቡ የማይሰሩ በመሆናቸው እንዳሻው ህዝብን ለራሱ ጥቅም ይቆጣጠራል፡፡ ድርጊትም ይወስዳል፡፡ በዚህ ረገድ ደህንነት ለስርዓቱ ሳይሆን እንዳሻቸው በህዝብ ላይ የሚወስዱት ማወከብና እርምጃ የሚጠቀስ ነው፡፡ ፖሊስና መከላከያም ቢሆን ፖሊስ መንግስት ውስጥ ያሉ ሌላ የፖሊስ መንግስት ይመሰርታሉ፡፡ ይህ ስርዓት በተንሰራፋበት አገር መልካም ነገር የሚሰሩ ስለማይበረታቱ የሚኖሩበት አጋጣሚ ጠባብ ነው፡፡ ቢኖሩ እንኳ ፍርሃት ውስጥ የሚገኘው ህዝብ እነዚህን ሰዎች እውቅና የሚሰጥበት አጋጣሚን አያገኝም፡፡

ፖሊስ፣ መከላከያና ደህንነቱን ተጠቅሞ ደህንነቱን ይጠበቅለታል የተባለው ህዝብ ደህንነቱን የሚያጣው፣ ሽብር ውስጥ የሚገባው፣ አገሩ ውስጥ ሆኖም ባይተዋር የሚሆነው በእነዚህ አካላት ነው፡፡ ህገ መንግስቱን ለማስከበር እንደቆሙ የሚነገርላቸው እነዚህ አካላት የህዝብን ሰብአዊና ዴሞክራሲዊ መብት እንዳሻቸው እየደፈጠጡ ነው፡፡ መንግስታት ሰላማዊ ሰልፍና ሌሎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች ፈቅዶ የሚደፈጥጠው በእነዚሁ ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ይጠብቃሉ የተባሉ አካላትና ተቋማት አማካኝነት ነው፡፡ ከአገራዊ ፖሊስ፣ ከአገራዊ መከላከያና ደህንነት ይልቅ ጠባብ የፖለቲካ ማንነት አሊያም የገንዘብ ጥቅም ወይንም የስራ ዋስትናን መሰረት ያደረጉ መግዢያ መሳሪያ ሆነዋል፡፡ ከመከላከያ፣ ከፖሊስም ከሚባሉት ይልቅ ስለ ስራውና ሙያው የማያውቁት አካላት አዛዥ ናዛዦች ናቸው፡፡ ፖሊስ፣ መከላከያና ደህንነቶች የገዥው ፓርቲ አባላትና አንድ አካል ተደርገው ስለሚቆጠሩ ህዝብ በእነዚህ አካላትና ተቋማቱ ላይ እምነቱን አጥቷል፡፡ በዚህ ስርዓት ስለ መጻፍ፣ መናገር፣ ዴሞክራሲየዊና ሰብአዊ መብቶች ሰነድ ላይ ሰፍረው አይከበሩም፡፡ ፖሊስ፣ መከላከያና ደህንነት የስርዓቱን ገመና ያጋልጣሉ፣ ህዝብን ያነቃሉ ተብለው የሚፈራውን የሚዲያ ተሳታፊዎች በ‹‹ህገ ወጥነት›› በማሳደድ ተግባር ላይ ከተሰማሩ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ከ1997 በኋላ ደግሞ በአገር ክህደትና ሽብርተኝነት የሚከሰሱት ጋዜጠኞች ሆነዋል፡፡

ፖሊስና መከላከያ እንዲሁም ደህንነት የህዝብንና የአገርን ደህንነት ይጠብቃል እየተባለ ነገር ግን የሚፈራውና የሚጠላው የስርዓቱ አንድ አካልና መሳሪያ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ እነዚህ አካላት ላይ ያለው ጥርጣሬ ህዝብ የግዱን መገዛት እንዳለበት፣ ከዚህ ውጭ በህጋዊ ሰነዶች የተቀመጡትን መብቶቹን ቢሰራባቸው እንኳ ዋጋ እንደሚያስከፍሉት እንዲያምን ይሆናል፡፡ ጊዜያዊም ሆኑ ሌሎች አስገዥ አዋጆች የፖሊስ መንግስት የመጨረሻው ደረጃ ናቸው፡፡ በአገራችን ከ1997 ምርጫ ማግስት የወጣውን ጊዜያዊ አዋጅ ጨምሮ ፖለቲካ ፓርቲ፣ ሲቪክ ማህበራትን፣ ሚዲያውንና አጠቃላይ ህዝብን የሚያፍኑ ህጎች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ የፖሊስ መንግስት ከፖሊስ፣ ከመከላከያና ደህንነትም በላይ እራሱ የማያከብራቸውን ህጎች በማጥቂያነትና በማሰሪያነት የሚጠቀምባቸው ስለመሆኑ ህወሓት/ኢህአዴግ አዋጆችንም ሆነ ህገ መንግስቱን እሱ በሚፈልገው መንገድ ለማጥቂያም ሆነ ራሱን ህጋዊ ለማስመሰል መጠቀሙ አንድ ማሳያ ነው፡፡ እነዚህ አብዛኛዎቹ ህጎች ህገ-መንግስቱም ሆነ የሰው መሰረት ጋር የሚጋጩና የህዝብና የአገርን ጥቅም የሚጎዱ ሆነው ይታያሉ፡፡

ሁሉም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የሚከወኑባቸው ተቋማት ህዝብን አድራጅቶ መብቱን ለማስጠበቅ ከሚያገለግሉት ይልቅ ለመቆጣጠሪያነት ያገለግላል፡፡ ነጻ ገበያ ለፖሊስ መንግስት የሚታሰብ አይደለም፡፡ ስልጣን ላይ ያሉ አካላት ብቻ በኢኮኖሚው እንደፈለጉ ይጠቀሙበታል፡፡ ከእነሱ ጋር የሚቀራረቡትም እንዲሁ፡፡ ይሁንና አገሪቱ ነጻ ገበያ የምትጠቀም ከሆነ ሌሎች መንግስት የሚጠቀምባቸው ወሳኝ ተቋማት ወደ ግል ይዘዋወራሉ፤ ነጻ አስተሳሰብንና ዴሞክራሲን የሚያዳብሩት ሚዲያና ሌሎችም ተቋማት ይጠናከራሉ፡፡ በአጠቃላይ የገዥዎችን የመቆጣጠር አቅም የሚፈታተን ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በተለይ እነዚህ መንግስታት ህዝብ ከደህንነቱ ጀምሮ ስኳርና ዘይትን ከመንግስት እንዲጠብቅ ስለሚፈልጉ ኢኮኖሚውንም እንደ አንድ መቆጣጠሪያና መግዢያ መሳሪያ አደርገው ይጠቀሙበታል፡፡ ለዚህም ሲባል መንግስት በተደጋጋሚ ጣልቃ የሚገባበት ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ በደህንነት ስም ከዴሞክራሲ ይልቅ ከገዥዎች ኪስ የማያልፍ እድገት የሚያመጣ ልማት በልማትነት ይወሰድና ከገዥዎቹ በተቃራኒ ሀሳብ የሚያራምዱ አካላት ጸረ ልማትና ሰላም ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ በፖሊስ መንግስት አገዛዝ ህዝብን በመሳሪያ ከሚያስፈራራው ፖሊስ፣ መከላከያና ደህንነትም ባሻገር በእነዚህ ተቋማት የሚሸበረው ህዝብ እርስ በእርሱ ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ አንዱ ስልት ነው፡፡ በደረግ ጊዜ ከነበረው የአብዮት ጠባቂ በተመሳሳይ ደንብ አስከባሪ በሚል የተደራጁት ወጣቶች ዋነኛው ስራቸው ህዝብን ለማገለገል ነው ተብሎ አይታመንም፡፡ በተለይ በአገራችን በአሁኑ ወቅት ተግባር ላይ እየዋለ የሚገኘው ማሕበረሰብ አቀፍ (ኮሚኒቲ) ፖሊስ ቤተሰብ ድረስ በመድረስ የአገራችን የፖሊስ መንግስት አገዛዝ እስከ የት እንደደረሰ የሚያሳይ ነው፡፡

ከወራት በፊትም የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን "አገራዊ የማሕበረሰብ አቀፍ ፖሊሳዊ አገልግሎት ፖሊሲ" ረቂቅ አዘጋጅቶና ከባለ ድርሻ አካላት ተወያይቶ በአሁኑ ወቅት ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡ ሆኖም በረቂቅ አዋጁ ወቅት የተገኙት ተቃዋሚዎች ጨምሮ በርካቶች የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት እንደ ሌሎች አገራት ለስርዓቱ በአጋዥነት ሊያገለግል እንደሚችል ስጋታቸውን ገልጸዋል፡፡ በተለይ ረቂቁ ውይይት በተደረገበት ወቅት ለተወያዮቹ ዋናው ረቂቅ ሳይሆን የተጨመቀና በአሉታዊነት ሊታይ የማይችል ጽሁፍ መቅረቡ በዚህ የፖሊስ አገልግሎት አሉታዊነቱ ሊያመዘን እንደሚችል አስጠርጥሯል፡፡

ከተወያዮቹ መካከል መድረክን ወክሎ የተገኘው ወጣቱ ፖለቲከኛና ጸሃፊ አስራት አብርሃም ‹‹"የማሕበረሰብ አቀፍ ፖሊሳዊ አገልግሎት ፖሊሲ" አንድምታዎችና ስጋቶች›› በሚል መጣጥፉ የሚያስረዳው ይህንኑ ስጋቱን ነው፡፡ እንደ አስራት አብርሃ ለአብዛኛዎቹ ተወያዮች (ለተቃዋሚዎች?) የተሰጠው ፅሁፍ ከዋናው ፅሁፍ ተጨምቆ የወጣ እንጂ ዋናውን ፅሁፍ አልነበረም፡፡ ዋናውን ኮፒ የያዙ ሌሎች ሰዎች እንደነበሩ የሚገልጸው አስራት ወክሎት የሄደው መድረክ ከውይይቱ በፊት ረቂቁን እንዲደርሰው ጠይቆ ያልተሳካለት መሆኑና በውይይቱ ወቅት ራሱ ዋናው ረቂቅ ቢጠይቅም አወያዮቹ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው በመግለጽ ጥርጣሬውን ያጠናክረዋል፡፡

በመጀመሪያው ጥያቄው ለአዘጋጆቹ "ለሁሉም አባዝቶ መስጠቱ ከፍተኛ የሆነ ወጭ ስለሚጠይቅ ነው" የሚል መልስ የተሰጠው አስራት ቆይቶ ሲጠይቅ ደግሞ "ይህ በረቂቅ ደረጃ ላይ ያለ ሰነድ ስለሆነ፣ ምን ብለን እንሰጣለን?" የሚሉ የማህበረሰብ ፖሊስ አገልግሎት ከአተገባበሩም በፊት በረቂቅ ህጉም ላይ አሉታዊ ነገሮች እንዳሉበት የሚያስጠረጥር መልስ ማግኘቱን በጽሁፉ አስፍሯል፡፡ ጥርጣሬ ከሚያጭሩት መልሶች በኋላ ዋናውን ቅጅ ከሌሎች ተሰብሳቢዎች አግኝቼ አይቸዋለሁ የሚለው ወጣቱ ፖለቲከኛ ‹‹ለእኛ ተዘጋጅቶ የተሰጠን ቅጂ የዋናው ቅጂ ሀሳብ ፍሬ ነገሩን ብቻ የያዘና በአቀራረቡም ዘንድ ጭቅጭቅና ክርክር ሊያስነሱ የሚችሉ ነጥቦች ለዘብ ብለው እንዲቀርቡ መደረጋቸውን›› ይገልጻል፡፡ ይህም የሚያሳየው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ፖሊስ ከአተገባበሩ በፊት ህግ ላይም አጨቃጫቂ ጉዳዮች እንዳሉበት ነው፡፡

አስራት አብርሃ ለአብዛኛዎቹ ተስብሳቢዎች አልተሰጠም ከሚለው ዋናው ቅጅ የማህበረሰብ ፖሊስ አገልግሎት መንግስት ህዝብን ለማፈን ሊጠቀምበት እንደሆነ ያሳያል ይለናል፡፡ ለአብነት ያህልም ‹‹ህብረተሰቡን በሙሉ በ1ለ5 አወቃቀር በማደራጀት አወቃቀሩ ከፌደራል ፖሊስ ጀምሮ እስከ ቤተሰብ ድረስ የሚዘልቅ ጥብቅ የሆነ የእዝና የቁጥጥር ሰንሰለት በእያንዳንዱ ሰው ላይ ለመዘርጋት ያለመ መሆኑ ቀዳሚው ስጋት ነው፡፡ ይህን ተግባራዊ የመሆን ዕድል ካለው ህዝቡን በጠቅላላ ወደ ማህበረሰባዊ ፖሊስነት የሚቀይር 15 ሚሊዮን የሚደርሱ የኮሚዩኒቲ ፖሊስ 1ለ5 አደረጃጀቶች በአገሪቱ ውስጥ በማቋቋም አንድም ሰው ከዚህ አደረጃጀት ውጪ እንዳይሆን የተፈለገ ነው የሚመስለው፡፡ ስለ 1ለ5 አደረጃጀት በረቂቁ ውስጥ በመግቢያውና በዋናው ፅሁፍ ላይ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል፡፡››

ከዚህም በተጨማሪ "ህብረተሰቡን እስከ ቤተሰብ በማድረስ ከቤተሰብ አባላት መካከል አንድ የፖሊስ ተጠሪ በማስመረጥ፣ በየአከባቢው 1ለ5 አደረጃጀትን በመፍጠር፣ በተለያዩ የድለላ ሥራ የተሰማሩ፣ ጫማ የሚያፀዱ ወጣቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ የሀይማኖት መሪዎችን እና የቀን ሰራተኞችን በየአካባቢያቸው በማደራጀት የወንጀል መከላከል አጋር እንዲሆኑ ማድረግ" በሚል አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ለመጠርነፍ መታቀዱን ያስረዳል፡፡ ከዚህም ባሻገር "በመፍትሄ አተገባበሩም በፀጥታ ስራ እንደ አመቺነቱ በመሳተፍ በእውቀቱና በሀብቱ በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ እንዲሳተፉ ማድረግ በሚያስችል መልኩ እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በቀበሌ፣ በብሎክ / በጎጥ/ በመንደር ወዘተ በ1ለ5 ወይም እንደ አመቺነቱ በአቅራቢያ ጎረቤታሞች መደራጀት" በመላ አገሪቱ ተግባራዊ ለማድረግ መታቀዱን ያመለክታል፡፡ ለ‹‹እነዚህን 1ለ5 የማሕበረሰብ ፖሊሲያዊ አደረጃጀቶችን በበላይነት የሚቆጣጠር ደግሞ በየአካባቢው ከ9-11 ሰዎች ያቀፈ የፀጥታ አማካሪ ምክር ቤት ይኖራል፡፡›› ይለናል፡፡

ይህ እንግዲህ ቅቡልነት በማጣቱ ምክንያት የትኛውንም የህዝብ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚፈልግ ‹‹የፖሊስ መንግስት›› የመጨረሻው ምዕራፍ ነው፡፡ ቁሳቁስ ከሚዘርፉ፣ ነፍስ ከሚያጠፉና ከሌሎች ህገ ወጦች ይልቅ ስልጣኑን ሊያሳጡት እንደሚችሉ የሚያምናቸው ጥቃቅን እንቅስቃሴዎች ሁሉ ለመቆጣጠር ይጥራል፡፡ ከዋናዎቹ ህገ ወጦች ይልቅ በህጋዊ መንገድ መብታቸውን የሚጠይቁት ዜጎችን ህገወጦች አድርጎ ይከታተላል፡፡ አምነውበት፣ ባለማወቅም ይሁን በጊዜያዊ ጥቅም ከስሩ የሚገኙትንም ‹‹ህገወጥ›› እንዳይሆኑ ይጠረንፋል፡፡

# አምጽ . . . ሐገርህን . . .

ከ ገፅ 3 የዞረ

ግን በፍርሃት ተሸብቦ ለአገዛዙ እየተባበረ እንዳለ ላረጋግጥልህ እፈልጋለሁ፡፡

እስኪ ወደ ቀበሌ ስብሰባ ሂድና ተመልከት፡፡ ሐገሩ በፍርሃት ታጥሮ የማስመሰል ዓለም ውስጥ እኮ ነው ያለው፡፡ ታዲያ አንተ ሄደህ ዝምታውን ብትሰብረው የማይከተልህ ወገንህ የቱ ሊሆን ይችላል...አንተን ውሃ ጠምቶህ ከሆነ ሌሎችን እንደሚጠማቸው አስብ፡፡ እናም አንተ ስታምጽ አብሮህ የሚያምጽ እንዳለ እርግጠኛ ሁን፡፡ ደግሞ ግዴታህም ነው! በሐገር ደረጃ ፍትህና ነጻነት ከሌለ አንተ ብቻህን አመጽ ላይ እንዳልሆንክ እርግጠኛ ሁን፡፡ ለዚህ ነው አንተ ትችላለህ....ስለሆነም አሁንኑ መምራት ጀምር የምልህ! ህዝብ አፍኖ የያዘውን ሰቆቃ አንተ ደፍረህ አፈንዳው...ብቻህንም ልትሆን እንደማትችል እርግጠኛ ሁን፡፡

መሪዎች ደፋሮች ናቸው፡፡ ድፈር! አትፍራ...ቀኝና ግራ በስጋት የምትባንንበት ጊዜ ማብቃት አለበት፡፡ እሱን ማድረግ የምትችለው ደግሞ አንተ ነህ...እንደምትችል አሳያቸው፡፡ ሊግ፣ አደረጃጀት፣ ፎረም...ገለመሌ የሚባሉት ውስጥ ግባና ቦርቡረው፡፡ አማራጭህን አሳውቃቸው፡፡ የተሻለ ነገር እንዳለህ አሳያቸው፡፡ በእርግጠኝነት ቀፍዳጁን ስርዓት ትለውጠዋለህ፡፡ የዳር ተመልካች አትሁን፡፡ ሐገር ማስመለስ የሚቻለው በድፍረትና በአማራጭ ሀሳብና ድርጊት ነው፡፡ አንተ ደግሞ ይህ እንዳለህ አስታውስ፡፡

ደግሞ የራስህ አደረጃጀት መፍጠር ትችላለህ፡፡ ተደራጅ! ተደራጅ! ተደራጅ! ይህ ነው መሳሪያህ፡፡ ይህ ነው የማመጫ መሳሪያህ፡፡ ለዚህ ጨቋኝ ስርዓት እጅ አትስጥ፡፡ እነሱ የመግደያ መሳሪያው አላቸው፡፡ አንተ ግን የለውጥ መሳሪያ ነው ያለህ፡፡ በለውጥ ውስጥ ደግሞ የመግደያ መሳሪያው ራሱ ይለወጣል፡፡ አዎ በአንተ የአመጻ ለውጥ ውስጥ የሐሳብ እንጂ የመግደያ መሳሪያ አትጠቀምም፡፡ ከእነሱ እንደምትሻል የምታሳየው በሐሳብ እንጂ በጠብመንጃ አማራጭ እንዳልሆነ እንዲያውቁ የአንተ መነሳት ያስፈልጋል፡፡ ጊዜውም አሁን ነው፡፡ ሐገርህን አስመልስ፡፡ አምጽ...! ደግሞም አስታውስ....የአንተ ጊዜ ዛሬ ነው!

ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና የዘመነ አስተዳደር ይገባታል!

# ገዳይ ነጭ ሰው ጥርቡሽ የደፋ . . .

ከ ገፅ 8 የዞረ

ዕርፈት አለ? አርበኝነት ልበ ሙሉነት ነው! አርበኝነት የብሔራዊ ስሜት መግለጫ ነው! አርበኝነት የኢትዮጵያዊት ማን አህሎኝነት ነፀብራቅ ነው! አርበኝነት አልበገር ባይነት ነው! የድንገዜ ጦርነት አሁን በድል ተጠናቅቋል! ጀግናውን አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህን አሁን የምናገኘው በመንዝ ውስጥ ነው! በአካል የተጎሳቆሉ በመንፈስ የጠበደሉ ጀግኖችን እስከትሏል! ራኃብም ሆነ የውሃ ጥማት አልበገራቸውም! ከወራሪው ኃይል ጋር ተፋጥጠዋል! ብዙ አልቆዩም! ለቅድሚያ ተነሳሽነት አላቅማሙም! ወዲያው ጦርነት ተከፍቷል! ከስዓታት ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ አርበኞች ድል አድራጊነት ተበሰረ፡፡ ይህ በአምስቱ የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ዓመታት የኢትዮጵያ አርበኞች የሞት ሽረት ፍልሚያ የድል ቀጥታ ድምፅ ነው! ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት! ከመንዝ ምድር! መስከረም 1930 ዓ.ም!

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በተደጋጋሚ የአርበኞችን ክንድ ቢቀምስም ከመፍጨረጨር አልታቀበም! አሁንም ከመንዝ ለቅቆ አልሄደም! እንዲያውም ተዋጊ ኃይል ተጨምሮለት እንደገና ጦርነት ከፍተ! የኢትዮጵያ አርበኞች እንደተለመደው በውስን የሰው ኃይልና በነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ በልበ ሙሉነት ሊዋጉ ገቡ! እጅግ መራራ ጦርነት እንደነበረ በታሪክ ተመልክቷል! ሆኖም የኢትዮጵያ አርበኞች የሚበገሩ አልነበሩም፡፡ በራኃብና በውሃ ጥም ክፉኛ መጎዳታቸው ታውቋል፡፡ ጀግና በድል ራኃብና በነፃነት ጥማት ካልሆነ በስተቀር እንጀራ ወይም ውሃ አጥቶ መቼ ሞቶ ያውቃል? አይሞትም! ራኃብም ሆነ ጥማት የሚሰማው ህሊና ሲሞት አይደል? የጀግና ህሊና ዘወትር ንቁ ነው! ግፋ ወደ ፊት! የአባትህን ታሪክ አድስ! ይህ የጀግናው አርበኛ የደስታ ሸዋርካብህ የጦር ሜዳ የትዕዛዝ ቀጥታ ድምፅ ነው! አሁንም ጦርነቱ ተፋፍሟል! የኢትዮጵያን አርበኞች ከሕዳር 18 ቀን 1930 ዓ.ም አንስቶ ለአምስት ቀንና ሌሊት ባካሄዱት በዚሁ ጦርነት አንፀባራቂ ድል አስመዝግበዋል! በርካታ የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያዎችም ከመሰል ጥይቶች ጋር ተማርከዋል! ይህ ከፍ ባለ ቃና የሚደመጠው የቀደምት ኢትዮጵያውያን አርበኝነትና የድል ታሪክ ቀጥታ ድምፅ ነው!

ቆፍጣናው ጀግና ደስታ ሸዋርካብህ በመቀጠል ባካሄደው ጦርነት ታህሳስ 12 ቀን 1930 ዓ.ም ጀኔራል ማሉሊ የተባለው የፋሽስት መኮንን ሸሽቶ ደብረ ብርሃን እንዲገባ አድርጎታል! እንደገናም በአንኮበር ላይ ተዋግቷል! ውጤትም አስመዝግቧል! ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ለዕርቅ ደብዳቤ ተጻፈለት፡፡ አልተቀበለውም፡፡ እንደገናም ተጻፈለት፡፡ ዋጋም አልሰጠውም፡፡ ቆራጡ አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ ዙሪያውን በአምስት ባታሊዮን የፋሽስት ወራሪ ኃይል ተዋጊዎችና በጀኔራል ማሌቴ ጦር ከበባ ተደረገበት እየተታኮሰ በድል አድራጊነት ሰንጥቆ የወጣ ጀግና ነው! እንዲሁም ግንቦት 11 ቀን 1930 ዓ.ም ወደ ቡልጋ ይጓዝ የነበረውን የፋሽስት ወራሪ ኃይል ገጥሞ ድል ተቀዳጅቷል! በዚህ ብቻም አላበቃም! ግንቦት 12 ቀን 1930 ዓ.ም እንደገና በጉረቤላ፣ ሰኔ 22 ቀን 1930 ዓ.ም በመስጫ አራባ፣ ሰኔ 26 ቀን 1930 ዓ.ም በፍቅሬ ግንብ፣ ነሀሴ 15 ቀን 1930 ዓ.ም በቁምቢ፣ ነሀሴ 18 ቀን 1930 ዓ.ም በእመምህረት፣ ነሀሴ 28 ቀን 1930 ዓ.ም ወሳኝ ጦርነቶችን እንዳካሄደ በአርበኝነት ዝርዝር ታሪኩ ላይ ተመልክቷል፡፡

ጀግናው አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ በመቀጠልም ከመስከረም 24 እስከ 26 ቀን 1931 ዓ.ም በሐራምባ ቆቦ፣ ጥቅምት 25 ቀን 1931 በተጉለትና ናስ እንዲሁም ከህዳር 20 እስከ 21 ቀን 1931 ዓ.ም በርካታ የወራሪ ኃይል ተዋጊዎችን ገድሏል! ጀግናው ደስታ ህዳር 21 ቀን 1931 ዓ.ም ክፉኛ ቆስሎ ከወደቀበት በቃሬዛ ተገልሏል፡፡ ሆኖም ለጥቂት ጊዜ ካገገመ በኋላ ጦርነቱን ቀጥሏል፡፡ በዚህም መሰረት ጌታ ገደል በተባለ ቦታ ተዋግቶ ድል አድርጓል፡፡ ጀግናው ደስታ ሸዋርካብህ የፈጸማቸው ጀብዱዎች በጣም ብዙ ናቸው፡፡ የዋለባቸው የጦር ሜዳዎችም ተዘርዝረው አያልቁም! የዚህ ጀግና ታሪክ አንድ መፅሐፍ ይወጣዋል፡፡ አምስቱንም ዓመታት ከውጊያ ያልተለየ ጀግና አርበኛ መሆኑ ታውቋል፡፡

ቆራጡ የጦር ሰው ደስታ ሸዋርካብህ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በተጎለትና ቡልጋ አውራጃ በአንኮበር ወረዳ ልዩ ስሙ ሐራምባ በተባለ መንደር በ1893 ዓ.ም ተወለደ፡፡ አማርኛ ተምሯል! ሰገሌ ዘምቷል! እንዲሁም ማይጨው ዘምቷል! ጀብዱ ፈፅሟል! በአራት ቦታ ቆስሎ ተመልሷል!

ጀግናው አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ ከድል በኋላ የአርበኝነት ሜዳይ ባለ አምስት ዘንባባ፣ የቅዱስ ጊወርጊስ የጀብዱ ሜዳይ ባለሁለት ዘንባባ፤ የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን ባለ አምበል፣ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የፈረሰኛ ደረጃ ኒሻን፤ የድል ኮከብ ሜጋይ፤ የዳግማዊ ምኒልክ የወርቅ ሚዳያ፤ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ የአንገት ኒሻን ከነፕላኩ የዳግማዊ ምኒልክ የአንገት ኒሻን ከነፕላኩ፣ የዳግማዊ ምኒልክ የአንገት ኒሻን ከነፕላኩና የኦሜድላ መታሰቢያ ሜዳይ ተሸልሟል፡፡ ጀግናው ደስታ ሸዋርካብህ ሐምሌ 26 ቀን 1972 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡ ጀግናው ደስታ ሲሞት ባህላዊና ወታደራዊ ማዕረጉ ደጅአዝማች እንደ ነበር ታውቋል፡፡

ክብር ለጀግናው አርበኛ ለደጅአዝማች ደስታ ሸዋርካብህ! ክብር በዱር በገደሉ ለወደቁ አርበኞች! ክብር ዛሬም ከዕለታዊ ጥቅምና ከጊዜያዊ ተድላ ርቀው ለእናት ሀገራችን ነፃነት በመታገል ላይ ለሚገኙ ጥቂት ቆራጦች! የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ዳግም ይከበራል! አንድነታችን ትንሳኤ ያገኛል! ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

# የሰላማዊ ትግል . . .

ከ ገፅ 9 የዞረ

ህዝብ ንግድ እንዳይነግድ አደረገ፡፡ በዚህን ጊዜ ንጉሱ ወዲያው ወደ ሐማሴን አውራጃ ገዢዎች እና ባላባቶች መልክተኛ ልኮ፥

"ቅቤ፣ ማር፣ እህል ይዞ ከሐማሴን ወደ ምጽዋ ለንግድ ማንም እንዳይሄድ፣ የሄደ ግን ብርቱ ቅጣት ያገኘዋል" ሲሉ ዐዋጅ ነገረ፡፡

በዚህ ዐዋጅ ቱርኮች ታላቅ ችግር ላይ ወደቁ፡፡ የአርኪቆ ገዥ ናይብ ሙሳም ወታደራዊ ዘመቻ አድርጎ ዐዋጁን በኃይል እንዳያስፈርስ ያቄ እያሱ ጦር ሰራዊት ቀደም ብሎ በአክሱም እና በሐማሴን መስፈሩን አስተውሏል፡፡ ምንም እንኳን በመድፉ ቢተማመንም ጦርነት በኢትዮጵያ ምድር ቢጀምር ኢትዮጵያውያን የሽምጥ በፈረስ ጋልበው በመደፉ መካከል በመግባት ውጊያውን ወደ ጨበጣ ውጊያ እንደሚቀይሩበት ያውቃል፡፡ ስለዚህ ናይብ ሙሳ በቀረጥ ምክንያት የዘረፈውን ሸቀጥ ይዞ ንጉሱ የነበረበት አክሱም ድረስ መጣ፡፡ የጨመረውን ቀረጥ እንደሚያነሳ ቃል ገብቶ ከንጉሱ ጋር እርቅ አደረገ፡፡ የዘረፈውን ሸቀጥ ለንጉሱ አስረከበ፡፡ ከዚህ በኋላ የሐማሴን ህዝብ ወደ ምጽዋ፣ የምጽዋ ህዝብም ወደ ሐማሴንም ወደ ትግራይም እየመጣ እንደቀድሞው እንዲነግድ ስምምነት አደረጉ፡፡ ከስምምነቱ በኋላ ናይብ ባሻ ወደ ስፍራው ንጉሱም ወደ ጎንደር ተመለሱ፡፡

እርግጥ ይህ በታላቁ እያሱ የተደረገው የሰላም ትግል በኢትዮጵያ የተደረገ የመጀመሪያ የሰላም ትግል ነው ከሚል ድምዳሜ አያደርሰንም፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ የሰላም ትግል መደረጉን ያረጋግጥልናል፡፡

(2) በ20ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ምሁራን ሰላማዊ ትግል

እነ ነጋድራስ ገብረ ህይወት ባይከዳኝ (1886-1919) እና የቀሩት በዚያን ዘመን በራሳቸው አነሳችነት ከሚሲዮናውያን እና ከጎብኚዎች ጋር እየተወዳጁ ውጭ አገር እየሄዱ ተምረው ወደ አገራቸው የተመለሱት ምሁራን የኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ ምሁራን መሆናቸውን ባህሩ ዘውዴ ያመለክታል፡፡

እነዚህ ምሁራን ውጭ አገር ተምረው ሲመለሱ ክብረ ነገስት (The Glory of Kings) የተባለውን መጽሐፍ የዳቦ ቅርጫት እያለ የሚጠራት አገራቸው የነበረችበት ድህነት እና ኋላቀርነት ደረጃ እጅግ ይጸጽታቸው ነበር፡፡ ኢትዮጵያን እንደ ጃፓን ማድረግ አለብን ይሉ ነበር፡፡ ጃፓንን እንደ ሞዴል የመረጡበት ምክንያት ጃፓንም እንደ ኢትዮጵያ በንጉሰ ነገስ የምትገዛ ደሃ እና ኋላቀር አገር ስለነበረች እና በፍጥነት የምዕራቡን ዓለም ስልጣኔ ወርሳ እድገት በማድረጓ ነበር፡፡ ይኽን ምኞታቸውን ተፈጻሚ ለማድረግ የሞከሩት በሰላማዊ መንገድ እንጂ በትጥቅ ትግል አልነበረም፡፡ አገሪቱ በዙፋናዊ ገዢዎች እጅ ስለነበረች የመረጡት ሰላማዊ መንገድ የወጣት ሉዑላንን እና መስፍኖችን አስተሳሰብ በመለወጥ አገሪቱን ወደ ስልጣኔ እና ብልጽግና እንዲወስዷት ማድረግ ነበር፡፡ በዚያን ዘመን ትኩረታቸው በልጅ እያሱ እና በራስ ተፈሪ ላይ ነበር፡፡ በራስ ተፈሪ ላይ የሰሩት የመለወጥ ስራ የፈለጉትን ያህል ለውጥ ባያመጣም በዘመናዊ (Secular) ትምህርት ላይ ለዘመናት ተዘግቶ የነበረውን በር በመጠኑም ቢሆን በመክፈት ረገድ ውጤት አምጥቷል፡፡

(3) ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ማለቂያ ወዲህ የምርጫ ፓርቲዎች ሰላማዊ ትግል

እንደሚታወቀው ለመደነስ ሁለት ሰው እንደሚያስፈልገው ሁሉ ለስልጣን የእርስ በርስ ጦርነት ለማድረግም በጦርነት ማድረግ የሚስማሙ ገዢ እና ተገዢ ፓርቲዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ዛሬ እንደምናየው ግን በኢትዮጵያችን ሰላማዊ ትግልን የሚያራምዱ በርካታ ተቃዋሚ የምርጫ ፓርቲዎች አሉን፡፡ ይህ የሚያሳየው ለዘመናት ኢትዮጵያን እጅና እግሯን ተብትቦ የኋሊት ሲጎትታት የነበረው የመገዳደል የመንግስት ሽግግር ባህላችንን ቢያንስ ቢያንስ 50 ከመቶ ያህል ወድቅ ማድረጋችንን ነው፡፡ የኋሊት ጎታቹን ጸረ-እድገትና ጸረ-አንድነት የርስ በርስ ጦርነት ለመላቀቅ እና የስልጣኔን መንገድ ለመጀመር ቢያንስ ቢያንስ ጀምረናል ማለት እንችላለን፡፡ እነዚህን የምርጫ ፓርቲዎች ስናስተውል ኢትዮጵያችን የሰላማዊ ትግል ፍልስፍና እና ባህልን በተቋም ደረጃ መደገፏን እናጤናለን፡፡ ይህ የምስራች የሚያሰኝ ነው፡፡ ብዙ ስራ ግን ይቀራል፡፡

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ትናንት አምባገነኑ ህውሃት/ ኢህአዴግ እንዳደረገው ከጫካ ጠበንጃ አንግቦ ዘው ብሎ የመንግስት ስልጣን ባለቤት መሆን አይቻልም፡፡ ያን ማድረግ ለኢትዮጵያችን የትናንት ታሪክ ሆኗል ብዬ አፌን መልቼ እናገራለሁ፡፡ በአገር ውስጥ ያሉት የምርጫ ፓርቲዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ህዝባዊ መከላከል (People's Resistance) ሊጠሩ ይችላሉ፡፡ ህዝቡም የራሱ ነፃ አውጭ የመሆን ባህል እየገነባ ነው፡፡

በተጨማሪ የሰላም ትግል መሪዎቹን እነ ጋንዲን፣ እነ ማርቲን ሉተር ኪንግን እና እነ ሮሳ ፓርክስን እንደ አርአያ የወሰዱ በርካታ የኢትዮጵያ ወጣቶች አገራቸውን በሰላማዊ ትግል ለመለወጥ በመታገል ተገቢውን መስዋትነት መክፈል ጀምረዋል፡፡ የአልበርት አነስታይን ተቋም ምርምር ስራዎችንም መተዋወቅ የጀመሩ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም፡፡ ይህ ሁል ተስፋ ይሰጠናል፡፡ ይሁን እንጂ የሰላማዊ ትግል እውቀት ይበልጥ በህዝባችን ዘንድ እንዲታወቅ ለማድረግ ብዙ መስራት አለብን፡፡ በተረፈ የተጫናትን አምባገነን ቡድን ለማስወገድ ኢትዮጵያ የሰላማዊ ትግል እውቀትና አቅም ትገነባለች እንጂ ፊቷን ወደ ኋላቀሩ እርስ በርስ ጦርነት አትመልስም፡፡

# ሰማያዊ በአርባ ምንጭ ህዝባዊ ስብሰባ ያካሂዳል

## •ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ ሁለተኛ ዙር የክፍለ ሀገር መዋቅሮቹን ይጎበኛል

አዲስ አበባ፡- ሰማያዊ ፓርቲ (ሰማያዊ) ቀጣይ እሁድ መጋቢት 7/2006 ዓ.ም በአርባ ምንጭ ከተማ ህዝባዊ ሰብሰባ እንደሚያካሂድ የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ብርሃኑ ተክለያሬድ ለነገረ ኢትዮጵያ ገለጹ፡፡

አቶ ብርሃኑ ሰማያዊ አርባ ምንጭ ላይ ከድሬዳዋ ቀጥሎ በሳምንታት ጊዜ ውስጥ ሁለተኛው የሆነውን ህዝባዊ ስብሰባ ለማድረግ ውሳኔ ማሳለፉን ተናግረዋል፡፡ በአካባቢ ካለው የበዛ አፈና የተነሳ ሰዎች አዳራሽ ለማከራየት ፈቃደኛ ያለመሆን አዝማሚያ መኖሩን ለመታዘብ እንደቻሉ የጠቀሱት ኃላፊው፣ ገዥው ፓርቲ በሚፈጥረው መሰናክል ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ሊኖሩ ቢችሉም በሰማያዊ ፓርቲ በኩል ስብሰባውን ለማካሄድ ዝግጅት መጠናቀቁን አስታውቀዋል፡፡

‹‹በእኛ እቅድ መሰረት በቀጣዩ እሁድ አርባ ምንጭ ላይ ህዝባዊ ስብሰባ አለን፡፡ ከአዳራሹ ውጭ ሌላው ጉዳይ ዝግጁ ነው፡፡ የአደራሹ ጉዳይ እንዳለቀ ከአካባቢው መዋቅር ጋር በመተባበር ስብሰባውን እናካሂዳለን፡፡››

ነገረ ኢትዮጵያ ባለፈው መርሃ ግብር ባልተካተቱት የኢትዮጵያ ክፍሎች መዋቅራቸውን ለማደራጀትና ለማጠናከር ሁለተኛውን ዙር መቼ ለማድረግ እንዳሰቡ ላነሳችላቸው ጥያቄ ቀጣዩ ዙር በሚቀጥሉት ሳምንታት ጀምሮ የሚካሄድ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡ ሁለተኛው ዙር ‹‹ስራ አስፈጻሚዎች የሚሳተፉበት በባሌ፣ ጅማ፣ በደሴ፣ ሮቤና የመሳሰሉትን አካባቢዎች አንድ ቡድን ጉዞ ያደርጋል፡፡ በአንጻሩ ቤንሻንጉልና አካባቢውን ደግሞ ሌላ ቡድን ይሸፍናል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች አካባቢዎች ማለትም ወደ ሀረርጌ መስመር፣ ድሬዳዋ፣ ጅጅጋ፣ ትግራይ መስመርን ጨምሮ ሌሎች ቦታዎችን ቀሪ ቡድኖች ጉዞ እንደሚያደርጉ እንጠብቃለን፡፡›› ብለዋል፡፡

ፓርቲው በየካቲት ወር ድሬዳዋ ላይ ህዝባዊ ስብሰባ ከማካሄዱም በተጨማሪ ባለፉት ሳምንታት 200 በሚደርሱ የሐገሪቱ ወረዳዎች ተንቀሳቅሶ መዋቅሩን ሲያጠናክር እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

# በግድቡ ሕይወታቸው የተገደበ ኢትዮጵያውያንን ለማትረፍ የሚደረገው እርብርብ



አለማየሁ ገብረማርያም (ፐ/ር)

ከሁለት ዓመታት በፊት "ግድቡና አደጋው፡፡ ግልገል ጊቤ ሦስት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በደቡብ ኢትዮጵያ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ከሚካሄደው ልማት ጋር በተያያዘ መልኩ ግድቡ ሊያስከትል በሚችለው እንደምታ ላይ ትኩረት በማድረግ ትንታኔ አቅርቤ ነበር፡፡ በዚያ ትንታኔዬ በዚህ የልማት ሰበብ እየተካሄደ ያለው እንቅስቃሴ በአካባቢው ስነ-ምህዳር ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽእኖ እና ግድቡ በአካባቢው ለዘመናት ሰፍረው በሚኖሩት ህዝቦች ህይወት ላይ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ ቀውስ ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብት ተሟጋች እና የአካባቢ ጥበቃ ድርጅቶች መንግስት ከዚህ ድርጊቱ እንዲታቀብ ድምጻቸውን ሲያሰሙ እኔም የሀሳቡ ተጋሪ በመሆን የነበረኝን ጥልቅ ስጋት በተደጋጋሚ አሰምቼ ነበር፡፡

ከዚህም በተጨማሪ "በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ያለውን ምቹ ያልሆነ ሁኔታ እና ተጋርጦ የሚታየውን የወደፊት አደጋ አስቀድመው ግንዛቤ በመውሰድ ታላላቆቹ ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ማሳወቃቸውን በማስመልከት የነበረኝን ልዩ አድናቆት እና ምስጋና አቅርቤ ነበር፡፡ "በይበልጥም ደግሞ የዓለም አቀፍ ወንዞች/International Rivers/ የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ሂዩማንራይት ስዎች/Human Rights Watch/ የኦክላንድ ተቋም/Oakland Institute/፣ የዓለም አቀፉ የኑሮ ዋስትና/Survival International/፣ እና የአፍሪካ ህብረቶች የስራ ቡድን/the Africa Resources Working Group በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት የአካባቢውን የተፈጥሮ ስነ-ምህዳር ለመጠበቅ እና ለዘመናት ሰፍረው የኖሩትን ህዝቦች ህይወት ለመታደግ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ላይ ለመተግበር የተያዘው መጠነ ሰፊ ዕቅድ ወደ ተግባር እንዳይሸጋገር ባደረጓቸው እና አሁንም በማከናወን ላይ ባሏቸው ጉልህ እና አንጸባራቂ ተግባራት ላይ የተሰማኝን አድናቆት እና ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በግልገል ጊቤ ሦስት የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ግድብ ግንባታ ምክንያት ህይወታቸው ለከፋ አደጋ ተጋልጦ የሚገኙትን ኢትዮጵያውያን ህይወት ለመታደግ በሚደረገው የህይወት ማዳን እርብርብ ለዓመታት በመጀመሪያው ረድፍ ላይ በጽናት ተሰልፈው የሚገኙ ናቸው፡፡

የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የህዝቡን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ እና የቅስቀሳ ዘመቻዎችን በማካሄድ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ላይ ሊከሰት በሚችለው የከፋ የአካባቢ ስነ-ምህዳር አደጋ ላይ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የጠራ አቋም እንዲይዝ በማድረግ እረገድ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ ባለፉት ዓመታት በጥንቃቄ የተዘጋጁ ዘገባዎችን፣ የጥናት ውጤቶችን እና ዝርዝር የፖሊሲ ትንተናዎችን እንዲሁም ሌሎች ሳይንሳዊ እና አሀዛዊ ዘገባዎችን በማዘጋጀት በኢትዮጵያ በስልጣን ላይ ያለው ገዥው አካል በሚተገብራቸው "የልማት መርሀ ግብሮች" ሰበብ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ግራ እና ቀኝ ለዘመናት ሰፍሮ በሚኖረው ህዝብ የዕለት ከዕለት ኑሮ እና አጠቃላይ ህልውና ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ውጤት በሰነድ አስደግፈው አቅርበዋል፡፡ እነዚህ ዓለም አቀፍ የአካባቢ ስነ-ምህዳር ጥበቃ እና የመብት ተሟጋች ድርጅቶች በጊቤ ሦስት የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ግድብ ግንባታ አማካይነት በወንዙ ሸለቆ የሚገኙትን የተለያዩ ጎሳዎች መሬት በማይመጥን የኪራይ ተመን ሰበብ ገዥው አካል በመንጠቅ ለወጭ ገበያ ምርትነት የሚውሉ የስኳር እና ሩዝ ልማቶች ዘርፍ ተግባራዊ በማድረግ በሸለቆው ግራ እና ቀኝ ሰፍሮ ለዘመናት ሕይወቱን ሲመራ የኖረውን ህዝብ በግዳጅ "የመንደር ሰፈራ" ("villagization") በሚል ከቀየው ለማፈናቀል እያደረገ ባለው ጭካኔ የተሞላበት አካሄድ ላይ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የጋራ ግንዛቤ እንዲጨብጥ እና የኗሪውን ህዝብ ተጠቃሚነት አሽቀንጥሮ የጣለው የስመ ልማት ከንቱ ሙከራ ተግባራዊ እንዳይሆን ለማስቆም እና ተጽዕኖ መፍጠር እንዲችል በመጋፈጣቸው ነው፡፡

እ.ኤ.አበ2012 ባቀረብኩት ትችቴ የዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና የአካባቢ ስነ-ምህዳር ጥበቃ ድርጅቶች እንዲሁም ቡድኖች በኦሞ ወንዝ ሸለቆ የልማት መርሁ ግብር ሰበብ ህልውናቸው ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጦ የሚገኙትን ኢትዮጵያውያን ህይወት ለመታደግ ከልማት ሰለባው ህዝቦች ጎን በመሰለፍ ድርጊቱን በማውገዝ እና ለመቀልበስ እንዲቻል የሞት ሽረት ትግል እያደረጉ ባሉበት ወቅት እኛ ኢትዮጵያውያን በተለይም ደግሞ የዲያስፖራው ማህበረሰብ አባላት እጃችንን አጣጥፈን ከዳር የመቆማችን እውነታ ለምን እንደሆነ በመጠየቅ ለዚህ አንገብጋቢ አደጋ ልዩ ትኩረት ባለመስጠቱ ጉዳይ ላይ በማብሰልሰል የተሰማኝን ቅሬታ ለወገኖች በይፋ ገልጬ ነበር፡፡ እነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ተቋማት እና ቡድኖች ለእኛ ብለው እንደዚህ ያለ ከባድ እና ቀጣይነት ያለው ስራ እያከናወኑ እያሉ እኛ ግን በጸጥታ እየተመለከትን ነው፡፡ በዚያን ጊዜ "ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት እና ከአካባቢ ስነ-ምህዳር ጥበቃ ድርጅቶች ጋር በመቀላቀል ለአካባቢያችን ለመሚገት እራሳችን ንቁ ተሳታፊ በመሆን እገዛ እናድርግ በማለት ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሁሉ የተማጽዕኖ ጥያቄ አቅርቤ ነበር፡፡" እንዲሁም "በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገው እና የተለያዩ ብዝሀ ህይወት ዝርያዎችን አካትቶ የያዘው የኢትዮጵያ ሀብት አሁን ላለው እና ለወደፊቱ ትውልድ ጠቀሜታ እንዲውል ክብካቤ እና ጥበቃ እንዲደረግለት የእራሳችንን የአካባቢ ጥበቃ ሲቪል ድርጅት እኛው ኢትዮጵያውያን በተለይም የዲያስፖራው ማህበረሰብ እናቋቁም" የሚል የተማጽዕኖ ጥሪ አቅርቤ ነበር፡፡ የሁኔታውን አሳሳቢነት በመገመትም እንዲህ የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥቼ ነበር፣ "ይህንን ማድረግ ካልቻልን በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ግራ ቀኝ በሚኖሩ ወገኖቻችን ላይ ግድቡ እያደረሰ ያለው አደጋ ዓይነት እጣ ፈንታ ውስጥ እራሳችንን ማግኘት እንደምንገደድ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡"

ያንን ትችት ጽፌ ካቀረብኩ ከሁለት ዓመታት በኋላም ቢሆን እስከ አሁን ድረስ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የአካባቢ ስነ-ምህዳር ጥበቃ ድርጅቶች ለእኛ ብለው ያንን ሁሉ እልህ አስጨራሽ ትግል እና ጥረት እንዲሁም የእኛን ወገኖች ህልውና ለመታደግ እርብርብ እያደረጉ ባሉበት ወቅት እኛ ከዳር ቆመን እየተመለከትን የመገኘታችንን ሁኔታ ሳስበው ለመቀበል በጣም ይቆጠቁጠኛል (በግልጽ ለመናገር ሀፍረት ይሰማኛል፡፡) እነዚህ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ተመሳሳይ ጥያቄዎች ምንም ምላሽ ባይኖራቸውም ደግሜ ደጋግሜ እንዳነሳቸው እገደዳለሁ፡፡ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የአካባቢ ስነ-ምህዳር ጥበቃ ድርጅቶች በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ላይ እየተካሄደ ላለው የከፋ አደጋ የሚያመጣ መርሀ ግበር መቀልበስ ለእኛ ሲሉ ሁሉንም እልህ አስጨራሽ ስራዎች እንዲሰሩ መጠበቅ በእውነቱ ፍትሀዊ ነውን? እነዚህ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ለወጎኖቻችን እና ለሀገራችን ሲሉ ይህንን የመሰለ ጥንቃቄና እናክብካቤ ሲያሳዩ እኛ የጉዳዩ ባለቤቶች ምንም ዓይነት ትኩረት ያልሰጠነው ለምን ይሆን? ለወገኖቻችን ህልውና ሲሉ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ከሚያሰሙት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የማንቀላቀል እና ድጋፍ የማናደርግላቸው ስለምን ይሆን? ጨቋኙ ገዥ አካል የጭቃ ጅራፉን እያጮኸ በእነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ላይ ቅጥፈት የተሞላበት እና አሳፋሪ መግለጫ እየሰጠ መልካም ስራቸውን እና ስማቸውን ሲያጠለሽ ለምንድን ነው ወደ እነዚህ ድርጅቶች በመጠጋት የማናግዛቸው እና የማንከላከልላቸው? ተመሳሳይ የአካባቢ ስነ-ምህዳር ጥበቃ ወንጀሎች እና የሰዎችን ሰብአዊ መብቶች የመደፍጠጥ ወንጀሎች በስመ "ልማት" ሰበብ በሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች ቢፈጸሙ ኖሮ በእውነት ግድ የለሾች እና በዝምታ የምንመለከተው ይሆን ነበርን? በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ግራ እና ቀኝ የሚኖሩ ወገኖቻችን የተገለሉ አናሳ ጎሳዎች በመሆናቸው ብቻ ለእነርሱ መብቶች መደፍጠጥ ግድ የለሾች መሆን ይኖርብናልን? በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ግራ እና ቀኝ የሚኖሩ ወገኖቻችን እንደ ሌሎቻችን ሁሉ "ዘመናዊነትን" የተላበሱ ባለመምሰላቸው በእነርሱ አፍረንባቸው ወይም ደግሞ በቅርቡ ያረፉት አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት የእነዚህ ህዝቦች አኗኗር "ኋላቀር ስልጣኔ" ነው በማለት በግልጽ እንደፈረጇቸው ቆጥረነው ሊሆን ይችል ይሆን? በምን ዓይነት ሁኔታ ነው እረፍት በሌላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከፍተኛ ተጋድሎ አማካይነት በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ግራ እና ቀኝ ለሚኖረው ህዝብ የተገኘ የአካባቢ ክብካቤ እና ጥበቃ ቅርስ ነው እናም ኑ ተረከቡን ብለን የወደፊቱን ትውልዶች ለማሳመን የምንሞክረው? ውድ አንባቢዎች በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ በአንክሮ እንድታስቡ እጠይቃለሁ፡፡

እኛን እየረዱን ያሉትን ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ቢያንስ በገንዘብ ልናግዛቸው የሚገባ መሆኑ ፍትሀዊ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ግራ እና ቀኝ ለሚኖሩት ወገኖቻችን ሰብአዊ መብት ጥበቃ ይህን ያህል ተጋድሎ እያደረጉ ባለበት ሁኔታ እኛ ድጋፋችንን በተጨባጭ ሁኔታ ለወገኖቻችን የማናሳይበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ ከእነርሱ ጋር በጋራ መቆም ይገባናል እናም ከዳር ቆመን የእነርሱ ተመልካች መሆን አይኖርብንም፡፡

## የግልገል ጊቤ ሦስት ግድብ በአካባቢው ህዝቦች ላይ የሚያስከትለው ግልጽ እና ወቅታዊ አደጋ

የጊቤ ሦስት ግድብ ግንባታ በአሁኑ ወቅት በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ግራ እና ቀኝ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ማለትም በቦዲ፣ ካሮ፣ ሙጉጂ፣ ሙርሲ፣ ኒያንጋቶም እና ዳሰነች ከብዙዎች ጥቂቶቹ ሲሆኑ ለሺህ ዓመታት" ባህረ ሸሽ ግብርና" እየተባለ የሚጠራውን የግብርና ስራ በመስራት ህይወታቸውን ሲመሩ በኖሩት ላይ ግልጽና ወቅታዊ አደጋ አንዣቦ ይገኛል፡፡ የዝናብ ወራት ከተጠናቀቁ በኋላ ውኃው ሲሸሽ በወንዙ ዳርቻዎች አካባቢ ተሸፍኖ የነበረው መሬት ለም የሆነ ደለል በርካታ የአዝዕርት ዓይነቶችን ማለትም ማሽላ፣ በቆሎ እና ባቄላ ለማምረት ያስችላል፡፡ የእነዚህ ኢትዮጵያውያን ህልውና የተመሰረተው በየጊዜው በሚለዋወጡት የጎርፍ ወቅቶች አማካይነት ነው፡፡ የጊቤ ሦስት ግድብ የወንዙ የላይኛው ክፍል ወደ ውጭ አገር ለሚላክ የኤሌክትሪክ ምርት ማመንጫነት ሲባል በሚገደብበት ጊዜ ወንዙ በሸለቆው ውስጥ የሚያደርገውን የተፈጥሮ

ወደ ገፅ 15 ይዞራል

# ገዳይ ነጭ ሰው ጥርቡሽ የደፋ፣ በሽንጡ ነድሎ ፈርስ የሚያስተፋ።

## ከጀግኖች የፋከራ ስነ - ቃል የተወሰደ



ታዴዎስ ታንቱ

የመ-ሣ-ቁጥር 43414

አሁን አንኮበር ውስጥ በተለይ ጉረቤላ በተባለ መንደር ከቆራጥ የኢትዮጵያ አርበኞች ጋር ሰልፋችንን አሳምረናል! ይህ የታሪክ ድምፅ ነው! ሰኔ 1 ቀን 1928 ዓ.ም! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የኢትዮጵያ አርበኞችን በንቀት ዓይን ይመለከታቸዋል። ወራሪው ኃይል ስሌቱ ልክ እናዳልነበር አሁን ምናልባት ሊገባው ይችላል። የኢትዮጵያ ጀግና ሞልቷታል። ከጊዜያዊ ሽንፈት በኋላ ወርቃማ ድል ይመዘገባል። ጦርነቱ ተቀጣጥሏል! የአርበኝነት ፍልሚያ ተለኩሷል! መስዋትነትን ማን ይፈራል? የሀገር ነፃነት በጀግኖች ደም ይከበራል! ድም! ድም! ድም! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ይህ የኢትዮጵያ አርበኞች የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ ተኩስ ቀጥታ ድምፅ ነው! ቆራጡ አርበኛ ደስታ ሸዋ ርካብህ በግንባር ቀደም ተዋጊነት ይስተዋላል። ተከታዮቹ ደግሞ በአርያነቱ ኮርተዋል! አንኮበር የጎበዛዝት ምድር! የደም መሬት! የቆራጦች ርስት!

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አሁን አቅሙን በበለጠ አጠናክሯል። በድል ሕልም ተስፋ ሰንቋል! የኢትዮጵያ አርበኞችም ለወሳኙ ፍልሚያ ቆርጠዋል! መፍትሔው ጦርነቱ ነው! ጀግና ይዋጋል! ፈሪ ይሸሻል! ይህ የታሪክ ቀጥታ ድምፅ ነው! አሁንም በአንኮበር ውስጥ መሆናችን ይመዝገብልን! ሰኔ 2 ቀን 1928 ዓ.ም! ሁለቱም ወገኖች አድፍጠው ውለዋል! ሰኔ 3 ቀን 1928 ዓ.ም ግን እንደገና ጦርነቱ ተቀሰቀሰ! የተፋፋመ ጦርነት ሆነ! እሳት ዘነበ! ትንታግ ተቅመዘመዘ! የአንኮበር መሬት በደም ተለወሰ! የኢትዮጵያ ጀግና በገዛ ሀገሩ መራሱ መሬት ማንን ሊፈራ ይችላል? አንበሳ ዝንጀሮን መቼ ፈርቶ ያውቃል? ጦርነቱ ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ይህ የታሪክ በቀጥታ ድምፅ ነው! ሰኔ 2 ቀን 1928 ዓ.ም! ሞት ያማረው ባንዳ እንደ ጉንዳን ይርመሰመሳል! ሀገሩን ክዶ ለባዕድ አድሯል! በአጭር ጊዜ ምሱን ያገኛል! እንደ ወይራ ፍልጥ ይማገዳል! እንደ ብሳና ቅጠል ይነድዳል!

የኢትዮጵያ አርበኛ ለሀገር ህልውና ትግል የጠየቀውን መስዋትዕነት ሁሉ ይከፍላል! ኢትዮጵያውያን ለቅኝ ተገዥነት የተቀረፀ ስነ ልቦና ኑሮን አያውቅም! ሊኖረንም አይችልም! አሁንም በታሪክ ላይ አንኮበር ውስጥ መሆናችን ይመዝገብልን! ጀግናው አርበኛ ደስታ ሸዋ ርካብህ ከመካከላችን ይጎማለላል! ጦርነቱ ከድል ወዲህ እንደማይቆም ታውቋል! ለዕብሪተኞች ተገቢውን ዋጋ መክፈል የኢትዮጵያውያን ዘመን የማይሽረው ባህል መሆኑን አድዋ ትመስክር! ትናንትም ነበርን! ዛሬም አለን! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች የአቋም ቀጥታ ድምፅ ነው! ከአንኮበር የውጊያ መስክ! 1928 ዓ.ም!

ወራሪው ኃይል አሁን በራሱ ምክንያት ወደ ፊት ለመግፋት ከመፍጨርጨር የታቀበ ይመስላል። ጦርነቱ ለጥቂት ቀናት ጋብ ብሏል! ቆራጦቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ደግሞ በውስን የቀናት ክፍተት የጦር መሳሪያ በሚስጢር ሲያስገቡ ታይተዋል! ጦርነቱ ግን ብዙ ጊዜ ሳይቆይ እንደገና ተጋጋለ! በአንኮበር መሬት ላይ እንደገና እሳት ነደደ! የኢትዮጵያ አርበኞች የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያዎቻቸውን እሳት ያስተፉ ገቡ! ፍልሚያው ቀጠለ! መስዋትነት ድልን ይወልዳል! በድል ሉዓላዊነት ይረጋገጣል! በሉዓላዊነት አንድነት ይጠናከራል! የኢትዮጵያ ጀግኖች ይህን በውል ተረድተውታል! አንበሳው ደስታ ሸዋርካብህ ቆርጧል! ጦርነት! ሰኔ 12 ቀን 1928 ዓ.ም! የኢትዮጵያ ጀግኖች የአርበኝነት ግዳጃቸውን በብቃት በመወጣት አቋም ደድረዋል! ባንዳ ህሊናውን በሆዱ ለውጧል! ክብሩን በሊሬ ሸጧል! ጀግናው አርበኛ ደግሞ አሸዋ ለብሶና ድንጋይ ተንተርሶ ከሞግዜሩ ጋር ሲነጋገር ያድራል! ሲነጋገር ይውላል! በአርበኞችና በባዳዎች መካከል ያለው ልዩነት በልዩነት ይህንን ይመስላል!

ጦርነቱ አሁን ተቋርጧል! ምክንያቱ በታሪክ በግልፅ ሳይነገረን ታልፏል! ለአንድ ወር ፍልሚያ ሳይካሔድ ሰንብቷል! የኢትዮጵያ አርበኞች ጊዜያቸውን የጦር መሳሪያ አስሰርገው ለማስገባት ተጠቅመዋል! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የፀረ ፋሽስት ተጋድሎ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው! ሰኔ ነጉዷል! ሐምሌ ገብቷል! ከወር በኋላ ጦርነቱ ፈንድቷል! እሳቱን በእሳት የማጥፋት ተግባር ደምቋል! ዛሬ ሐምሌ 12 ቀን 1928 ዓ.ም ነው! ጦርነቱ ተፋፍሟል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ምሽቱ ገብቷል! ተኩስ ግን ቀጥሎ አድሯል! በነጋታውም የኢትዮጵያ አርበኞች በጋለ ወኔ ሲዋጉ ውለዋል! የወራሪውን ኃይል ተዋጊዎች በከፍተኛ ደረጃ አጥቅተዋል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት በውጊያ መስክ እንዲያይ የግድ ሆኗል!

አንበሳው ደስታ ሸዋርካብህ አሁን ውቴ ከተባለ መንደር ገብቷል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የሰፈረበትን ቦታ ከመስክ መረጃ አውቆታል! የኢትዮጵያ አርበኞች በፅኑ አቋም ለቅድሚያ ተነሳሽነት ወደ ፊት ተጠግተዋል! ቀርበዋል! ቀርበዋል! ቀርበዋል! ድም! ድም! ድም!ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ይህ የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኝነት ተኩስ ድምፅ ነው! የወራሪው ኃይል ተዋጊዎች ለአፀፋ እንዳልዘገዩ ታውቋል! የኢትዮጵያ አርበኞች ግን በጥቂት ጊዜአት የበላይነትን ጨብጠዋል! በውስን የሠው ኃይልና በኋላ ቀር የጦር መሳሪያ ቁርጠኝነታቸውን በተግባር አሳይተዋል! የዓላማ ፅናት ግብን ይወስነዋል! ጦርነቱ በተጋጋለ ሁኔታ ይስተዋላል! የጀግኖች ሀገር የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መፈንጫ ሆና እንደማትቀር ታውቋል! ዛሬ ታህሳስ 19 ቀን በ1929 ዓ.ም ነው! አሁንም በውቴ የውጊያ መስክ የተፋፋመ ጦርነት ቀጥሏል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በኢትዮጵያ አርበኞች ጥይት በተደመሰሱ ምትክ አዳዲስ ተዋጊዋችን ያሰልፋል! በሁለቱም በኩል ተኩሱ እንደቀጠለ አድሯል! ጦርነቱ ሳይበርድ ረፍዷል! ሞቱ ረክሷል! መስዋትነቱ ከብዷል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አዲስ በመጣው ተዋጊ ኃይል በበለጠ የተበረታታ ይመስላል! ሆኖም ተርቦቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ሳይበገሩ ቀጥለዋል! ጦርነቱ አሁን ወደ ተጉለት ወረዳ ተዛምቷል! ቆራጡ አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ በአሁኑ ስዓት በተጉለት ውስጥ መሆኑ ታውቋል! ጦርነቱ አንዴ ጋል ይላል! ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ቀዝቀዝ ሲል ይስተዋላል! የካቲት 16 1929 ዓ.ም! ማን ይፈራል ሞት? ሀገርን ማዳን የትውልድ ቀዳሚ ግዴታ ይሆናል! በመራራ ጦርነት ድል ይበስራል! ጀግናው አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ በአሁኑ ስዓት በግምባር ቀደም ተዋጊነት የውጊያ መስመሩን ይዟል! ድም! ድም! ድም! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዛሬ የካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም! ጀግና ተዋርዶ ከመኖር ሞትን ይመርጣል! ጀግናው አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ በዚህ አቋም ፀንቷል! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የወር ተረኝነት የጦርነት ቀጥታ ድምፅ ነው! ከሸዋ ጠቅላይ ግዛቱ ከተጉለት ወረዳ የውጊያ መስክ የካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም!

ጦርነቱ ቀጥሏል! ጀግና ይገድላል! ጀግና ይቆስላል! ጀግና ይሰዋል! በተጉለት ውስጥ መሆናችን አይረሳ! ጦርነቱ ቀንና ሌት ይካሄዳል! ጦርነት! ጦርነት! ጦርነት! የሀገር ህልውናን ለማረጋገጥ አቋራጭ መንገድ ፍፁም ሊኖር አይችልም! ጦርነት! ለዕብሪተኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሊገባው የሚችል ቋንቋ ጦርነት ብቻ መሆኑን የኢትዮጵያ አርበኞች በውል ተረድተዋል። በምክንያቱ ምክንያት ለህይወታቸው የማይሳሱ ጀግኖች ጦርነቱን ተያይዘውታል! ይህ የታሪክ ቀጥታ ድምፅ ነው! ለ26 ቀናት በተጉለት ውስጥ በተካሄደው በዚሁ መራራ ጦርነት በርካታ ጀግኖች ተሰውተዋል! ከዕብሪተኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎችም በጣም ብዙ ተደምሰሰዋል! በጦርነቱ ሂደት የኢትዮጵያ አርበኞች ከወራሪው ኃይል ተዋጊዎች ልዩ ልዩ የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያዎችን ከመሰል ጥይቶች ጋር ማርከዋል! ጀግናው አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ በዚህ በተራዘመ ጦርነት ባንዶችን እንደ ገብስ ከማጨዱም በላይ ሁለት አልቤን ጠበንጃዎችን ማርኳል!

ድም! ድም! ድም! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ይህ የኢትዮጵያ አርበኞች የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ ተኩስ ድምፅ ነው! ጦርነቱ ቀጥሏል! የጀግኖች ሀገር በጀግኖች ደም ይከበራል! የአርበኞች መሬት በአርበኞች መስዋትነት ይጠበቃል! ጦርነቱ ቀጥሏል! ይህ የታሪክ ቀጥታ ድምፅ ነው! በአርበኝነት ታሪካችን በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ወይራ ገበያ በተባለ የውጊያ መስክ በተጋጋለ ጦርነት መካከል መሆናችን ይመዝገብልን! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከንፍ ያለ የሌለ ኃይሉን ሰብስቦ ይፍጨረጨራል! የኢትዮጵያ አርበኞችን ክንድ ቀምሷል! ያልጠገበ ለመሆኑ ግን እንቅስቃሴው ይመሰክራል! አሁንም ይህችን ቅድስት ሀገር በቅኝ ገዥነት ይዞ ለመቆየት ይቋምጣል! የነፃነት እመቤት ኢትዮጵያ እናታችን ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አትገዛም! አትገዛም! አትገዛም! አትገዛም! ወይራ ገበያ በደም ጨቅይቷል! የሰው ማረጃ ቄራ መስሏል! የባንዳ ሬሳ በየቦታው ተዝረክርኳል! ሞት የማይፈራ ትውልድ ሞትን በሞት ይፋለማል! የኢትዮጵያ ጀግኖች ከጠበንጃዎቻቸው ጋር ጨዋታ ይዘዋል! ጦርነቱ ተጋግሏል! አሁንም በወይራ ገበያ በውጊያ መስመር ላይ መሆናችን ይመዝገብልን! ሞት አይቀርም! ስም አይቀበርም! ግፋ ወደ ፊት! ድም! ድም! ድም! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ይህ የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ ድምፅ ነው! ታሪክ ይነግረናል! ቆራጦቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ነፃነትን አጥንቶ ከመኖር የክብር መስዋዕትነትን በፅኑ አቋም መርጠዋል! ይህ የታሪክ ድምፅ ነው! ቀደምት ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ወደ ፊት ሲገሰግሱ ይስተዋላል! በጉዞ መስመራቸው ላይ ወራሪው ኃይል የያዘውን የመከላከያ በር አስለቅቀዋል! ልበ ሙሉ የጦር ሰው ደስታ ሸዋርካብህ መንገዱን እየጠረገ ይገሰግሳል! ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች አሁን ጁሩ ገብተዋል! ድል የቆረጠች መሆኑ ታውቋል!

ቆራጦች ውድ የኢትዮጵያን አርበኞች ጉዟቸውን ቀጥለዋል! ሞት አይፈሬሞች ጀግኖች በአሁኑ ስዓት እነዋሪ ደርሰዋል! ውጣ ውረዱን በድል እየተሸጋገሩ ዘልቀዋል! አንዱን የጦርነት መሳናክል በጥሰው ሲያልፉ ግን ሌላ የወራሪው ኃይል ምሽግ ይጠብቃቸዋል! አሊያም የወራሪው ኃይል ተዋጊዎች ጊዜአዊ ሠፈረን ያገኙታል። በዚህ ሂደት በመስክ ቀዳሚ ስምሪት መረጃ እንዲሰበስቡ የግድ ይሆናል! አሁንም እነዋሪ ላይ የሰፈረውን የወራሪው ኃይል ተዋጊ በማስመልከት በቂ መረጃ አግኝተዋል! ወራሪው ኃይል በተጠንቀቅ ላይ መሆኑን ቆራጦቹ የኢትዮጵያ አርበኞች አውቀዋል! ጀግናው የኢትዮጵያን አርበኞች ደስታ ሸዋርካብህ ከወራሪው ኃይል ተዎጊዎች ሰፈር በቅርብ ርቀት ላይ ይስተዋላል! አርበኞቹ ተጠግተዋል! የወራሪው ኃይል ተዋጊዎች እንደማይቀርላቸው አውቀዋል! ቅድሚያ ተነሳሽነትን ወስደዋል! ወዲያው በነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ ተኩስ ከፍተዋል! ቆራጦቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ለአፀፋ ተኩስ ከአንድ ደቂቃ ክፍልፋይ በላይ ጊዜ እንደአላስፈለጋቸው ታውቋል! ጦርነቱ በቅፅበት ተጋጋለ! ይህ የታሪክ ድምፅ ነው! አንዘንጋ! እናስታውስ!

ጦርነቱ አሁን ተቋርጧል! ምክንያቱ በታሪክ በግልፅ ሳይነገረን ታልፏል! ለአንድ ወር ፍልሚያ ሳይካሔድ ሰንብቷል! የኢትዮጵያ አርበኞች ጊዜያቸውን የጦር መሳሪያ አስሰርገው ለማስገባት ተጠቅመዋል! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የፀረ ፋሽስት ተጋድሎ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው! ሰኔ ነጉዷል! ሐምሌ ገብቷል! ከወር በኋላ ጦርነቱ ፈንድቷል! እሳቱን በእሳት የማጥፋት ተግባር ደምቋል! ዛሬ ሐምሌ 12 ቀን 1928 ዓ.ም ነው! ጦርነቱ ተፋፍሟል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ምሽቱ ገብቷል! ተኩስ ግን ቀጥሎ አድሯል! በነጋታውም የኢትዮጵያ አርበኞች በጋለ ወኔ ሲዋጉ ውለዋል! የወራሪውን ኃይል ተዋጊዎች በከፍተኛ ደረጃ አጥቅተዋል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት በውጊያ መስክ እንዲያይ የግድ ሆኗል!

እንዲሁም 600 ጥይቶችን ከነካሴታው እንደ ማረከ በአርበኝነት ዝርዝር ታሪኩ ተመልክቷል! በዚሁ ጦርነት በግፈኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደ ደረሰበት ታውቋል! የጀግናን ልክ ከጦር ሜዳ በላይ ማን ሊነግረን ይችላል? ጀግናው አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ ማንነቱን በተግባር አስመስክሯል! እናቱ መንታ ትውለድ! ይህ የጀግናው ገድል ድምፅ ነው!

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በደረሰበት ኪሳራ ሽንፈቱን ተቀብሎ የኢትዮጵያን መሬት ለቅቆ ለመውጣት ዝግጁ አልነበረም። ይልቁንም የተዋጊዎችን አቅም አጎልብቶ ለጥቃት ሲቅበዘበዝ ተስተውሏል! ይህ የታሪክ ቀጥታ ድምፅ ነው! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አንድ ተዋጊ ክንፍ አሁን ወይራ ገበያ በተባለ ቦታ ሰፍሮ እንዳለ ታውቋል። ጀግናው አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ መረጃው በስዓቱ ደርሶታል። ተገቢው እርምጃ በተገቢው ስዓት ሊወሰድ ይገባል። ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች በተጠንቀቅ ቁመዋል! ብዙ ጊዜ ግን አልፈጁም! ከጥቂት ጊዚአት በኋላ ወደ ወይራ ገበያ ተንቀሳቅሰዋል! የቅድሚያ ተነሳሽነትን በተኩስ አሳውቀዋል! ከባድ ጦርነት ተከፈተ! ከወራሪው ኃይል ተዋጊ ክንፈ ብዙ ባንዶች ተደመሰሰዋል! ከኢትዮጵያ አርበኞችም የተወሰኑ ጀግኖች በክብር ወድቀዋል! ቆራጦቹ የኢትዮጵያ አርበኞች የአድዋ ጀግኖች ቀጥታ ተወላጆች መሆናቸው ልብ ሊባል ይገባል። ድል ማድረግ ልማዳችን መሆኑ ይታወቃል! ቅኝ ተገዥነትን የሚቀበል ስራ ልቦና መቼ ኖሮን ያውቃል? መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን! እንደነበሩ ይታወሳል! በዚህች ሀገር ላይ ትውልዶች የኮሩበት ትውልድ ተፈራርቋል! ለታሪክ የተፈጠረ ትውልድ ታሪክ ሰርቷል! ከብዙ ሰዓታት ውጊያ በኋላ የኢትዮጵያ አርበኞች የበላይነትን ተቀዳጅተዋል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎች ሲፈራጠጡ ይስተዋላል! በወይራ ገበያ የጦርነቱ የኃይል ሚዛን ተለውጧል! ቆራጦቹ የኢትዮጵያ አርበኞች የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎችን እያሳደዱ ሲደፉት ይታያል! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች የጦርነትና የድል ቀጥታ ድምፅ ነው! ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት ከወይራ ገበያ ጦር ሜዳ! ከሚያዚያ 29 እስከ ግንቦት 2 ቀን በ1929 ዓ.ም! አንበሳው የኢትዮጵያ ልጅ ደስታ ሸዋርካብህ ለአፍታም ሳያርፍ ጦርነቱን ይመራል! ከቅኝ ተገዥነት ይልቅ በፅኑ አቋም መስዋዕትነትን የመረጡ አናብስት ከጎኑ ቆመዋል! የወራሪውን ኃይል ሰፈር ሰንጥቀው እየተዋጉ ወደ ጁሩ ለመውጣት አቋም ወስደዋል! የተሰውትን ጀግኖች ቀብረዋል! ለተከታይ ፍልሚያ በአዲስ መንፈስ ተነስተዋል! የተሰው ጀግኖችን የጦር መሳሪያ ጦርና ጋሻ ብቻ ለያዙ አርበኞች አድለዋል! ጉዞ ወደ ፊት! አዲስ ውጊያ ተከፍቷል! ቆራጡ አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ አሁን ደንገዜ በተባለ ቦታ በተፋፋመ ውጊያ ላይ ይስተዋላል! ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች በጠንካራ የውጊያ ዝግጁነት መንፈስ ግዳጁን በድል ለመደምደም ቆርጠዋል! በዚህ ጦርነት ጀግናው ደስታ ሸዋርካብህ ጀብዱ ፈፅሟል! አሁን የኢትዮጵያ አርበኞች የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊያዎችን እየመነጠሩ እነዋሪ ላይ ከፍተኛ ጦርነት ይካሄዳል! ቆራጦቹ የኢትዮጵያ አርበኞች እነዋሪ ላይ የወራሪውን ኃይል ተዋጊዎችን ደምስሰው ወደ መርሐቤቴ ለመግባት አቋም ይዘዋል! ይሳካላቸው ይሆን? ደፋርና ጭስ መቼ መውጫ አጥቶ ያውቃል? ጦርነቱ ቀጥሏል! ውጊያው ተፋፍሟል! ከሰዓታት ፍልሚያ በኋላ አርበኞቹ የበላይነትን ጨብጠዋል! የድል ጉዞ መንገዱ ተጠርጓል! ጀግናው ደስታ ሸዋርካብህ በዚህ ጦርነት በከፍተኛ ጀብዱ እንደፈፀመ ተመልክቷል! የወራሪው ኃይል ተዋጊዎች ተደምስሰዋል! ግፍ ወደ ፊት! ይህ የጀግናው አርበኛ የደስታ ሸዋርካብህ የውጊያ አመራር የመስክ ትዕዛዝ ነው! የኢትዮጵያ አርበኞች ከተደመሰሱ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎች ሬሳ ላይ የጦር መሳሪያዎችን ፈትተው ሰብስበዋል! በርካታ የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎችና ዝናሮች ተገኝተዋል! ጉሮ ወሸባ! ጉሮ ወሸባ! የኢትዮጵያ አርበኛ ድል አድርጎ ሲገባ!

ቆራጡ አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ ዓላማው ተሳክቶለታል! ወደ መርሐቤቴ አቅንቷል! ድል አድራጊው አርበኛ ገስግሷል! ከጀግና ጋር ለመሰዋት የቆረጡ አርበኞችን አስከትሏል! ማን ይፈራል ሞት? አሁን የኢትዮጵያን አርበኞች መርሐቤቴ ገብተዋል!

አንበሳው የኢትዮጵያን አርበኛ ደስታ ሸዋርካብህ እንደገናም ደንገዜ ላይ ከፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ኃይል ጋር ተዋግቶ ጀግንነቱን አስመስክሯል! አኩሪ ውጤትም አስመዝግቧል! ወረሪው ኃይል የኢትዮጵያን መሬት ለቅቆ ሳይወጣ ምን

ወደ ገፅ 6 ይዞራል

# የሰላማዊ ትግል እድገታችን (2)



ግርማ ሞገስ

(6) በ20ኛው መገባደጃ እና ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን በአልበርት አነስታይን ተቋም

ባለንበት ዘመን በዓለም ውስጥ በርካታ ታዋቂ የሰላማዊ ትግል ተመራማሪዎች እና ጸሐፊዎች አሉ:: ይሁን እንጂ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ጀምሮ በሰላማዊ ትግል አምባገነኖችን ከመንግስት ስልጣን በማስወገድ ረገድ ለተሳኩ ሰላማዊ ትግሎች ቀጥተኛ ጥናታዊ ጽሑፎች በማተም እና ምክሮችን በስልጠና መልክ በመለገስ ረገድ ግን ቦስተን ከተማ የሚገኘው የአልበር አነስታይን ሰላማዊ ትግል ምርምር ተቋም ጎልቶ ወጥቷል:: የዚህ ተቋም ተቀዳሚ ትኩረት የሰው ልጅ ባለንበት ክፍለ ዘመን እንዴት በሰላማዊ ትግል ከአምባገነኖች ነፃ ሊወጣ እና ድሉን ከቅልበሳ ጠብቆ ወደ አስተማማኝ ዴሞክራሲ መሸጋገር ይችላል? የሚል ሲሆን ሁለተኛው ተዛማጅ ትኩረቱ ደግሞ በአለም ወስጥ እርስ በርስም ይሁን በአገሮች መካከል የሚፈጠሩ ጦርነቶችን ተቃዋሚ የነበረውን ታዋቂ የፊዚክስ ሊቅ የአልበርት አነስታይን (1879-1955) ምኞት መታሰቢያ ነው::

ለምን አልበርት አነስታይን የሚል ስያሜ ተሰጠው ተቋሙ? ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ ባጭሩ የአቶሚክ ቦንብ የተፈጠረው በ1905 ዓ.ም. አልበርት አነስታይን ስለ ኢነርጂ (Energy) የቀመረውን ፎርሙላ በመተቀም በመሆኑ እና አልበር አነስታይን ግን ፎርሙላውን የቀመረው ለአቶሚክ ቦንብ መፈጠር ብሎ ሳይሆን ለሌሎች ሰላማዊ የሰው ልጅ ኢነርጂ (Energy) ፍጆታዎች ብሎ ነበር:: ስለዚህ አለበር አነስታይን ከ1929 ዓ.ም. ወዲህ ጀምሮ በዓለም ውስጥ በአገሮች መካከል ጦርነት ቢነሳ ምንም አይነት ወታደራዊ ግልጋሎት እንደማይሰጥ እና የማንኛውም አይነት ጦርነት ተቃዋሚ መሆኑን በህትምት ለዓለም ህዝብ አሳውቆ ነበር:: የፈራው አልቀረም በሁለተኛው ዓለም ጦርነት አሜሪካ ፎርሙላውን በመጠቀም አቶሚክ ቦንብ ሰርታ በ1945 ዓ.ም. ሂሮሽማ እና ናጋሳኪ የተባሉ ሁለት የጃፓን ከተሞችን በአቶሚክ ቦንብ በመምታት ሁለቱ ከተሞች ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ እንዲቀልጥ አድርጋ ጃፓንን ማሸነፍ ቻለች:: ዛሬምም ድረስ በአካባቢው የሚወለዱ ሰዎች የሚዘገንን የአእምሮ እና የአካል ጉድለቶች አሉዋቸው:: ከቦንቡ መሰራት ጀምሮ ጦርነቱን አልበርት አነስታይን ተቃውሟል:: አልበርት አነስታይን የሰላማዊ ትግል አማኝ ነበር:: ተቋሙ የአልበር አነስታይን መታሰቢያ የተባለው በዚህ ምክንያት ነው::

ተቋሙን የመሰረተው በሃርቫርድ ዩንቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰር የሆነው ጅን ሻርፕ (Gene Sharp) ነው:: ተቋሙ የሚሰራው ለትርፍ አይደለም:: ጅን ሻርፕ በ1928 ዓ.ም. በኦሃዮ ክፍለ አገር (Ohio State) ተወልዶ የመጀመሪያ ዲግሪዎቹን ከሰራ በኋላ ዶክትሬቱን በኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ አገኘ:: የመመረቂያ ወረቀቶቹም በሰላማዊ ትግል ጥናት እና ምርምር ላይ ያተኮሩ ናቸው:: ስለዚህ ጋንዲ በብዙ የዘመናችን የሰላማዊ ትግል ተመራማሪዎች ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ጅን ሻርፕንም አልማረም ነበር:: ጅን ሻርፕን የእድሜ ልክ የሰላማዊ ትግል ተማሪ፣ ተመራማሪ እና መምህር እንዲሆን አድርጎታል::

ጅን ሻርፕ የጋንዲን እና ዓለማችን ከጋንዲ ቀደም ብላ ያፈራቻቸው የሰላማዊ ትግል ፈላስፎች እና አራማጆች ለሰው ዘር ያበረከቱትን እውቀት አሰባስቦ እና የራሱንም ምርምር ጨምሮ በንደፈ ሀሳብ እና በአፈጻጸም ሰላማዊ ትግልን ከፍተኛ ደረጃ አድርሶታል:: ብዙ የሰላማዊ ትግል ተመራማሪዎችም አፍርቷል:: በዩንቨርስቲም ሆነ በመጽሐፎቹ የሚያስተምረው ሰላማዊ ትግል ነው:: የመሰረተው ተቋምም በዘመናችን የሰላማዊ ትግልን መሰረታዊ ሀሳብ በተለያዩ የዓለም ቋንቋዎች በማሰራጨት ዓለም አቀፍ እውቅናን አግኝቷል::

የጅን ሻርፕ ስራዎች በከፊሉ የሚከተሉትን ያካትታሉ፥ (1) ከርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ለነፃነት ያደረጋቸውን ሰላማዊ ትግሎች ታሪክ በማሰባሰብ ረገድ ጅን ሻርፕ ብዙ ጠቃሚ ስራዎች ሰርቷል:: (2) ስለ ሰላማዊ ትግል ንድፈ ሀሳብ እና አፈጻጸም ዘመናዊ የሆኑ በርካታ መጽሐፍቶች ጽፏል:: ከአምባገነን ወደ ዴሞክራሲ የሚለው መጽሐፉ በአምባገነን አገሮች ስለሚደረጉ ሰላማዊ ትግሎች ያሉትን ሀሳቦች ጨምቆ ያቀርባል::

የጅን ሻርፕ እና የባልደረቦቹ ሰላማዊ ትግል ስራዎች በምስራቅ አውሮፓ፣ በላቲን አሜሪካ፣ አሁን በቅርቡ ደግሞ በግብጽ፣ በየመን፣ በቱኒሲያ እና በቀሩት አረብ አገሮች ህዝቡ የራሱ ነፃ አውጪ በመሆን አምባገነኖችን ከስልጣን ማስወገድ እና ወደ ዴሞክራሲ መሸጋገር እንዲችል በማድረግ ትልቅ አስተዋጾ አድርጓል:: እርግጥ በግብጽ እና በመሳሰሉት አገሮች ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገው ሽግግር አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል:: ምክንያቱ ግን ሰላማዊው ትግል እና ሰላማዊ ትግል ለውጥ የሚያመጣባቸው ሶስቱ መንገዶች ባለመስራታቸው ሳይሆን የሰላማዊ ትግል መሪዎች እውቀት ማነስ እና የዝግጅት እጥረት ነው::

የፖለቲካ ኃይል ምንጮች፣ የፖለቲካ ድጋፍ ምሶሶዎች፣ የሰላም ትግል መሳሪያዎች (200 ግድም ደርሰዋል)፣ የሰላማዊ ትግል ለውጥ ማምጫ መንገዶች፣ ህዝብን የራሱ ነፃ አውጭ ማድረግ፣ የሰላማዊ ትግል አቅም መገንባት፣ ሰላማዊ ትግልን ፕላን ማድረግ (ግብታዊ እንዳይሆን)፣ የትጥቅ ትግልን ችግሮች፣ ሰላማዊ ትግል እና መለዮ ለባሽ፣ ሰላማዊ ትግል እና ከተሞች፣ ሰላማዊ ትግል እና ምርጫ (ለምርጫ ፓርቲዎች)፣ ሰላማዊ ትግል እና መፈንቅለ መንግስት የሚሉት ቁልፍ ጽንሰ አሳቦች በሙሉ ግልጽ በሆነ መንገድ ተተንትነው የተሰራጩት በአልበርት አነስታይን ተቋም ባልደረባ ምሁራን እና ተመራማሪዎች ነው::

አንድ ህዝብ ሰላማዊ ትግል እና ምርጫ በመጠቀም የራሱ ነፃ አውጪ ለመሆን የሚሻ ከሆነ የፖለቲካ ኃይል ምንጮችን ለይቶ ማወቅ እና የፖለቲካ ምንጮችን ለመቆጣጠር የሚያስችል አቅም መገንባት እንደሚያስፈልገው የሚቀጥለው የሰርቢያ ህዝብ የነፃነት እና የዴሞክራሲ አጭር ታሪክ ያስረዳል፥

በ1990ዎቹ ሰርቢያዎች የአምባገነኑን የሞልሶቪች መንግስት በመቃወም አጥንት የሚሰብር የክረምት ብርድ ሳይበግራቸው ሰላማዊ ሰልፎች ያደርጉ ነበር:: ይሁን እንጂ በሰላማዊ ሰልፍ ብቻ የሞልሶቪችን መንግስት ከስልጣን ማስወገድ እንደማይችሉ በመረዳታቸው በሰላማዊ ትግል የሞልሲቪችን መንግስት መጣል የሚያስችላቸው ተጨማሪ ሀሳብ ያፈላልጉ ነበር:: በዚህን ጊዜ ነበር የሰርቢያ ሰላማዊ ትግል ጎበዝ ስትራተጂስት ስርድጃ ፖፖቪች (Srdja Popovic) የጂን ሻርፕ ባልደረባ ሄልቬይ (Helvey) ቡዳፔስት (ሃንጋሪ) ውስጥ ሰላማዊ ትግል ስልጠና በመስጠት ላይ ሳለ የተገናኘው:: ስትራተጂስቱ ስርድጃ ፖፖቪች (Srdja Popovic) ለሄልቬይ (Helvey) ፍላጎቱን ከገለጸለት በኋላ በምላሹ ሄልቤይ (Helvey) የራሱን የስልጠና ስራ ከአምባገነን ወደ ዴሞክራሲ እና የሰላማዊ ትግል ፖለቲካ (The Politics of Nonviolent Action) ከሚሉትን የጅን ሻርፕን ስራዎች ጋር ጨምሮ እንዲያነብ መክሮት እና መጽሐፍቶቹን ሰጥቶት ይለያያሉ::

ስርድጃ ፖፖቪች (Srdja Popovic) የተባለውን ካደረገ በኋላ "ጅን ሻርፕ ህዝብን በሰላማዊ ትግል የራሱ ነፃ አውጭ በማድረግ አምባገነን መንግስትን ማስወገድ የሚያስችል አስደናቂ ስራ ለግሷል::" ይላል:: "አስደናቂ ስራዎች" የሚለው ጅን ሻርፕ የተነተናቸውን 6 የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ምንነት ጨምሮ ማለቱ ነው:: ከዚያ ስርድጃ ፖፖቪች (Srdja Popovic) እና ጓደኞቹ በጅን ሻርፕ መጽሐፍ ውስጥ በተዘረዘሩት 6 የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ላይ ያተኩራሉ:: በመጨረሻም በ2000 ዓ.ም. የተደረገውን ምርጫ ተከትሎ ሞልሶቪች እንደተለመደው ድምጽ በመስረቅ ምርጫውን ማሸነፉን ቢገልጽም ህዝብ የገዢነት መብት፣ አገር ለማስተዳደር ከህዝብ የሚያገኛቸውን ትብብር እና ድጋፍ (የሲቪል ሰርቫንቱን ትብብር)፣ የአገር ተፈጥሮ እና ኢኮኖሚ ሃብት ባለቤትነት የተባሉትን የፖለቲካ ኃይል ምንጮች በመንፈግ ድምጹን አስከበረ:: የኢኮኖሚ ሃብት ባለቤትነቱን በማጣቱ ለመለዮ ለባሹ የወር አበል መክፈል እንደማይችል ግልጽ ሲሆን መለዮ ለባሹ ሞልሶቪችን ከድቶ ህዝብን ተቀላቀለ:: ታማኝነቱን እና ታዛዥነቱን በምርጫ ላሸነፉት ፓርቲዎች መሪ ለገሰ:: ሞሊሶቪች ከስልጣን ወረደ::

እነዚህ የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ህዝብ በፈቃደኛነት፣ ወይንም በፍራቻ፣ ወይንም በግዴለሽነት ለአምባገነኖች የሚለግሳቸው ናቸው:: ስለዚህ ህዝብ የለገሰውን 6 የፖለቲካ ኃይል ምንጮች እንዲነፍግ ለማድረግ የርስ በርስ ጦርነት (ትጥቅ ትግል) ማወጅ እና ከምስኪኑ መለዮ ለባሽ ጋር ደም መፋሰስ ትክክል አይደለም:: እንደ ኢትዮጵያ አይነቱ አገር ውስጥ አብዛኛው ዝቅተኛ ማዕረግ መለዮ ለባሽ እና ተራ ወታደር ወታደርነት የሚቀጠረው እራሱን ለመመገብ፣ ደሃ እናቱን ለመርዳት እና ልጆቹን ለመመገብ እና ለማስተማር ሲል መሆኑ መታወቅ አለበት:: ለስልጣን ሲባል ከማንም የኢትዮጵያ ጠላት መንደር በተሰበሰበ እርዳታ የኢትዮጵያን ምስኪን ተራ ወታደር ደም ማፍሰስ ኢ-ሞራል (Immoral) ነው:: አምባገነኖችን ከስልጣን ለማስወገድ እንኳን ቦምብ ማፈንዳት፣ ክፉ ቃል መለዋወጥ እና ጠብ መፍጠር አያስፈልግም:: ከ6ቱ የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ውስጥ ዋናዎቹን በሰላማዊ ትግል በመቆጣጠር እና በመንፈግ አምባገነኖችን ከስልጣን ማስወገድ ይቻላል:: 6ቱን የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ወደፊት ከቦታው ስንደርስ እናነባቸዋለን:: አምባገነኖች አለን ብለው የሚነግሩዋችሁን ያህል አቅም የላቸውም::

(ለ) የሰላማዊ ትግል እድገት በኢትዮጵያ

በዚህ ክፍል በኢትዮጵያ የሰላማዊ ትግልን ታሪክ እና ሰላማዊ ትግል በኢትዮጵያ ያደረገውን ትግል እናጠናለን::

(1) በ17ኛው ክፍለ ዘመን የታላቁ እያሱ (ዐፄ እያሱ አንደኛ) ሰላማዊ ትግል

ዐፄ ሠርፀ ድንግል (1556-1590) ወራሪዎቹን ቱርኮች ከምጽዋ ቢያባርር እና ምጽዋን ነፃ ቢያወጣም በኢትዮጵያ የጦር መሳሪያ ኋላቀርነት እና በተለይም ካዔ ሠርፀ ደንግል ወዲህ በኢትዮጵያ ለስልጣን የሚደረገው የእርስ በርስ ጦርነት ስለተባባሰ ቱርኮች ከምጽዋ አልፈው እስከ ድባርዋ ድረስ ተጠናክረው መያዛቸው እና ከድባርዋ እንዲወጡ ቢደረግም ጣሊያን በ1877 ዓ.ም. በጦር እስከያዘቻት ጊዜ ድረስ ምጽዋ ለ300 መቶ አመቶች ያህል ዘመን በቱርኮች ስር መቆየቷ ይታወቃል::

ስለዚህ በኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ላይ ቱርኮች የጋረጡትን እንቅፋት ለማስወገድ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ህዝቡ ታላቁ እያሱ (1674-1698/9) ብሎ የሚጠራው ተወዳጅ ንጉሰ ነገስት በታሪካችን ሰላማዊ ትግል አድርጓል:: ከእያሱ ሰላማዊ ትግል የምንማረው በሰላማዊ ትግል ፍልስፍና እምነት በመመራት ብቻ ሳይሆን የአቅም ጉዳይም ሰላማዊ ትግል እንድንማር ሊያስገድደን እንደሚችል ነው:: ጭንቅላቱ ካለ ማለት ነው! እያሱ ብልህ ሰው ነበር::

የምጽዋን ወደብ በመያዛቸው ቱርኮች ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ ቀረጥ እየጨመሩ የኢትዮጵያ ነጋዴ እንዲጎዳ እና የኢትዮጵያ ውስጥ ንግድ እንዲዳከም አደረጉ:: (1) በምጽዋ ያሉት ቱርኮች የሚበሉትን እና የሚጠጡትን በሙሉ የሚገዙት ከኢትዮጵያ ነጋዴዎች እንደሆነ ታላቁ እያሱ ያውቃል:: (2) ቱርኮች ምግብ እና መጠጣቸውን በጦርነት ማረጋገጥ ከፈለጉ ደግሞ ጦርነት ለማድረግ ሜዳ ወዳለበት ወደ ኢትዮጵያ ምድር ገባ ማለት አለባቸው:: ቱርኮች መድፍ እና የመሳሰሉት በወቅቱ ዘመናዊ የሚባሉት የጦር መሳሪያዎች ቢኖሩዋቸውም ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ተዋጊ ፈረሰኞች በፈረሰኛ ጋልበው ቱርኮች መካከል እየገቡ ጦርነቱን ወደ ጨበጣ ውጊያ እየለወጡባቸው ቱርኮችን ደጋግመው ስላሸነፉዋቸው ቱርኮች በኢትዮጵያ ሜዳ ላይ ከኢትዮጵያውያን ጋር መዋጋት አይፈልጉም:: ታላቁ እያሱ እነዚህን ሁለት ሃቆች ያውቃል:: ስለዚህ ታላቁ እያሱ ጦሩን ቀደም ብሎ አክሱም እና ሃሜሴን ላይ አስፍሮ ከትግሬዎች እና ሃማሴኖች ጋር ከመከረ በኋላ ከኢትዮጵያ ወደ ምጽዋ ወደብ ምንም አይነት ምግብ ነክ ሸቀጥ እንዳይሄድ ዐዋጅ አስነገረ:: ቱርኮች የምግብ ምንጫቸው ተዘጋ:: በዚህ አይነት ቱርኮችን በአዋጅ እንዲራቡ በማድረግ ቱርኮችም በተራቸው ከወደቡ የሚያገኙት ጠቀሜታ ዝቅ እንዲል አደረገ:: ታላቁ እያሱ በዐዋጅ የንግድ ልውውጥ እገዳ አደረገ ማለት ነው:: ቱርኮች የሚበሉት ተቸገሩ:: በደረሰባቸው ችግር ተገደው ወደ ድርድር መጡ:: ከዚህ በፊት የዘረፉትን ሸቀጥ መለሱ:: የጫኑትን ቀረጥ አነሱ:: በዘመናችንም የዚህ አይነት የንግድ እቀባ በመንግስታት መካከል የሚደረግ የሰላም ትግል እንደሆነ እናውቃለን:: የሰላም ትግል በሚል ባይፈርጀውም የተደረገውን ዝርዝር ሁኔታ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ "የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ካዔ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ" በሚለው መጽሐፍ ገጽ 179 ላይ በሰፊው ይተርካል:: ባጭሩ እንመልከት::

ናይብ ሙሳ የተባለው በምጽዋ እና በአርኪቆ የነበረው የቱርኮች ሹም ብዙ ሸቀጥ እየነጠቀ እና ቀረጥ እያበረከተ የምጽዋ እና የሐማሴን

ወደ ገፅ 6 ይዞራል

**በኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ላይ ቱርኮች የጋረጡትን እንቅፋት ለማስወገድ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ህዝቡ ታላቁ እያሱ (1674-1698/9) ብሎ የሚጠራው ተወዳጅ ንጉሰ ነገስት በታሪካችን ሰላማዊ ትግል አድርጓል። ከእያሱ ሰላማዊ ትግል የምንማረው በሰላማዊ ትግል ፍልስፍና እምነት በመመራት ብቻ ሳይሆን የአቅም ጉዳይም ሰላማዊ ትግል እንድንማር ሊያስገድደን እንደሚችል ነው።**

**ጭንቅላቱ ካለ ማለት ነው! እያሱ ብልህ ሰው ነበር።**

ሰማያዊ ፓርቲ (ሰማያዊ)    BLUE PARTY (BLUE)

# በሴቶች የነጻነት ቀን በሴት አባላቶቻችን ላይ የተወሰደውን ህገ ወጥ እርምጃ እናወግዛለን!

**ከሰማያዊ ፓርቲ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ**

‹‹ማርች-8›› የሴቶችን ነጻነትና እኩልት እንዲሁም ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ የሚከበር የሴቶች ቀን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህን በዓል አስመልክቶ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ባለፈው ዕሁድ የካቲት 30/2006 ዓ.ም ሴቶች ብቻ የሚሳተፉበት የጎዳና ላይ ሩጫ ማዘጋጀቱ ይታወቃል፡፡ በዚህ የሐገራችንም ሆነ የዓለም ሴቶች የነጻነት ቀናቸውን በሚያከብሩበት ዕለት እንደሌሎች ሴቶች ሁሉ የሰማያዊ ፓርቲ አባላትም አላማውን ደግፈው በዕለቱ ቀኑን አስመልክቶ በተዘጋጀው ሩጫ ላይ ተሳትፈዋል፡፡

እንደሚታወቀው ታላቁ ሩጫ በተለያየ ጊዜ በሚካሄድበት ወቅት ተሳታፊዎች በሐገራቸው የሰፈነውን ጭቆና በመቃወም ሀሳብን የመግለጽ ህገ መንግስታዊ መብታቸውን በመጠቀም ድምጻቸውን የሚያሰሙበት በመሆኑ ‹‹የብሶት መግለጫ›› መድረክ እስከመባል ደርሷል፡፡ ልክ እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ በእሁዱ የጎዳና ሩጫም  በርካታ የሩጫው ተሳታፊዎች ይህን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ የመጣውን ጭቆና በመቃወም ድምጻቸውን ሊያሰሙበት ችለዋል፡፡

በዚህ በሴቶች የነጻነት ቀን በስርዓቱ ላይ የሚነሱ ብሶቶችን ካሰሙት ተሳታፊዎች ውስጥ የሰማያዊ ፓርቲ አባላት የሚገኙበት ሲሆን፣ በተለየ መልኩ በእነዚህ አባላቶቻችን ላይ ያነጣጠረ የአፈሳ እርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡ ሰማያዊ ፓርቲ እንደዚህ አይነት ህዝባዊ መድረኮችን ላይ ብቻ ሳይሆን ሁሌም ህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል በማጋለጥ ለህዝብ መብት እና ለአገራችን ብሄራዊ ጥቅም በመቆሙ በገዥው ፓርቲ ተደጋጋሚ ህገ ወጥ እርምጃ ሲወሰድበት ቆይቷል፡፡ በትናንትናው ዕለት የተደረገውም ከዚሁ ፓርቲው ለህዝብና ለአገር መቆሙን ተከትሎ እየደረሰበት ያለው የከፋ የጭቆና አካል ነው፡፡

ምንም እንኳ ይህ የህወሓት/ኢህአዴግ ህገ ወጥ እርምጃ አዲስ ባይሆንም በሴቶች ነጻነት ቀን በአባላቶቻችን ላይ የተወሰደው ህገ ወጥ እርምጃ አገዛዙ በህገ መንግስቱም ሆነ በሌሎች ህጎች ለሴቶች መብት መከበር የደነገጋቸው አንቀጾች ከወረቀት ያለፉ እንዳልሆኑ በተጨባጭ ያሳየ ምሳሌ ነው፡፡ ከምንም በላይ አባላቶቻችን የታሰሩበት ምክንያት ‹‹የጣይቱ ልጅ ነን፣ የምኒልክ ልጅ ነን›› ማለታቸው እንደሆነ በመርማሪ ፖሊስ የተገለጸላቸው መሆኑ ነው፡፡ ይህም ህወሓት/ኢህአዴግ ምን ያህል ከታሪክ ጋር የተጣላ መሆኑን ከማሳየቱም በተጨማሪ አባላቶቻችን ለማሰር አሳፋሪ የሆኑ ምክንያቶች እየፈለገ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ይህኛውን እርምጃ የተለየ የሚያደርገው ሰማያዊ ፓርቲ በመላው አገሪቱ መዋቅሩን እያደራጀና ህዝብን ከጎኑ እያሰለፈ ባለበት ወቅት መሆኑ፤ የህዝብ ድጋፍ የሌለው ገዥው ፓርቲ በሰበብ አስባቡ ሰማያዊ ፓርቲን ከወዲሁ ለማዳከም የወሰደው ነው፡፡  በተለይ የምርጫ ወቅት እየቀረበ መሆኑን ተከትሎ ይህን ህገ ወጥ እርምጃ መውሰዱ አሁንም ቢሆን የአገራችን የፖለቲካ ምህዳር ምን ያህል እየጠበበ እንደሄደ ያሳያል፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ መቼም ቢሆን ይህንና መሰል የአገዛዙን አፈናዎች አጥብቆ የሚያወግዛቸውና የሚታገላቸው መሆኑን እየገለጸ በሴቶች የነጻነት ቀን ያላአግባብ የታሰሩ አባላቶቻችን በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል፡፡ ኢትዮጵያውያንና መላው የዓለም ማህበረሰብ ይህን ህገ ወጥ እርምጃ ተመልክቶ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን እንዲቆም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር!!!

መጋቢት 1 ቀን 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ስልክ፣ +251920 761 776 / +251910 506 411 ኢ-ሜይል፡- info@semayawiparty.org Website:- www.semayawiparty.org

# እድገት፣ ልማት፣ ጥራት…

አፈወርቅ በደዊ

የተለያዩ ሚዲያዎች እንደምንሰማው ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለማችን እጅግ ፈጣን እድገት (growth) ከሚያስመዘግቡ ሃገሮች አንዷ እንደሆነች ይነገራል:: በአንድ አገር እድገት አለ ለማለት መለኪያው የህዝብ ተጠቃሚነት ነው:: ታዲያ ህዝቡ ከዚህ እድገት ምን አተረፈ? የመንገድ፣ የት/ት ተቋማት፣ የጤና ማዕከላት … እና የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ግንባታ በከፍተኛ ደረጃ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ከሚስራባቸው ፕሮጀክቶች መካከል ዋነኞቹ ናቸው:: ታዲያ እነዚህ ምን ያህል ጥራትን መሰረት ያደረጉ ናቸው? አንዳንዶች ጥራት ቀስ በቀስ ይመጣል ሊሉ ይችላሉ:: በእኔ እምነት ግን ከብዛት ጥራት ያሳስበኛል:: አንድ አዲስ ዩኒቨርሲቲ ወይም ሆስፒታል ከመገንባት የነባሮቹን አቅም መገንባት የተሻለ ነው::

የበግ መንጋ ውስጥ እንደገባ ተኩላ ማህበረሰቡን የሚያምሰው ከነዚህ ጥራት የሌላቸው ትምህርት ተቋማት የሚመረቀው የህብረተሰብ ክፍል ነው:: ከግብርና ትምህርት ተቋሞቻችን የምናስመርቃቸው ባለሞያዎቻችን ጥራት ከሌላቸው በዘርፉ የሚተዳደረውን ህብረተሰብ ክፍል ወዳልተፈለገ መንገድ እየመሩ እንኳን ለተቀረው ህብረተሰብ የምግብ ዋስትናን ሊያረጋግጥ እራሱንም መመገብ ይሳነዋል:: እንዲሁም ጥራት የሌለው የጤና ባለሙያ እንኳንስ ህብረተሰብን ከበሽታ ሊጠብቅ እና ሊፈውስ እራሱም መገኛው ከሆስፒታል እና ጤና ጣቢያ ይልቅ በየ መጠጥ እና ጫት ቤቱ ይሆናል:: በጤናው፣ በቤቶች ልማት እና በመንገዱ ዘርፍ የምናካሂዳቸው ግንባታዎች ይበል የሚሰኙ ቢሆኑም የእነርሱም የጥራት ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ነው:: የመንገዱ ግንባታ ከምጠናቀቁ በፊት ከመጀመሪው የሚፈረካከስበት ሁኔታ ትንሽ አይደለም:: በግንባታ ስም ነባር መንገዶች ተቆፍረው ለአመታት ህዝብን ለተለያዩ ችግሮች ማጋልጣቸው በየአከባቢው የተለመደ ሆኗል:: በተጨማሪም በጋራ መኖሪያ ቤቶቻችን አከባቢ የምናየው የጥራት እና ተያያዥ ችግሮች ለግንባታ ካወጣነው ወጪ በላይ እያስወጡን ይገኛሉ::

ቤት ገንብቶ እና የጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል የሚል ታፔላ ለጥፎ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል ማለት አይቻልም:: ጤና ተቋማትን ጤና ተቋማት የሚያሰኛቸው የተለጠፈባቸው ታፔላ ሳይሆን የሚሰጡት አገልግሎት ነው:: ቀላል የመመርመሪያ መሳሪያዎች እንኳን በሌለበት የጤና አገልግሎት ተስፋፍቷል ማለት እራስን ከማታለል ተለይቶ አይታይም:: በውሃ፣ ስልክ እና መብራት በኩልም ያለው የጥራት ችግር ከላይ ከተጠቀሱት የሚለይ ጉዳይ አይደለም:: የአገሪቷ ብሎም የአህጉሪቷ ዋና ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ እንኳን የነዚህ መሰረተ ልማቶች የጥራት ችግር እጅግ አሳሳቢ ነው:: ያልተቆራረጠ የንጹህ ውሃ፣ የስልክ እና የመብራት አገልግሎት ተደራሽነት ምን ያህል ነው? የተዘረጋው ኔትዎርክ መሸከም ከሚችለው በላይ የስልክ መስመሮችን በመሸጥ ዘርፉ አድጓል ማለት ምን ያህል ተገቢ ነው? የሚሉ እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ማግኘት ከቻሉ እድገታችን ወዴት እና እንዴት እንደሆነ በቀላሉ መረዳት እንችላለን::

በእኔ እምነት ከመሰረተ ልማት ባልተናነሰ መልኩ የእድገት መለኪው የህዝባችን የኑሮ ሁኔታ ምን ያህል ተለውጡዋል የሚለው መታየት አለበት:: እውነቱን ለመናገር የህዝባችን የኑሮ ሁኔታ በእጅጉ ተለውጧል:: ድሮ ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ የማያሳስበው ሕዝብ በአሁኑ ወቅት ቤት እና ልብስ የቅንጦት እየሆኑ የምግብ ፍላጎቱን እንኳን በዝቅተኛ ሁኔታ ማሟላት ተስስኖታል:: 85% ነው የሚባለው ገበሬው ሕዝባችን እንኳን እራሱን መመገብ ተስኖታል:: ይህ ገበሬ አሁንም ከዝናብ ጠባቂነት እና ከኋላቀር አስተራረስ ዘዴ ሊወጣ አልቻለም:: ለግብርና የተመቸ መልከዓ ምድር እና ለም አፈር እንዲሁም ለመስኖ የሚውሉ በቂ ወንዞች ያሏት አገር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በሚሄድ በምግብ እራስን ያለመቻል ችግር ውስጥ ስትዳክር ዓለም በአግራሞት እየተመለከታት ይገኛል:: ታዲያ ይህንን ኋላቀር የሆነ የግብርና ስርዓት ካለበት ችግር ቀና ማድረግ ካልተቻለ እድገቱ ምኑ ላይ ነው? ያለንን ለም መሬቶች ከገበሬው እየነጠቅን ገበሬውን ከቀዬው እያፈናቀልን የምናስመዘግበው እድገት ምን ያህል ሕዝባችንን ተጠቃሚ ያደርገዋል? በእኔ አመለካከት የአንድ አገር እድገት በገነባችው መሰረተ ልማት ከሚገለጸው በላይ በእጅጉ ራስን በመቻል ይገለጻል:: ምን ያህሉ ህዝባችን በምግብ እራሱን ቻለ? ከውጪ መንግስታት የምናገኘው የምግብ እና የገንዘብ እርዳታ በምን ያህል ቀነሰ? ከዚህ ቀደም የወሰድናቸው ብድሮችን የመክፈል አቅማችን በምን ያህል ጨመረ? እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች ካለፉት የሃገሪቱ መንግስታት ጋር ብቻ ሳይሆን ቀድሞ በድህነት ሰንጠረዥ ውስጥ አብሮ ስማችን ሲፃፍልን ከነበሩ የአፍሪካ፣ የኤሲያ፣ የአውሮፓ እና የአሜሪካ አገሮች ጋር ራሳችንን ማወዳደር ይጠበቅብናል:: እድገታችን በጠንካራ መሰረት ላይ መገንባት ካስፈለገ በሌሎች አገሮች ችሮታ ለይ የተመሰረተውን የምግብ ዋስትናችንን በበቂ ሁኔታ መመለስ እና ማረጋገጥ ከሁሉም ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው:: አበባ ወይም የኤሌክትሪክ ሀይል ሸጦ በሚገኝ የውጪ ምንዛሪ ስንዴ እና ሩዝ እየገዙ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ሙከራን ነዳጅ ሸጠው ስንዴ እና ሩዝ በመግዛት የህዝባቸውን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት ለሚሞክሩ የአረብ አገራት ትተን በቀጥታ በአገራችን ምርት የምግብ ዋስትናችንን ለማረጋገጥ መስራት ይኖርብናል:: አለበለዚያ ግን በአገራችን ላለው የዋጋ ንረት የዓለም አቀፉን የምጣኔ ሃብት አለመረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላበረከተ የሚለው አሳማኝ ያልሆነ ምክንያት ሁልጊዜ መስማታችን አይቀሬ ነው::

ወደ ውጪ ከምንልካቸው ምርቶች (export commodities) በላይ ሊያሳስበን የሚገባው ነገር ከውጪ የምናስገባቻውን ነገሮች (import commodities) በሃገር ውስጥ ለመተካት (import substitution) የምናደርገው ጥረት ነው:: የውጪ ምንዛሪ (foreign currency) ለማግኘት እያልን ከምንልከው ቆዳ ያገኘነውን የውጪ ምንዛሪ መልሰን ከቡና ያገኘነውን የውጪ ምንዛሪ ጨምረን ጫማ እና ሌሎች የቆዳ ውጤቶችን የምንገዛበት ከሆነ እንዲሁም ከአበባ እና የቅባት እህሎች ያገኘነውን የውጪ ምንዛሪ መልሰን ለስንዴ እና ዘይት የምናውጣው ከሆነ መቼም ከውጪ ምንዛሪ አዙሪት አንወጣም:: ሁል ጊዜም በሃገራችን ምርት ፍላጎታችንን ለማሟላት የምናደርገው ጥረት ወደ ትክክለኛ የእድገት መንገድ ያደርሰናል:: ነገረ ግን የህዝባችንን ፍላጎት (domestic demand) ሳናሟላ ወደ ውጪ ከምንልካቸው ምርቶች የምናገኘውን የውጪ ምንዛሪ መልሰን ያጎደልናትን የህዝብ ፍላጎት (demand and supply gap) ለመሙላት ተጨማሪ የውጪ ምንዛሪ ይዛብን ትሄዳለች:: ስንዴ ሸጦ ስንዴ ወይም ዱቄት ከመግዛት ስርዓት መውጣት ይኖርብናል:: ላለፉት ሁለት አስርት አመታት እንኳን ይህንን ለማሟላት ቢሞከር ኖሮ የህዝባችንን የምግብ ጥያቄ በሌሎች አገሮች መልካም ፈቃድ ላይ ተንጠልጥሎ ባልቀረ ነበር::

ከሁሉም በፊት ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባን ጉዳይ የህዝባችንን መሰረታዊ ፍላጎቶች ከማንም ጥገኝነት ነጻ በሆነ መልኩ ማሟላት ነው:: የዚህን ታላቅ እና ኩሩ ህዝብ ታላቅነት እና ኩራት መመለስ ከፈለግን ከአሳፋሪው የምግብ ልመና መላቀቅ ይኖርብናል:: ሌላው የእድገታችን ትሩፋት መሆን የነበረበት እና ሳይሆን የቀረው ከሃገሪቷ በተለያዩ መንገዶች የሚሰደደው ህዝቧ መቀነስ ነበር:: በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ መንገዶች የሚሰደደው ህዝባችን ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ ነው:: ይህ የሚታይ እውነታ ስለሆነ እድገቱ የህዝብን ተጠቃሚነት አላረጋገጠም ለማለት እንደ አንድ ማሳያ መሆን ይችላል::

ሕዝባችን በእቃ መጫኛ ኮንቴነሮች ሳይቀር በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትሮች ለመጓዝ የሚያደርገው ሙከራ ምክንያት የባዕድ አገር ናፍቆት ይሆን? ለመሰደድ በሚሞክሩበት ወቅት በኮንቴነር ታፍኖ፣ በበረሀ ሃሩርና ውሃ ጥም ተቃጥሎ፣ በባህር ሰጥሞ እንዲሁም በድንበር ጠባቂዎች ተደብድቦ እና ተሰቃይቶ መሞት የተለመደ ቢሆንም ሕዝባችን ግን አሁን ካለበት አሰቃቂ ድህነት ለመውጣት ብቸኛው አማራጭ ስደት ማድረጉን አጠናክሮ ቀጥሎበታል:: በስደት የሞተ ጎረቤቱን ሳልስት እንኳ ሳይደርስ ለስደት ሻንጣውን የሚሸክፍበት አገር አለች ከተባለ የኛው አገር እማማ ኢትዮጵያ የመሆን እድሏ ሰፊ ነው:: ከኢትዮጵያ ተነስቶ በሱዳን እና ሊቢያ በረሃ አቋርጦ አውሮፓ ለመግባት የሚጓዘው የተማረው የሃገሬ ሰው በሃገሩ ስርቶ ድህነትን በእውቀት ጥይት ማንበርከክ ቢያቅተው እና የቤተሰብ ድህነት ቢያንገበግበው አውሮፓ ተስፋ ሰንቆ ድህነትን በ “Euro” ጥይት ሊሞክረው የቆረጠ እንጂ የሰላም ተጓዥ አይመስለኝም:: ታዲያ አገሪቷ ላለፉት አመታት ባለ ሁለት አህዝ እድገት አስመዘግባ ከሆነ ይህ በዚች አገር ከመኖር በስደት መኖር ወይም መሞት ይሻላል ብሎ የሚሰደደው ወገኔ በባእድ ሃገር ናፍቆት ምክንያት ይሆን? ምሁራኖቻችንስ ለትምህርት ልከን የማይመለሡት የሰው አገር ተመችቷቸው ይሆን?

በመጨረሻም የሃገር እድገት ማለት የድንጋይ ንጣፍ ወይም ቁልል ማለት አይደለም:: የአገር እድገት ማለት የሕዝብ እድገት ማለት ነው:: ከመንገድ እና ከህንጻው በፊት የህዝብ የመኖር ህልውና መረጋገጥ አለበት:: ይህንን ያህል ኪሎ ሜትር መንገድ ሰራን፣ ዩኒቨርሲቲ ገነባን፣ የዚህን ያህል ህዝብ የመብራት እና ስልክ ተጠቃሚ አደረግን፣ የዚህን ያህል ሜጋ ዋት የመብራት ሀይል ማመንጫ ገነባን እና የመሳሰሉት ከህዝብ በኋላ የሚመጡ ናቸው:: በርሀብ የሚሞት ህዝብን የመብራት ተጠቃሚ ለማድረግ መሞከር ቀብርን ከማዳመቅ የዘለለ ጥቅም የለውም:: እንዲሁም በዳቦ እጦት የሚንገላታ ህዝብን የስልክ ተጠቃሚ ለማድረግም መሞከር መርዶ ከመንገሪያነት የዘለለ ፋይዳ አይኖረውም:: በብርሃን ውስጥ በረሃብ የሚሰቃይን ህዝብ እያዩ ከመሠቃየት እና ከመዋረድ በጨለማ ጠግቦ የሚድር ህዝብ በብዙ ሺህ እጥፍ ይሻላል:: የምግብ ፍላጎቱን የተሟላ ህዝብ ጤንነቱ የተጠበቀ ነው:: አክሱምን፣ ላሊበላን፣ ፋሲልን የገነባ ትውልድ ጮማ እየቆረጠ እና ወተት እየተጋተ ያደገ ትውልድ ነው:: ያ ትውልድ መንገድ፣ ሆስፒታል እና ዩኒቨርሲቲ አልነበረውም:: ነገር ግን ያለመንገድ ይጓዛል፣ ያለ ሆስፒታል ጤናውን ይጠብቃል:: እንዲሁም ያለ ዩኒቨርሲቲ ዓለም በአግራሞት የሚመለከተውን ይህ በዩኒቨርሲቲ የተጥለቀለቀ ትውልድ የማይሰራውን ብቻ ሳይሆን የማያልመውን ሥራ ይከውናል:: ስለዚህ ከመሰረተ ልማት ግንባታ በፊት የህዝብ ግንባታ ይቀድማል:: ህዝብ ደግሞ በሬንጅ፣ በኮብልስቶን እና በብሎኬት አይገነባም:: የህዝብ አቅም በተመጣጠነ ምግብ ነው የሚገነባው:: ሕጻናትን እንኳን በወተት፣ በእንቁላል፣ በፍራፍሬ፣ በአትክልት እና በስጋ ማሳደግ በማቻልበት በዚህ ወቅት እንዴት ጤናማ ትውልድ መፍጠር ይቻላል? ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነጋ ጠባ ህጻናትን የተመጣጠነ ምግብ መግቡ እያለ በቴሌቪዥን ይለፈልፋል:: ሕዝቡ ይህንን መች አጣው? ያልገባኝ ግን የማይቀመሰው ወጪ በማን ይሆን? የሚያስለፈልፋት እና የሚለፈልፉት በብዙሀኑ ህዝብ እና በእነርሱ መሃከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቀው ያዩት አይመስለኝም:: ገበሬ መስሎ ማስታወቂያ መስራት ወይም ማሰራት እና ገበሬ መሆን የተለያየ ነው:: እንቁላል ከምግብነት አልፎ ሕንጻ የተገነባበት እንዲሁም ውሃ ለጠማው መንገደኛ ወተት የሚሰጥበት ጊዜ አልፏል:: አሁን በክፍያ እንኳ አልተቻልም:: ለነገሩ እነርሱ ወተት ከየት ይገኛል ቢባሉ ከፍሪጅ ከሚለው የሕብረተሰብ ክፍል ሊሆኑ ስለሚችሉ ወተት ለማግኘት ፍሪጃቸውን መክፈት ብቻ በቂ ነው:: የሳምንት ሰው በለን!!

> **ከሁሉም በፊት ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባን ጉዳይ የህዝባችንን መሰረታዊ ፍላጎቶች ከማንም ጥገኝነት ነጻ በሆነ መልኩ ማሟላት ነው:: የዚህን ታላቅ እና ኩሩ ህዝብ ታላቅነት እና ኩራት መመለስ ከፈለግን ከአሳፋሪው የምግብ ልመና መላቀቅ ይኖርብናል:: ሌላው የእድገታችን ትሩፋት መሆን የነበረበት እና ሳይሆን የቀረው ከሃገሪቷ በተለያዩ መንገዶች የሚሰደደው ህዝቧ መቀነስ ነበር:: በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ መንገዶች የሚሰደደው ህዝባችን ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ ነው:: ይህ የሚታይ እውነታ ስለሆነ እድገቱ የህዝብን ተጠቃሚነት አላረጋገጠም ለማለት እንደ አንድ ማሳያ መሆን ይችላል::**

# በፖለቲካውም ማለባበስ ይቁም



ታምራት ታረቀኝ

መድሀኒት አልባው ቀሳፊ በሽታ ኤድስ በሀገራችን መግባቱ በታወቀበት ወቅት የነበረው አመለካከትና የተያዘው መንገድ በጣም መጥፎ እንደነበረ እሙን ነው፡፡ በሽታውን ለመግታት ተብሎ የሚሰራው የሚነገረው ሁሉ በእውቀት ሳይሆን በስሜት የሚመራ ታስቦና ታቅዶ ሳይሆን በሆይ ሆይታ የሚከናወን ነበርና በሽታውን ለመከላከል ተብሎ የተሰራው ሁሉ ለበሽታው መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ቆም ብሎ ማሰብ ሲጀመር በመፍራትም በመጥላትም በመደበቅም ወ.ዘ.ተ አስተማማኝ መፍትሄ እንደማይገኝ ታወቀና ‹‹ማለባበስ ይቅር!›› ተብሎ ተዜመ፡፡ በበሽታው የተያዙትም ‹‹በእኛ ይብቃ ትውልድ ይዳን!›› ብለው መጋረጃውን ገልጠው አደባባይ ወጡ፡፡ እናም በመፍራት ሳይሆን አውቆ በመጠንቀቅ በማለባባስ ሳይሆን ገላልጦ በመነጋር መፍትሄ ተገኘለት፡፡

የፖለቲካችንንም ጉዞ ቆም ብለን ብናየውና ሰከን ባለ መንፈስ ብንገመግመው መፈራራት፣ ጥላቻ፣ ድብቅነት፣ ሴራ ወ.ዘ.ተ የተጠናወተው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ‹‹አድሮ ቃሪያ›› ይሉት አይነት እየሆነ ያለው፡፡ ስለሆነም ማለባበስ ይቅር ብለን፣ እውነትን መሰረት አድርገን፣ ለውጥን ዓላማችን አድርገን፣ ከጥላቻ ግርዶሽ ወጥተን ደፈር ብለን መነጋገር ካልቻልን የትናንቱ ዛሬ እየተደገመ ለነገ ስንቅም ተስፋም ሳንይዝ መጓዛችን ይቀጥላል፡፡

ፖለቲከኞቻችን (በየትኛውም ሰፈር ያሉት) በአደባባይ የሚናገሩትን፣ በመግለጫ የሚያስተላልፉትን፣ በመገናኛ ብዙን የሚደሰኩሩትን፣ እንዳለ ከተቀበልን ከእውነት በጣም እንርቀን የመፍትሄው ሳይሆን የችግሩ አካል እንሆናለን፡፡ የሚናገሩት እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር ብለው ሳይሆን የፍላጎታቸውን መሳካት፣ የጥቅማቸውን መጠበቅ፣ የወንበራቸውን መርጋት፣ ወ.ዘ.ተ እያሰቡ በመሆኑ ንግግራቸውን ከድርጊታቸው እየመዘንን፣ ያለባበሱትን እየገለጥን፣ እውነቱን ከሀሰቱ እያነጠርን ማየት ካልቻልን አውቀንም ሆነ ሳናውቅ የእነርሱ እኩይ ድርጊት ተባባሪ በመሆን የምንሻውን ለውጥ እየናፈቅን እንኖራለን፡፡ ስለሆነም በፖለቲካውም ማለባበስ ይቁም ልንል ይገባል፡፡

ይህን ብለን ከተነሳን ብዙ የሚነሱ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከእነዚህም በተለይ የምርጫ ዋዜማን እየጠበቀ የሚነሳው የፓርቲዎች የመተባበር ብሎም የመዋሀድ ጥያቄ አንዱ ነው፡፡ የፓርቲዎች ህብረት ወይንም ውህደት በእምነት ሳይሆን በስሜት ይነገራል፣ በጥናትና በእቅድ ሳይሆን በሆይ ሆይታ ይሞከራል፣ ለሰላማዊ ትግሉ አንድም ውጤት ሳያስመዘግብ ይሰነካከላል፡፡ በመሆኑም ወይ አንድ ሁለት ጠንካራ ፓርቲ ሳናይ ወይ ጠንካራ ህብረት ወይንም ውህደት ሳይፈጠር ነገሩ ሁሉ የእንቧይ ካብ እየሆነ ሁለት አስርት ዓመታት ተቆጠሩ፡፡

እንደምንም ለመቀናጀት የቻሉት የአላቻ ጋብቻ ‹‹ቆይ ብቻ! ቆይ ብቻ!›› እንዲሉ በአብሮነት ቆይታቸው ከአንድነታቸው ይልቅ እየተጠባበቁና የጎሪጥ እየተያዩ መሄዳቸው ይልቃል፣ ተነጋግረው ከመስረታቸው ይልቅ መተማማታቸውና መወነጃጀላቸው ሚዛን ይደፋል፤ ለይቶላቸው የአብሮነት ገመዳቸው ሲበጠስ ደግሞ መዘላለፋቸው ራስን ነጻ አድርጎ ሌላኛውን ጥፋተኛ የማድረግ መካሰሳቸው ይከፋል፡፡ ከአራት አመት የድብስብስ ጉዞ በኋላ ሰሞኑን የተሰማው መድረክ አንድነትን አገደ የሚለው ዜና ለዚህ የቅርብ ጊዜ ማስረጃ ነው፡፡

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበርነታቸውን በቅርቡ የለቀቁት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ከሪፖርተር ጋዜጣ ጥር 18/2006 ዕትም ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ከመድረክ መስራችነታቸውና ከአምስት አመት ልምዳቸው ተነስተው ስለ ፓርቲዎች ውህደት የተናገሩት በጣም ትክክል ነው፡፡ «…አንድ ሁኑ ይባላል እንዴት ተደርጎ ነው በአንድ ጊዜ መዋሀድ የሚቻለው? ፍቅር እንኳን ቀስ ብሎ በመላመድ ነው ወደ ትዳር የሚያመራው፡፡ ሁሉም ነገር በሂደት ነው…» በማለት ነበር ፓርቲዎች አሁን ባሉበት ደረጃ ውህደት መፈጸም የማይችሉ መሆኑን በግልጽ የተናገሩት፡፡ አለባብሶ እያረሱ በአረም መመለስ ካልተፈለገ በስተቀር እውነቱ ይህ ነው፡፡ ያለ እምነት ያለ በቂ ውይይትና ዝግጅት ህብረትም ሆነ ውህደት ቢፈጸም ደግሞ ተደጋግሞ እንደታየው የአንድ ሰሞን የፕሮፓጋንዳ ሞቅታ ይፈጥር ለሰዎቹም ገንዘብ ያስገኝ ካልሆነ በስተቀር ለለውጥ የሚያበቃ ትግል ለማድረግ የሚያስችል አቅም አይፈጥርም፡፡ ምክንያት በድቡሽት ላይ የቆመ ነውና፡፡

እውነታው ይህ ቢሆንም እውነት የአጭር ጊዜ የፕሮፓጋንዳም ሆነ የኢኮኖሚ ጥቅም የማስገኘት አቅሟ ደካማ በመሆኑ ከእውነት ይልቅ በስሜት መጓዝ፣ ከሀገራዊ ለውጥ ይልቅ የፓርቲ መሪ እየተባሉ መኖር ምርጫ ሆኖ ዛሬም ስለ ምርጫ 2007 ሊመከር፣ ሊሰራ በሚገባበት ወቅት ውህደት ይወራል ያጨቃጭቃል፣ ያፈራርጃል፡ አሳዛኝ!

ለአመታት በተደጋጋሚ የተጻፈ የተነገረውን ትተን የቅርቡን የዶ/ር ነጋሶን የተሞክሮ ምስክርነት ይዘን ብንነሳ የምንገነዘበው ውህደት ለመፍጠር የፓርቲ መሪዎች እያወሩ ሳይሆን እየሰሩ በተግባር እየተፈታተኑ፣ በአደባባይ ከሚናገሩት በስተጀርባ ያለው ማንነታቸው፣ በፕሮግራማቸው ካሰፈሩት ዓላማቸው በተጓዳኝ ያለው ፍላጎታቸው፣ የተከደነው ተከፍቶ የተለባበሰው ተገላልጦ መታየት መታወቅ ብሎም መተዋወቅ ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ለእኔ እንደሚገባኝ ዶ/ር ነጋሶ ሂደት ያሉት ይህን መሰል ተግባራት የሚፈጸሙበት ነው፡፡ አለበለዚያ ሰው አንድ መሆናችንን ይፈልጋል መሆን ባንችልም መስለን በመታየት የፕሮፓጋንዳ ድጋፍ የኢኮኖሚ እርዳታ በማግኘት ‹‹እድሜአችንን ለማራዘም እንችላለን!›› በሚል የሚታሰብ የሆይ ሆይታ ጥምረትም እንበለው ውህደት ‹‹የእነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ!›› ይሉት አይነት ከመሆን ሊዘል አይችልም፡፡

በጣት የሚቆጠሩ የአንድነት አመራር አባላት በጥናት ሳይሆን በስሜት፣ ለዘላቂ ግብ ሳይሆን ለአጭር ግዜ ፍላጎት አንድነትን ወደ መድረክ ለማስገባት ሲጣደፉ የተሰጡ አስተያየቶችን ሊያዳምጡ፣ የተሰነዘሩ ምክሮችን ሊቀበሉና ስሜታቸውን ሳይሆን እውነታውን በመገንዘብ ቆም ብለው ማሰብ ቢችሉ ኖሮ አምስት ዓመት በከንቱ ባልባከነ ነበር፡፡ ዛሬ የአጋጅና ታጋጅ ድራማም ባልተፈጠረ ነበር፡፡

የሚያሳዝነው ዛሬም ገላልጦ የማየቱ ድፍረት ወይም ፍልጎት ጠፍቶ ማለባበሱ መቀጠሉ፣ ወጣት አዛውንት ሳይባል የዚሁ መንገድ ተከታዮችም መብዛታቸው ነው፡፡ በራስ እግር ቆሞ፣ በራስ ዓላማና እምነት ጸንቶ ራስን ማጠናከር ትግሉንም መምራት ሲያቅት የውህደት ፕሮፓጋንዳ መደበቂያ ይሆናል፡፡ ለእድሜ ማራዘሚያ መድሀኒትነት ይፈለጋል፡፡ እውነታው ግን ዶ/ር ነጋሶ ያሉት ነው፣ ውህደት ዛሬ አይሆንም አይቻልም፡፡ ወደዛ የሚያመራን ጥርጊያ መንገድ የማመቻቸት ስራ ግን ዛሬ መጀመር ይቻላል ብቻ ሳይሆን ዛሬውኑ መጀመር ነበረበት፡፡ ነገር ግን ትኩረቱ ሀገራዊ ለውጥ ለሚያስገኝ ተግባር ሳይሆን ራስን በተቀዋሚ መሪነት ማቆየት ሆነና ከፈረሱ ጋሪውን እያስቀደሙ መደነቃቀፉና መደነባበሩ ቀጥሏል፡፡

ጥምረትም ይባል ውህደት፤ ቅንጅትም ይባል ግንባር ለመመስረት የሚያበቃ መጠናናት ለማካሄድ፣ ከመጋረጃው ጀርባ ዘልቆ ለመተዋወቅ፣ ለትግሉ ያለን ጽናት ለመፈታተሽ ወ.ዘ.ተ ምርጫ 2007ን መጠቀም ይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን በምርጫ 2002 ያገኘውን የ99.6 በመቶ ውጤት ለማስጠበቅ ኢህአዴግ ሌት ተቀን እየሰራ ተቀዋሚዎቹ ግን ካልተዋሀድን አይሆንም፣ የለም ውህደት ለመፈጸም የሚያስችል ሁኔታ ላይ አይደለንም በሚል ሲነታረኩ ይሰማል፡፡

የሀገራችንን አጠቃላይ ሁኔታና የተቀዋሚዎቹን ማንነትና የትግላቸው እንዴትነት በማጤን ሳይሆን እንደው በስሜት በአንድ ቀን ጀንበር ለውጥ ማየት የሚፈልገው ወገንም የተዋሀዱ ጩኸቱን ቀጥሎበታል፡፡ ስለ መወሀድ የሚያወሩት ፖለቲከኞች በእምነት ይሁን በእውነት መሆኑን ሳይረዳ ያደንቃል፣ ደግፎ ያጨበጭባል፣ ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ውህደት ለመፍጠር የሚያበቃን አይደለም ያሚሉትን ያወግዛል፣ ይኮንናል፡፡ በዚህ ስክነትም ማስተዋልም በጎደለው በስሜት በሚነዳ አመለካከት ለውጥ ይገኛል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

ማለባበሱ ይቁምና መጋረጃውን ገልጠን እውነቱን ለመጋፈጥ ከደፈርን የምናገኘው ተጨባጭ እውነት ከአምስት አመት ቆይታ በኋላ ከተግባር ተምረው ዶ/ር ነጋሶ የመሰከሩትን ውህደት ዛሬ አይቻልም አይሆንም የሚለውን ነው፡፡ ስለሆነም ውህደትን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ፣ ለእድሜ ማራዘሚያነትና ለማደናገሪያነት ማዋሉ ይቁምና፣ ምርጫ 2007ን ለዚህ መፈታተኛና መፈታተሻ እናውለው፡፡

ለምርጫ 2007 ውጤታማነት፣ ለውህደትም መንገድ ጠራጊነት ውይይት

ምርጫ 2007 የቀሩት 14 ወራት ያህል ናቸው፡፡ ይህም በጣም አጭር ጊዜ ነው፡፡ ከኢህአዴግ የጠለፋ ፖለቲካ ራሳችንን ለመጠበቅ በየጓዳችን እየሰራን ነው ካላሉ በስተቀር በተቃዋሚዎች ሰፈር ስለምርጫ የሚደረግ ዝግጅት አይታይም፡፡ ሰላማዊ ትግል ደግሞ ከምርጫ ውጪ ለድል ሊበቃ አይታሰብም፡፡ ስለሆነም ቢያንስ ከነድክመታቸውና የዴሞክራሲ ባይተዋርነታቸው ሕብረተሰቡ በተቀዋሚነት የሚያውቃቸው ፓርቲዎች ውህደት፣ ህብረት፣ አብሮ መስራት፣ የሚሉትን የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ጩኸታቸውን ገትተው ሀያ አመት ትግል ተካሂዷል፣ ለውጥ ናፋቂ አያሌ ዜጎች የሕይወትም የአካልም መስዋዕትነት ከፍለዋል፣ ውጤት ግን የለም፣ እኛም ተቀዋሚ ከመባል አልፈን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አዎንታዊ ሚና ለመጫወትና ስንዝር ለውጥ ለማስመዝገብ አልቻልንም ለምን ብሎ፣ አጀንዳ ቀርጾ ዛሬውኑ ውይይት መጀመር ተገቢ፣ አስፈላጊና የሚቻልም ነበር፡፡ ግን በሚያሳዝን መልኩ የምናይ የምንሰማው የተለመደ የውህደት ጩኸት ውኃ ወቀጣ ነው፡፡

ትግሉ ለሀያ ዓመታት ተካሂዶ ለውጤት ያልበቃው በምርጫ 97 የተገኘውንም ውጤት ማስከበርም መድገምም ያልተቻለው፣ ሕብረተሰቡ በሚከፈለው መስዋእትነት መጠን የሚሻውን ለውጥ እንዲያገኝ ማድረግ ያልቻልነው ለምንድን ነው ብሎ ከማለባበስ ወጥቶ በድፍረት የሀሰት ካባ አውልቆ ጥሎ በእውነትና በወኔ ተሞልቶ መነጋገር መቻል አንድም በምርጫ 2007 ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል ሁለትም ማን ከማን ጋር እንዴት፣ መቼና በምን ሁኔታ ጥምረት፣ ግንባር፣ ውህደት መፍጠር እንደሚችል ለመተዋወቅም ለመጠናናትም ለመወሰንም ያስችላል፡፡

በምርጫ 2007ም ቢቻል አብላጫ ወንበር አግኝቶ መንግሥት ለመመስረት፣ ካልሆነም ሕግ ለማስለወጥና ውሳኔ ለማስቀልበስ የሚያበቃ ወንበር ለማግኘት፣ ይህም ካልተቻለ የኢህአዴግን የ99.6 በመቶ ውጤት ለመቀየር በየግል ምን፣ በጋራስ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል ምንስ ማድረግ እንችላለን ብሎ መነጋገር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለግል ሥልጣን ሳይሆን ለሀገራዊ ውጤት ለሚያልሙ የሚቸግር አይደለም፡፡ ስለሆነም ወቅቱ በሚጠይቀው መጠን ትግሉን ለመምራት ያለመቻልን ድክመትም ሆነ የጽናት ጉድለትን በውህደት አጀንዳ ለመሸፋፈን የሚደረገው የፕሮፓጋናዳ ጩኸት ይቁምና በግልጽ በእውነትና በማስረጃ ስለ ትናንት ችግር ስለ ዛሬ ድክመት ስለ ነገ ውጤታማነት ውይይት ዛሬና አሁን ይጀመር፡፡

ህብረት እንበለው ግንባር፣ ቅንጅት እንበለው ውህደት እንዲሰምር የመሪዎች ፍቅር ሳይሆን የፓርቲዎቹ ዓላማ ነው ወሳኙ፡፡ የሚተባበሩበት መርህ ግልጽ ሆኖ መታወቁ ነው መሰረቱ፡፡ እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሚሰሩ የሚፈጽሙት ውል ነው ማሰሪያው፡፡ ራስን ለሥልጣን ማብቃትን በሚያልም ከራስ በላይ ነፋስ አስተሳሰብ ሳይሆን በእኔ መስዋዕትነት ትውልድ ተሻጋሪ አስተማማኝ የዴሞክራሲ መሰረት ማኖር በሚል የጸና እምነት የሚመራ ትግል ነው የሚያስፈልገው፡፡ በተግባር የሆነውና አሁንም የሚታየው ግን እውነቱ ለአደባባይ ቢበቃ ፍልጎታችንን ከወዲሁ ያመክንብናል፣ በጨዋታው ተሸናፊ ያደርገናል፣ ሥልጣናችንን ያሳጣናል ወ.ዘ.ተ በሚል ስጋት እያለባበሱ ስለ ውህደት እየደሰኮሩ መጓዝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትናንትም አልበጀ፣ ዛሬም እያዋጣ አይደለም፣ ለወደፊትም አይጠቅምምና ማለባበሱ ተወግዶ የማስመሰያው ጭንብል ወልቆ፣ የፕሮፓጋንዳው ዋይታ ረግቦ የሀያ አመት ትግል ለውጤት ያልበቃው ለምንድን ነው፣ በምርጫ 2007 ውጤት ለማስመዝገብ በየግል ምን በጋራስ ምን እናድርግ የሚል ውይይት ዛሬውኑ ይጀመር፡፡

ነጻ ፕሬስ የሚባሉት የህትመት ውጤቶችም ለፓርቲ መሪዎች ካላቸው ፍቅር ወይንም ጥላቻ ተነስተው ለሚወዷቸው ፓርቲዎቹ ከሚገኙበት ተጨባጭ ሁኔታ በእጅጉ የራቀና የተቃረነ ሙገሳና ውደሳ ከማቅረብ፣ በሚጠሉዋቸው ላይም ያልተገባ ትችትና ማጥላላት ከመጻፍ ከስሜት ይልቅ ለእውነት ቆመው ጥቅምን ሳይሆን የሙያውን ሥነ ምግባር ጠብቀው በሀቅ ላይ ተመስርተው እውነቱን ቢጽፉ ለፓርቲዎቹ በየግል መጠናከር፣ በሂደትም ለጠንካራ ህብረትም ሆነ ውህደት እውን መሆን በጎ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ እናም በፖለቲካውም ‹‹ማለባበስ ይቁም!›› ብለን ከተነሳን እያለባበስን ከውጤት ያራቀነውን ፖለቲካ ወደ ውጤት ጎዳና እንዲያመራ እናደርገዋለን፡፡ ስለሆነም በፖለቲካውም ማለባበስ ይቁም ብያለሁ፣ ሌሎችም የምትሉትን በሉና እንወያይበት፡፡

**የሀገራችንን አጠቃላይ ሁኔታና የተቀዋሚዎቹን ማንነትና የትግላቸው እንዴትነት በማጤን ሳይሆን እንደው በስሜት በአንድ ቀን ጀንበር ለውጥ ማየት የሚፈልገው ወገንም የተዋሀዱ ጩኸቱን ቀጥሎበታል፡፡ ስለ መወሀድ የሚያወሩት ፖለቲከኞች በእምነት ይሁን በእውነት መሆኑን ሳይረዳ ያደንቃል፣ ደግፎ ያጨበጭባል፣ ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ውህደት ለመፍጠር የሚያበቃን አይደለም ያሚሉትን ያወግዛል፣ ይኮንናል፡፡ በዚህ ስክነትም ማስተዋልም በጎደለው በስሜት በሚነዳ አመለካከት ለውጥ ይገኛል ተብሎ አይጠበቅም፡፡**

# የአስር ሳንቲም ኢኮኖሚ. . .

ከ ገፅ 16 የዞረ

አለመጠየቅና ለመብታችን ጥብቅና አለመቆም ነው፡፡ ዛሬ ቀበሌ ላይ የመናገር መብትህን የነፈገህ የቀበሌ አስተዳዳሪ ዝም ከተባለ የሐገር መሪም ሆኖ ጨቋኝና የለየለት አምባገነን መሆኑ የታወቀ ነው፤ ዛሬ ጨቋኝነቱን ቀበሌ ላይ የነገርነውና የታገልነው ሰው ሀገር የመምራት ዕድሉን አግኝቶ ስልጣን ላይ ቢወጣ የህዝብን ጉልበት የተረዳ ለመሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ እናም፣ የእኛ ለመብቶቻችንና ለገንዘባችን ቸልተኛ መሆን አምባገነንና ስግብግብ መሪዎችን ለመፍጠራችን እማኝ ነው፡፡ የመብት ትንሽ የለውም፤ መብት የክበር ጉዳይም ነው፡፡ ስንደፈር በትንሹ ነው፣ በትልቁ ነው ልንል አንችልም፡፡ ጭብጡ ያለው መርሁ ላይ ነው፡፡ መብቱን በእንዝላልነት አሳልፎ የሰጠ ሰው መልሶ ሲጠይቅም አያምርበትም፡፡

# ‹‹እኛን ካልመረጣችሁ...

ከ ገፅ 4 የዞረ

የትኛው አካባቢ ላይ ነው የሚል ጥናትን መሰረት ያደረገ መደምደሚያ መድረስ ችለናል፡፡ እግረ መንገዳችንንም እያንዳንዱ ከተማ ላይ የአመራር ክህሎት ስልጠና፣ የህዝባዊ ስብሰባ የምናደርግባቸውን ቀናት እየወሰንን ነው የመጣነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ዞን ተዘጋጅቶ የሚጠብቅበት፣ የሙያ ክህሎት ስልጠና የሚወስድበት፣ ህዝባዊ ሰብሰባ የሚያደርበትን ቀን እያሳወቅን፣ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የስብሰባ አዳራሽ ሁሉ እየፈለግን እያገኘን ነው የመጣነው፡፡ ለምሳሌ አርባ ምንጭ ላይ በቀጣይ ሳምንታት የሚደረግ ስብሰባ አለን፡፡ እሱ ላይ አዳራሽ ሁሉ አግኝተን ተነጋግረን ነው የመጣነው፡፡ ይህ የስኬታማነቱ መመዘኛ ነው፡፡

እስር ቤት ስንገባ ሳይቀር እያስተማርን ነው የመጣነው፡፡ አንድ ምሳሌ ልንገርህ፡፡ ደቡብ ላይ፣ አቶ አየለ ሀሚሶ የተባለ የአዋሳ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ባልታወቁ ሰዎች ተደበደቡ ተብሎ አስራ ስምንት ሰዎች ያለ ምንም ፍርድ ታስረዋል፡፡ ለ15 ቀናት ፍር ቤት አልቀረቡም፡፡ 36 ሰው ሶስት በሶስት በሆነች ክፍል ውስጥ ቆሞ ነው የሚያድረው፡፡ መቀመጥም አይችልም በጣም ጠባብ ነው፡፡ ባጃጅ ሾፌሮች ሳይቀር ደብዳቢውን ሸኝታችኋል ተብለው ለ25 ቀን ያህል እየተደበደቡ ታስረዋል፡፡ እኛ ገብተን ይህን መረጃ ሰምተን አንዳንድ እንቅስቃሴ ካደረግን በኋላ አዲስ እስር ቤት ተከፍቶ፣ እስረኞች ተቀንሰው ሌላ ቦታ ማዘዋወራቸውን የነገሩን ከእኛ በኋላ የተፈቱ ሰዎች ናቸው፡፡ ለ15 ቀናት ያህል ያለ ፍርድ የቆዩት ሰዎችም ፍርድ ቤት እንዲቀርቡና ቃል እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡ እስር ቤት ገብተን መረጃውን በማግኘት እንዲህ አይነት ውሳኔዎችን ማስቀየራችን የጉዞው ሌላ ስኬት አድርጌ እወስደዋለሁ፡፡

ነገረ-ኢት፡- 200 ወረዳዎች ከሚገኙ መዋቅሮቻችሁ ጋር መገናኘታችሁን ገልጸውልኛል፡፡ የእነዚህ መዋቅሮች ጥንካሬያቸው እንዴት ነው የሚገለጸው?

አቶ ብርሃኑ፡- መቼስ እኛ ከተመሰረትን ጥቂት ጊዜ ነው ያስቆጠርነው፡፡ ከአንድ አመት ከስድስት ወር እስከ ሁለት አመት በሚሆን ጊዜ ውስጥ ነው እንቅስቃሴ ያደረግነው፡፡ እኔ እንዳየሁት የመዋቅራችን ጥንካሬ ከጠበኩት በላይ ነው፡፡ አንደኛ መዋቅሮች ስላሉንም ነው ይህን ያህል ገንዘብ አውጥተን ለመጎብኘት ውሳኔ ላይ የደረስነው፡፡ በተለይ እኔ በሄድኩበት ደቡብ ክልል ህዝቡ በኢህአዴግ ተማርሮና የሚያምነው ተቃዋሚ ፓርቲ አጥቶ ቁጭ ብሎ እንዳለ ነው የተረዳሁት፡፡ አሁን የምናምነው ፓርቲ መጥቷል ብሎ ጠንካራ መዋቅር ፈጥሮ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ እንደ ወላይታና ሀድያ ያሉ አካባቢዎች ላይ ሳምንታዊ የውይይት ፕሮግራም አላቸው፡፡ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በተለይም ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ደግሞ ሴልና የዩኒቨርሲቲ መዋቅር በመስራት እስከ ገጠር ድረስ በመግባት የፓርቲውን ስራ እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በተለይ ወላይታ ላይ አረካ፣ ቦዲቲ፣ ጎሎሶሬና የመሳሰሉት ወረዳዎች ላይ መዋቅሮች አላቸው፡፡ እኛ ዞኑን ስናዋቅር እነሱ ደግሞ ወደ ወረዳዎች ወርደው በማጠናከር ላይ ናቸው፡፡ ስለሆነም በጣም ጠንካራ መዋቅር እንዳለን ለማየት ችያለሁ፡፡ አሁን የሚቀረን ያንን አካባቢ የፖለቲካ ማዕከል ማድረግ ነው፡፡

ዋናው የመዋቅራችን ጥንካሬ የምንለውና አሁንም የሄድንበት ምክንያት የጠባቂነት መንፈስን ማስቀረት ነው፡፡ ከማዕከል የወረደላቸውን ነገር ብቻ እየጠበቁ፣ እነሱም ወደ ማዕከል ሪፖርት ብቻ እየላኩ የሚቆዩበት ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተቃውሞ ፖለቲካ፣ ህዝባዊ ሰልፍ፣ ህዝባዊ ተቃውሞ ሌሎቹንም ነገሮች እያደረጉ እንዲንቀሳቀሱ ነው የምንፈልገው፡፡ አሁን እሱን ነው የቀረን፡፡ የመዋቅራችን ጥንካሬ ከዚህ በፊት እንደምንለው አንድም ሁለትም መረጃ አቀባይ ሲኖር አባል አለን የምንልበት አይደለም፡፡ ትክክለኛ የሆነ መዋቅር፣ መዋቅራዊ የሆነ፣ በቃለ ጉባኤ የተደገፈ፣ ጊዜያዊ አስተባባሪ የተመረጠበት ነገሮችን ነው ማየት የቻልነው፡፡ ይህ ግን በራሱ ስኬት ነው ማለት አይቻልም፡፡ ብዙ ነገር ይጠብቀናል፡፡ የአመራር ክህሎት ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ከአሁን ቀደም እንደተለመደው ስራም ሆነ ሌሎችን ነገሮች ከዋናው ማዕከል መጠበቅ ሳይሆን በራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በደንብ እንዲሰሩ ማድረግም ሌላኛው ቀጣይ ስራ ነው፡፡

ነገረ-ኢት፡- ሰማያዊ ፓርቲ ከአሁን ቀደም በስፋት የሚታወቀው በሰላማዊ ሰልፍ፣ ቢሮው ላይ አንዳንድ አገራዊ በዓላትን በማክበር ነው፡፡ በቅርቡ ህዝባዊ ስብሰባን በድሬዳዋ ጀምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ወደ ታች ወርዳጅሁ እያደራጃችሁ ነው፡፡ ከአሁኑ የምርጫ ዝግጅት ጀመራችሁ ማለት ይቻላል?

አቶ ብርሃኑ፡- አዎ! እንዲያውም አንዱ ጋዜጠኛ ‹‹የምርጫ ግርግር እንጅ መዋቅሩን ለማጠናከር አይደለም!›› የሚሉ ሰዎች እንዳሉ ገልጾልኛል፡፡ እኛ የምርጫ ስራ ነው የምንሰራው፡፡ የተመሰረትነው በምርጫ ገዥውን ፓርቲ አሸንፎ ስልጣን ለመያዝ ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዷ የምንሰራት ስራ የምርጫ ስራ ናት፡፡ የህዝብ ልጆች ነንና ከህዝቡ ጎን ሆነን እንሰራለን፡፡ ህዝብ ደግሞ በሰላማዊ መንገድ ይህን መንግስት አውርዶ እኛን ይመርጣል ብለን ስለምናምን ነው የምንቀሳቀሰው፡፡ ያች የምርጫ ግርግር የምትባለዋ አይደለችም እንጅ እየሰራን ያለነው የምርጫ ስራ ነው፡፡ ምርጫ ስለደረሰ ብቻ ተነስተን የምናደርገው አይደለም፡፡ እንግዲህ የ2007 ዓ.ም ምርጫ አንድ አመት ከስድስት ወር አካባቢ ይቀረዋል፡፡ እንደሌሎቹ ፓርቲዎች ቢሆንና የምርጫ ግርግር ቢሆን ኖሮ ሶስት ወር ሲቀረው መንቀሳቀስ እንችል ነበር፡፡ አሁን ያን ያህል የሰው ሀይልም ሆነ ገንዘብ ማውጣት አይጠበቅብንም ነበር፡፡ እስካሁን ባለው ተሞክሮ ሶስትና ስድስት ወር ሲቀረው ሁሉም ፖለቲከኛ ሲሆን ይታያልና ያን ጊዜ ወርደን ማደራጀት እንችል ነበር፡፡ እኛ መስራት የምንፈልገው ከዚህ በተለየ መንገድ ነው፡፡ አንደኛ በእውቀት የሚታገል፣ በእውቀት የሚቃወምና የሚደግፍ ሰው መፈጠር አለበት፡፡ ለምርጫ ሲባል ብቻ፤ በምርጫ ሙቀትና ግርግር የሚገባ፣ የሚመርጥና የሚታዘብ ሰው መፈጠር አለበት ብለን አናምንም፡፡ ቀድመን እያንዳንዱን ነገር ማስገንዘብ አለብን ብለን እናምናለን፡፡

ሌላው ነገር ግን፤ የ2007 ምርጫ ጊዜው ሲደርስ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ገዥው ፓርቲ ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር፣ ወደ ምርጫውም ለመግባት መጀመሪያ የተደራጀ መዋቅር ያስፈልጋል፡፡ የተደራጀ መዋቅር ካለ ምርጫ ኖረም አልኖረም ገዥው ፓርቲ ላይ ተጽዕኖ መፍጠር፣ አጀንዳ ማስቀየር ይቻላል፡፡ ስለሆነም አሁንም እየሰራን ያለነው ለዛች ምርጫ ብቻ አስበን አይደለም፡፡

ነገረ-ኢት፡- በደቡቡ ጉዞዋችሁ ደቡብ ህብረት እንቅፋት እንደነበር ገልጸውልኛል፡፡ ከሰማያዊ ጋር የተራራቀ የፖለቲካ አቋም ያላቸው የብሄር ፓርቲዎች ከእናንተ ኢህአዴግን ከመረጡ እነዚህ ፓርቲዎች በሚንቀሳቀሱበት ቦታዎች ልዩነታችሁን እንዴት ነው ልትፈቱ የምትችሉት?

አቶ ብርሃኑ፡- ቅድም ያስቀመጥኩት ነገር አለ፡፡ ጉዳዩ እኛ በግልጽ ያየነው ነገር ነው፡፡ አባላቶቻችን እንደነገሩንም ‹‹እኛን ካልመረጣችሁ ኢህአዴግን ምረጡ፡፡ እከሌ የሚባል ፓርቲን እንዳትመርጡ›› እየተባሉ ነው፡፡ አንተ የጠቀስከው ችግር እንደሚገጥመንም እናምናለን፡፡ እነዚህ ችግሮች ከአሁን ቀደም በተለያዩ ቦታዎች ስንቀሳቀስ ገጥመውናል፡፡ በእኛ በኢትዮያ አንድነትና በኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ላይ ባለን አቋም ህዝቡን በጎሳ ከፋፍለው ደጋፍ ለማግኘትና እኛን ለማስጠላት የሚሞክሩ አሉ፡፡ ከእነሱ ደጋፍ እናገኛለን ብለን አናምንም፡፡ ምክንያቱም የእኛ ትግል ከኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን በጎጥና በጎሳ



ከተደራጁ ፓርቲዎች ጋርም ስለሆነ ነው፡፡ ይህን እንዴት እንፈታዋለን ስንል፤ አሁን እየሰራነው ያለው ስራ ህዝብን የማንቃት ስራ ነው፡፡ አላማችንና ፕሮግራማችንን በደንብ የማሳወቅ ስራ እንሰራለን፡፡ አላማችንንና ፕሮግራማችን ህዝብ በደንብ ካወቀው ዳኛ የሚሆነው ህዝብ ነው፡፡ መጀመሪያ ግን ህዝቡ ኢትዮጵያዊነት ስንል ምንድን ማለት እንደሆነ ማወቅ አለበት፡፡ ምክንያቱም ለህዝብ ኢትዮጵያዊነትን ጭራቅ አድርገው የሚስሉ ስላሉ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነት ብለን ስንነሳ የአንድን ጎሳ የቆየ ስልጣን ለማስመለስና አሁን ኢህአዴግ ‹‹ብሄር ብሄረሰቦች›› የሚላቸውን ለመጨፍለቅ የተነሳን አድርገው ነው የሚነግሯቸው፡፡ ጭራቅ አድርገው ነው የሚነግሯቸው፡፡ ይህንን ብዙ ቦታዎች ላይ ማየት ችለናል፡፡ ለምሳሌ ያህል ደቡብ ክልል ላይ ሰላማዊ ሰልፍን ጨምሮ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል እንደምንቀሳቀስና ለደቡቡ ትኩረትና ክብር እንደማንሰጥ ተደርጎ ተነስቷል፡፡ ይህ እኛ ለማጥላላት የሚያደርጉት ዘመቻዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነት ፍትጊዎች አሉ፡፡ እነዚህን ፍትጊያዎች ለመፍታት የምናደርገው የመጀመሪያው ጉዳይ እነዚህ ፓርቲዎች ወደ ኢትዮጵያዊነት እንዲመጡ ትግል ማድረግ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነት ይዘን በትክክለኛ ሜዳ ላይ ነው ትግል ልናደርግ የሚገባው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን እኛ ለህዝቡ ጎጠኝነትና ዘረኝነት ምን ያህል ጉዳት እንደሚያመጣ ለህዝብ እናስተምራለን፡፡ የጎሳ ፓርቲዎች መኖር ለገዥው ፓርቲ ጠቅሞታል፡፡ ሲዳማ ላይ ሲአን የሚባል ፓርቲ እንዳለ አይተናል፡፡ ወላይታ ላይም የደቡብ ህብረት ይንቀሳቀሳል፡፡ እንዳገኘነው መረጃ በጎሳ ፓርቲዎች መበራከት ምክንያት እንደ ቡርጅ የመሳሰሉ ህዝቦችን ግጭት ኢህአዴግ እየተጠቀመበት ነው፡፡ ኢህአዴግ ለ23 አመት ያህል የሰራበት በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጉዳዩ መፍትሄ ያገኛል የሚል እምነት ባይኖረንም የቻልነውን ያህል እንሰራለን፡፡ ፍትጊያውን የምንፈታውም ቢቻል አቋማቸው የተሳሳተ በመሆኑ አቋማቸውን እንዲያስተካክሉ፤ ካልሆነ ግን አቋቸው ትክክል አለመሆኑን ለህዝብ በማሳየት ከህዝብ በመነጠል ነው፡፡

ነገረ ኢት፡- ከአሁን ቀደም ከውህደት ይልቅ ለትብብር ቅድሚያ ትሰጡ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይህም በሌሎች ፓርቲዎች ሳይቀር ሲያስተቻችሁ ቆይቷል፡፡ በቅርቡ ደግሞ ሎሚ መጽሄት ላይ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ውህደት እንደምትፈልጉ አንብቤያለሁ፡፡ አቋም ቀይራችኋል?

አቶ ብርሃኑ፡- እንግዲህ ባለፈው ቅድሜ በወጣው ሎሚ መጽሄት ላይ ‹‹ውህደት እንፈልጋለን፡፡ ለምንድን ነው የምንዋሃደው የሚለው ግን ያሳስበናል›› የሚል አብይ ርዕስ የተሰጠው ከእኔ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ አንብቤያለሁ፡፡ ሰማያዊ ፓርቲ የተለየ አቋም ለውጥ አድርጎ አይደለም፡፡ በመሰረቱ ጋዜጠኛው ይህንን ነገር ከየት አምጥቶ እንደጻፈው አላውቅም፡፡ ውስጥም ጽሁፉ ለይም እንዲህ አይነት ሀሳብ የሚያንጸባርቅ ነገር አይገኝም፡፡ ሰማያዊ ፓርቲ ከውህደት ትብብር መቅደም አለበት ሲል በብሄራዊ ምክር ቤት ተነጋግሮና ወስኖ፤ ከዛም በስራ አስፈጻሚ ቤት ተነጋግሮ ወስኖ፤ ከዚህም ባለፈ ህዝብ በተሰበሰበበት ጥናት አቅርቦ ይህንንም ህዝብ ተወያይቶበት ሀሳብ እንዲሰጥ አድርጎ ነው ትብብር ይቅደም የሚለው አቋም ላይ የደረሰው፡፡ ሎሚ ላይም ርዕሱ ላይ በተሳሳተ መንገድ ወጣ እንጅ ማለት የፈለኩት ‹‹ትብብር ይቀድማል፣ አሁንም ባልተቀናጀ መልኩ ለፓርቲዎችም፣ ለህዝብም አይጠቅምም፡፡ ፓርቲዎችን ያዳክማል፤ ህዝብን ተስፋ ያስቆርጣል፤ ለኢህአዴግ ግን ይመቸዋል ብለን እናምናለን፡፡›› ይህንን ስንል ቀድሞ ውህደት፣ ትብብር፣ ግንባር ፈጥረው ይንቀሳቀሱ ከነበሩ ፓርቲዎች ብዙ ትምህርት ወስደን ነው፡፡ አሁን በሰማያዊ ፓርቲ ጊዜያዊ አቋም ስለ ውህደት ማሰብ አይቻልም፡፡ ከፓርቲዎች ጋር በትብብር በሰራን ቁጥር የመቀራረቡ፣ የመተቻቸቱና ስራዎችን በጋራ የማከናወኑ ነገር ስለሚኖር ያኔ ስለ ውህደት ልናስብ እንችላለን፡፡ በደንብ ለማስመር የምፈልግበት ጉዳይ፤ ብዙ ፓርቲዎች ስለ ውህደት ሲያነሱ ካተዋሃድን ህዝቡን ስለምንከፋፍለው በመዋሃድ ህዝቡን አንድ ማድረግ አለብን የሚል መከራከሪያ ነው የሚያነሱት፡፡ ሰማያዊ የሚያነሳው መከራከሪያ ግን ‹‹እኛም ሌሎቹም ፓርቲዎች ህዝብ ውስጥ ገብተው የሚጠበቅብንን ያህል በመስራት ማምጣት ስላልቻልን የሚከፋፈል ህዝብ የለም›› የሚል ነው፡፡ የተወሰነው ህዝብ ሰማያዊን፣ የተወሰነው አንድነትን፣ ቀሪው መኢአደን ደግፎ ሲመጣ ያኔ በዚህ ጉዳይ ልንወያይበት እንችል ይሆናል፡፡ አሁን ግን እኛም ሆነ ሌሎች ፓርቲዎች የሚጠበቅብንን ያህል እየሰራን አይደለም፡፡ አሁን እንኳ በየ ወረዳው በጀመርነው እንቅስቃሴ ምን ያህል ህዝብ ለመደራጀት መጠማቱን ማየት ችለናል፡፡ ከድሮም ጀምሮ ፖለቲካ ውስጥ የነበሩ አካላት እየተዋሃዱ እየፈረሱ የመበራከት ስራ እንጅ ለህዝብ የሚጠቅም ስራ እየተሰራ አይደለም፡፡

ነገረ ኢት፡- በአሁኑ ወቅት ለትብብር ቅድሚያ ከሰጣችሁ ከማን ጋር ነው እየተባበራችሁ ያላችሁት? ወይንም መተባበር የምትፈልጉት?

አቶ ብርሃኑ፡- በፓርቲያችን ፕሮግራም ላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ከጎሳ ፓርቲዎች ጋር ልንተባበር አንችልም፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በኢትዮጵያዊነት የሚያምን፣ እንዲሁም የእውነት ከህዝብ ጎን ቆሞ የተሻለ አጀንዳ ይዞ ከመጣ ፓርቲ ጋር አብረን ለመስራት ዝግጁ ነን፡፡ እኛ መግለጫዎችን ስናወጣ ፖለቲካ ፓርቲዎችና ሲቪክ ማህበራት አብረውን እንዲሰሩ ጥሪ እናደርጋለን፡፡ ለምሳሌ ያህል ሳውዲ ኤምባሲ ላይ ያደረግነውን ጨምሮ ባከናወናቸው ሰላማዊ ሰልፎችና ሌሎችም እንቅስቃሴዎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሲቪክ ማህበራት አብረውን እንዲሰሩ ጥሪ አድርገናል፡፡ ፓርቲዎች የተለያዩ መድረኮች ሲያዘጋጁም አባላቶቻችን እንዲሳተፉ እናደርጋለን፡፡ በመሆኑም ለኢትዮጵያ የሚጠቅም አጀንዳ ያለው ፓርቲ ጋር ለመተባበር ዝግጁ ነን፡፡ አሁንም በድጋሜ ተባብረን እንድንሰራ ጥሪዬን አቀርብላቸዋለሁ፡፡ አሁን በሚዲያውና በተለያዩ መድረኮች የሚገለጸው ግን እኛ ውህደትን እንደምንጠላና ራሳችን ትልቅ አድርገን እንደምንቆጥር ነው፡፡ ይህ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ትልቅ ነን ልንል ብለን ልንኮፈስና ትልቅ ስራ ሰርተናል ልንል አንችልም፡፡ ስላልሰራን ነው አሁን በየወረዳው እየዞርን የምናደራጀው፡፡ ከአሁን ቀደም ብዙ ስራ ሰርቻለሁ የሚልማ ቢሮ ውስጥ ሆኖ መግለጫ ማውጣት ነው የሚጠበቅበት፡፡ እንደ ውህደት ጠል ባንታይ ግን ጥሩ ነው፡፡ ውህደት መቼ፣ ከማን ጋር፣ ለምን መካሄድ አለበት የሚባለው ግን መግባባት አለብን፡፡ ምርጫ ሲደርስ ብቻ እንደሙጫ ተጣብቀው በምርጫ ማግስት ሰርተፊኬት የሚከፋፈሉ ፓርቲዎች ፈጥረን ህዝብን ተስፋ በማስቆረጥ እንደገና ለሚቀጥሉት ሰባትና ስምንት አመታት ማስገዛት የለብንም ብለን ስለምናምን ነው፡፡

# ይህ ገጽ በሰማያዊ ፓርቲ አዘጋጅነት የሚቀርብ ሲሆን፣ ፓርቲው ፕሮግራሙንና አላማውን ለአባላትና ደጋፊዎቹ የሚያደርስበት ነው፡፡

*መንደርደሪያ*

ሰማያዊ ፓርቲ በዘር፣ በሃይማኖት በቋንቋ በፆታና በሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መመዘኛዎች በዜጎች መካከል ልዩነት ሳያደርግ በማደራጀት የኢትዮጵያን ህዝቡ የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ይታገላል፡፡

## ሰማያዊ ፓርቲ ለምን ተመሰረተ?

ሀገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ አኩሪ ታሪክ፣ ቀደምት የሥልጣኔ ባለቤትና ከ3000 ዘመን በላይ የመንግስትነት ታሪክ ያላት ታላቅ ሀገር ናት፡፡ የሰው ልጅ ዛሬ ለደረሰበት የዕድገትና የስልጣኔ ደረጃ መሰረት የሆኑ ቁሳዊና መንፈሳዊ ትውፊቶችን በማበርከት ለዓለም ስልጣኔ ታላቅ አስተዋፅዖ አበርክታለች፡፡ በየዘመናቱ ነፃነቷን ለማጥፋት የወረሯትን የውጭ ተስፋፊዎችና ቅኝ ገዥዎች በተደጋጋሚ ጊዜ ድል በማድረግ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷንም አስከብራ ኖራለች፡፡ ሀገራችንን በእብሪት ለመውረር የመጣውን የኢጣሊያን ወራሪ በመደምሰስ በዓለም ለመጀመሪ ጊዜ ጥቁር የሰው ልጅ ዘር ነጭ ወራሪዎችን ማሸነፍ እንደሚችል በአድዋ ታሪካዊ ድል ያስመሰከረች ብቸኛ የጥቁር ሰው ዘር መኩሪያና መመኪያ ሃገር ነች፡፡

ቅኝ ገዥዎችና ኢምፔሪያሊስቶች አፍሪካን ለመቀራመትና የተፈጥሮ ሃብቷን ለመዝረፍ ያደረጉትን ስምምነት ተከትሎ አፍሪካን በቅኝ ግዛት ስር ለማዋል በተደረገው ወረራ ተስፋፊዎችን በመመከት በቅኝ ገዥዎች ሥር ያልወደቀችና ለመላዉ ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ተምሳሌት ሐገር ነች፡፡ አብዛኛዎቹ አፍሪካዊ ሀገሮች ድንበሮቻቸውና ማንነታቸው በቅኝ ገዥዎች ፍላጎት እንዲወሰን ሲደረግ ሀገራችን ወራሪዎችን በመቋቋም የራሷን የድንበር ወሰንና ማንነት በራሷ መወሰን የቻለች ብቸኛዋ አፍሪካዊ ሀገር ናት፡፡

ሀገራችን የበርካታ ገፀ ምድርና ከርሰ ምድር ኃብት፣ አስደናቂ የተፈጥሮ ውበትና የሰው ልጅ ቀደምት ስልጣኔ መገለጫ የሆኑ ቅርሶች ባለቤት፣ ሰፊ መሬትና የሰው ኃይል ያሏት ታላቅ ሐገር ናት፡፡ ሀገራችን የተለያዩ የአየር ፀባያት ባለቤት ስትሆን ለሰው ልጅ መኖሪያና ለአዝርዕት መብቀያ ተስማሚ ተፈጥሮ በሰፊው የተለገሳት ሀገር ናት፡፡ በርካታ በጥቅም ላይ የዋሉና ገና ያልተነኩ የተፈጥሮ ስጦታየፈሰሰባትም ምድር ናት፡፡

ሆኖም የዚህ አኩሪ ታሪክ፤ ባህልና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት የሆነች ሃገራችን ዛሬ በቀሪው የዓለም ሕዝብ ፊት የምትታወቀው በርሃብተኝነት፣ በተመፅዋችነት፣ በስደትና በእርስ በእርስ ጦርነት ባለቤትነቷ ነው፡፡ የሰው ልጅ ዛሬ ከረደሰበት የአስተዳደርና የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ እንዳንደርስ ያደረገን በሃገራችን ተንሰራፈተው በቆዩና አሁንም ባሉ የአስተዳደርና የፖለቲካ ሥርዓት ብልሹነቶች ምክንያት ነው ብለን እናምናለን፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ በፖለቲካ እድገት ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚና በማህበራዊ እድገትም የዓለም ሃገራት የመጨረሻዎቹ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ሕዝቧ የዘር፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋና የባህል ልዩነቶችን ተቀብሎ ለበርካታ ዘምናት ተቻችሎ የኖረ ቢሆንም ዛሬ እርስ በእርስ በጥርጣሬ እንዲተያይና አንድነቱ እንዲላላ እየተደረገ ነው፡፡ ሃገራችን በተቀበለቻቸውና ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ህጎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እውቅና ያገኙ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚያከብራቸውና የሚጠብቃቸው ባለቤት አጥተዋል፡፡ የኢኮኖሚ መርሃችንም በጥናትና በአስተማማኝ መሠረት ላይ ያልተጣለ በመሆኑ ካለንበት የድሕነት አዘቅት ሊያወጣን አልቻለም፡፡ ፍትኃዊ የንብረት ስርጭትና የሥራ እድል ባለመኖሩ በኢትዮጵያውያን መካከል ያለው የኑሮ ደረጃ እጅግ እየተራራቀ መጥቷል፡፡ ዜጎችም የዜግነት እኩልነት ክብራችን ተነፍገን አብዛኛዎቻችን በሃገራችን ጉዳይ ባይተዋር ሆነናል፡፡

ዛሬ የዚህ ትውልድ አካል የሆንን ዜጎች ይህንን የተዛባ አካሄድ የመቀየርና ሃገራችንን የተሻለች ሃገር የማድረግ ኃላፊነት አለብን ብለን እናምናለን፡፡ በመሆኑም የሰማያዊ ፓርቲያችን ራዕይ፣ ተልዕኮና ዓላማ ለሃገራችን ካለን ጥልቅ ፍቅር፣ለፍትሃዊ አስተዳደር መስፈን ካለን ፅኑዕ እምነትና ከሰው ልጅ ምክንታዊ አስተሳሰብ ይመነጫሉ፡፡ ፍትሕ እንዲሰፍን የምንፈልግ ሃገራችንንም በእውነት የምንወድ ከሆነና በሰው ልጅ ምክንያታዊ አስተሳሰብ የምንገዛ ከሆነ ችግሮቻችን በሰላማዊ መንገድ፣ በመነጋገር፣ በመደማመጥና በመግባባት ብሔራዊ እርቅና መከባበርን በመፍጠር የሚፈቱ ናቸው ብለን እናምናለን፡፡

ፓርቲያችን በሃገሪቱ ህገ-መንግስት መሠረት በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ትግል በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከውስብስብና ፈርጀ ብዙ ችግሮች ተላቆ እያንዳንዱ ዜጋ በነፃነት ሃሳቡን የመግለፅ፣ የመደራጀት፣ የፈለገውን የመደገፍና የመቃወም፣ በፈለገው ሙያና የሥራ መስክ የመሰማራት፣ ሃብት የማፍራትና የሃብቱ ባለቤት የመሆን እንዲሁም የግል ስብዕናውን የማሳደግ መብቱ የተረጋገጠ እንዲሆን እንታገላለን፡፡ ሐገራችን ከድህነትና ከጦርነት የተላቀቀች፣ ፍትሕና ሰላም የሰፈነባት እንድትሆን የፖለቲካ ሥልጣን በመያዝ የዜግነት ድርሻችንን ለመወጣትና ራዕያችንን እውን ለማድረግ ሰማያዊ ፓርቲያችንን መስርተናል፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ ራዕዩን እውን ለማድረግ፤

ሀ. ፓርቲያችን የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መርሆችን ይከተላል፡፡

ለ. በሰማያዊ ፓርቲ ፕሮግራም ውስጥ ለተካተቱ አንዳንድ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የሕገ-መንግሥቱ አንዳንድ ድንጋጌዎችን ህገ-መንግስቱ ባስቀመጠው የህገ-መንግስት ማሻሻያ መርሆች መሰረት ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን ታሳቢ ተደርጓል፡፡

መ. ዓላም ዛሬ ከደረሰችበት የሥልጣኔ ደረጃና ከሰው ልጅ ምክንያታዊ አስተሳሰብ በመነሳት ከሰላማዊ ትግል ውጭ በሃገራችን የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓትን መገንባት አይቻልም ብለን እናምናለን፡፡ ስለዚህ ፓርቲያችን በሰላማዊ የትግል ስልት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ ይታገላል፡፡

የፖርቲው ስያሜና ትርጓሜ፤

የፓርቲው ስያሜ "ሰማያዊ ፓርቲ" በአህፅሮት "ሰማያዊ" በእንግሊዝኛው አጠራር "BLUE PARTY" ሲሆን ትርጓሜውም ሰማያዊ ቀለም የሰላም፣ የተስፋና የአንድነት መገለጫ በመሆኑና ፓርቲያችንም ሰላም ተስፋና አንድነት በሃገራችን እንዲሰፍን ያለውን የፀና እምነት መግለፅ ነው፡፡

የፓርቲው ዓርማ፡-

ከመሃል በጠባብ ክብ የሚጀምርና ሌሎች እየሰፉ የሚሄዱ ክቦቹ ሲኖሩት በደማቅ ሰማያዊና ውሃ ሰማያዊ ቀለሞች በመፈራረቅ የሚቀባ በጨርቅ ወይም በሌላ ቁስ ላይ የሚያርፍ ምልክት ይሆናል፡፡ የዓርማው ቀለማት የፓርቲያችንን ስያሜና ትርጉም የሚያሳዩ ሲሆን ከትንሽ ጀምሮ እየሰፉ የሚሄዱት ክብ ምልክቶች ደግሞ ጥቂት ሆነን ጀምረን እየበዛን እንደምንሄድ ለማሳየት ነው፡፡

የፓርቲው ሀገራዊ ዕይታ

ሀ. ኢትዮጵያ ሀገራችን በኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ ገዥነት ስር የሚገኘውን መሬት፣ ውሃ፣ የአየር ክልል፣ በከርሰ ምድርና በከርሰ ውኃ የሚገኘው ሃብት፣ በአየር ክልሉ ያለው የድምፅና የምስል ሞገድ ባለቤት ሉዓላዊ ሀገር ናት፡፡

ለ. የኢትዮጵያ ያልተመለሱ የድንበርና የይገባኛል ጥያቄዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የአስተዳደር ወሰን አሁን በኢትዮጵያ መንግስት ሥር የሚገኘውና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተመዘገበዉ ክልል ነው፡፡

ሐ. በኢትዮጵያ ውስጥና በውጭ ሃገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ናቸው፡፡

መ. የኢትዮጵያ ሕዝብም በኢትዮጵያ ጉዳይ ባለሙሉ የሥልጣን ባለቤት ነው፡፡ ሃገሪቱን የማስተዳደር ሥልጣን ከሕዝብ ይመነጫል፡፡

ሠ. የኢትዮጵያ አንድነትም ሆነ ሉዓላዊነት አይነጣጠሉም፤ለሌላም አይለቀቁም፡፡

ረ. ኢትዮጵያውያን በግል ያላቸው የዜግነት መብትም ሆነ በወል የሚጋሩት የህግ፣ የፖለቲካ የማህበራዊና የባህል መብት የአንድነታቸው ዓይነተኛ መሰረት ነው፡፡

ሰ. ኢትዮጵያ ሀገራችን የረጅም ጊዜ አኩሪ ታሪክ፣ የበርካታ ገፀ-ምድርና ከርሰ-ምድር ሃብት ባለቤት፣ አስደናቂ የተፈጥሮ ውበትና የሰው ልጅ ቀደምት ሥልጣኔ መገለጫ የሆኑ ቅርሶች ያሏት ታላቅ ሃገር ናት፡፡

ሸ. ሃገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ወግና ሥርዓት አሸብርቃ የኖረች፣ በብዙ ዓይነት ሃረጎች ተሳስረውና በታሪክ ተቆራኝተው የጋራ አመለካከትና ኢትዮጵያዊ ማንነትን በማዳበር ለዘመናት ተቻችለውና ተከባብረው በአንድነት የኖሩ ዜጎች ሃገር ናት፡፡ እነዚህ ዜጎች በየዘመናቱ የተለያዩ አስተዳደራዊ በደልና ጭቆና ደርሶባቸዋል፡፡ ዛሬም ቢሆን የዜጎች የአስተዳደርና የፍትህ ጥያቄ በአግባቡ አልተፈታም ወይም መብታቸው አልተከበረም፡፡ በመሆኑም ሁሉም ዜጎች የዜግነት መብታቸው እንዲከበርና በሃገር ጉዳይ ላይ ተገቢው ድርሻና ተሳትፎ እንዲኖራቸው አሁንም ፅኑዕ ትግል የሚያስፈልጋት ሃገር ናት፡፡

ራዕይ

የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ የተከበሩባት፤ ለሕዝብ ፍላጎት መሟላት በኃላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰራ መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት የተረጋገጠባት፤ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ብልፅግና የሰፈነባት፤ ለዜጎቿ ሁሉ አለኝታና መኩሪያ የሆነች፤ለዓለም ሕዝብ መልካም ግንኙነት የበኩሏን አስተዋፅዖ የምታደርግ ኢትዮጵያን ማየት ነው፡፡

ዓላማ

ሀ. የዜጎች ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩና ተፈፃሚም ኢንዲሆኑ በጽናት መቆም፡፡

ለ. ለዜጎች አስተማማኝ የማሕበራዊ ደህንነት ዋስትና አገልግሎት ማቅረብ፡፡

ሐ. የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ነፃ፣ ፍትሃዊና ትክክለኛ በሆነ መንገድ ተወዳድረው የፖለቲካ ሥልጣን የሚይዙበት የምርጫ ሥርዓት መመስረት፡፡

መ. ራዕዩን ተግባራዊ ለማድረግ በነፃና ፍትኃዊ ምርጫ በህዝብ ድምፅ የፖለቲካ ሥልጣንመያዝ

ሠ. ሀቀኛ፣ ብቃትና ተጠያቂነት ባለው አመራር አማካኝነት ታታሪና የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ዜጎች መፍጠር፡፡

ረ. የሕብረተሰቡን የፖለቲካ ግንዛቤ በማሳደግ ዜጎች በሃገራቸው ጉዳይ በንቃት እንዲሳተፉ፣ ግዴታቸውንና ኃላፊነታቸውንም እንዲወጡ ማድረግ፡፡

ሰ. የእያንዳንዱን ዜጋ ችሎታ በማሳደግ በሃገርና በዓለም ደረጃ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ያለውን ምኞት ማሳካት፡፡

ሸ. ከሀገራቸው ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሰብዓዊና ቁሳዊ አቅማቸውን ለሃገራቸው ልማት እንዲያውሉና ለሕዝብም ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት መሻሻል የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ማበርከት የሚችሉበት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ሥርዓት መመስረት፡፡

ቀ. ዓለምን ለመረዳትም ሆነ የዓለም ሕብረተሰብ በአግባቡ እንዲረዳው ማድረግ የሚችልና በነፃነት የሚያስብ ሕብረተሰብ መመስረት፡፡

በ. የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ በራሱና በወረሰው መልካም ነገር እንዲኮራና በሕይወቱ ውስጥ ተስፋ እንዲኖረውና ለከፍተኛ ግብ እንዲሰራ ማደፋፈር፡፡

ተልዕኮ

ተልዕኮአችን ዓላማችንን ማሳካት ሆኖ በተለይ በሀገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ዋስትና የሚሰጥ ከሕዝብ፣ በሕዝብ፣ ለሕዝብ የቆመ መንግስት በሰላማዊ መንገድ መመስረት ነው፡፡

ርዕዮተ ዓለም

እጅግ ውድ የሆነው የሰው ልጅ ሃብት ነፃነቱ በመሆኑ ሰማያዊ ፓርቲ ለግለሰብ ነፃነት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ዜጎች በቡድን ሊያከናዉኗቸው የሚፈልጓቸው እንደ ሃይማኖት፣ ልማዶች፣ ቋንቋ፣ ማህበሮች እና የመሳሰሉት የጋራ መብቶች የግለሰብን በነፃነት የመወሰን መብት ሳይሸረሽሩ እንዲከበሩ የህግ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው ያምናል፡፡ በመሆኑም ሰማያዊ ፓርቲ በለዘብተኛ ሊብራል ዲሞክራሲ መሰረታዊ መርሆች ይመራል፡፡

ትኩረት

ሰማያዊ ፓርቲ በኢትዮጵያ ውስጥ 51% ያህል ቁጥር ያላቸውን ሴቶች ወደ ፖለቲካው መድረክ እንዲመጡ ቅድሚያ በመስጠት ይሠራል፡፡ በተጨማሪም እድሜው ከ35 ዓመት በታች የሆነውና 70% የሚሆነውን የኢትዮጵያን ህዝብ ቁጥር የያዘው ወጣቱ ትውልድ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ወደፊት ለማራመድ ከፍተኛ አሰተዋፅኦ አለው ብሎ ፓርቲያችን ያምናል፡፡ ከፍተኛ ተኩረትም ለወጣቱ ትውልድ ይሰጣል፡፡ ይህንንም በተግባር ለማሣየት የፓርቲው አብዛኛው አማራሮች የዚህ ትውልድ አካል ናቸው ፡፡

ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች

1. ሰማያዊ ፓርቲ በምርጫ ቦርድ የተነፈገውን የምስክር ወረቀት በህግና በትግሉ ከቦርዱ ወረቀት በፊት ራሱን ህጋዊ አካል አድርጓል

2. ፓርቲው ራሱን ከህዝብና ከደጋፊዎቹ ለማስተዋወቅ በርካታ የውይይት መርሃ ግብሮችን አካሂዷል፡ ፡

3. ለፓርቲው ድጋፍ በዋቢ ሸበሌ ሆቴል ያዘጋጀው የራት ግብዣ ፕሮግራም በመንግስት ካድሬዎች ጫና ተስተጓጉሏል፡፡

4. "ውይይትና መነጋገርን እንለማመድ" በሚል ርዕስ "መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ" በተሰኘው የፕ/ሮ መስፍን ወልደማርም መፅሀፍ ላይ ውይይት እንዲደረግ በብሔራዊ ቲአትር ባዘጋጀው ዝግጅት ከሁለት ሺህ በላይ ተገኝቶ እንዲወያይ እድል ፈጥሯል፡፡

5. ለፋሽስቱ ግራዚኒ ሐውልትና የመታሰቢያ መናፈሻ ቦታ እንዲሰራለት መደረጉን በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ በማድረጉ አባላቱን አመራሮቹ ወደ አስር ቤት እንዲወረወሩ ተደርገዋል፡፡

6. በሚናገሩት ቋንቋ መለየት ምክንያት በቤኔሻንጉል ለዘመናት ከኖሩበት የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን እቦታቸው ድረስ በመሔድ ጎብኝቷል፤ አወያይቷል፡፡

7. በሐገራችን የሰፈነውን አምባገነንነት፣ የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ጥሰት፣ የዜጎችን መፈናቀልና የመንግስትን በሐይማኖት ጣልቃ መግባት በመቃወም ለስምንት አመታት የተነፈገውን የሰላማዊ ሰልፍ መብት በመመለስ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል፡፡

ድ-ገፅ www.semayawiparty.org ይጎብኙ፡፡

ወይም Facebook BluePartyEthiopia ላይክ ፔጅ

semayawiparty Ethiopia ይከታተሉ፡፡

አድራሻ፡- ሰማያዊ ፓርቲ

ፖ.ሳ. ቁ 180298

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ +251118592950

አቢሲኒያ ባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ቁጥር፡ C/A619

# በግድቡ ሕይወታቸው . . .

ከ ገፅ 7 የዞረ

የውኃ ፍሰት መጠን በመሰረታዊ መልኩ ያናጋዋል፡፡ ወደግድቡ ማጠራቀሚያ እና ለስኳር ልማት የመስኖ ስራ ለሚውለው ውኃ ፍጆታ ሲባል የውኃው የፍሰት አቅጣጫ ሲቀየር አጠቃላይ የኦሞ ወንዝ የውኃ መጠን ዘለቄታዊ ባለው ሁኔታ በእጅጉ እንደሚቀንስ በመስኩ የተሰማሩ ባለሙያዎች አሳማኝ በሆነ መልኩ ሞግተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በሸለቆው ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች በእርግጠኝነት ባህረ ሸሽ እየተባለ የሚጠራውን የግብርና ዘይቤ ለማካሄድ አይችሉም፡፡ እ.ኤ.አ በ2012 በዓለም ዕውቅናን ያተረፉት የተፈጥሮ ሀብት ክብካቤ እና ጥንታዊ የሰው ዘር ተመራማሪ የሆኑት ባለሙያ ዶ/ር ሪቻርድ ሊኬይ የጊቤ ሦስት ግድብ ግንባታ የግል ጥቅም ማሳደጃ "ሳይንሳዊ" ጥናት በስነ-ምህዳሩ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉትን ውጤቶች አሳንሶ የሚያይ መሆኑን የምር በመሞገት "ግድቡ በርካታ የሆኑ አሉታዊ ውጤቶችን እንደሚያስከትል እንዲያውም አንዳንዶቹ በሁለቱም በኩል ማለትም በአካባቢው ስነ-ምህዳር እና ለዘመናት ህይወቱን በዚህ ወንዝ የታችኛው ክፍል ላይ መስርቶ ለሚኖረው ማህበረሰብ ህይወት ውድመት እና ዕልቂት" ሊሆን እንደሚችል አስረግጠው ተንብየዋል፡፡

የኦሞን ወንዝ "ማልማት"

እ.ኤ.አ በ2011 መጨረሻ አካባቢ አቶ መለስ ዜናዊ በደቡብ ኦሞ ዞን በጅንካ ከተማ በመገኘት ንግግር አድርገው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ አቶ መለስ ረዥም እና የማስመሰያ፣ እንዲሁም ጠንከር ያለ እና እብሪት የተሞላበት ንግግር ነበር ያደረጉት፡፡ "በኋላ ቀር ስልጣኔ" ተተብትበው የሚገኙት ላሏቸው በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ግራ እና ቀኝ ለሚኖሩ ህዝቦች ከሰማይ መና እንደሚያወርዱላቸው ነበር ቃል የገቡት፡፡ እነዚህን ህዝቦች ከድንጋይ ዘመን መንጥቀው በማውጣት ወደ ስልጣኔው ዘመን በእልልታ በማምጣት "የፈጣን ልማት ምሳሌ" እንደሚያደርጓቸው ምለው ተገዝተው ነበር፡፡ እንዲህ በማለት ነበር ለማህበረሰቡ የመተማመኛ ንግግር ያደረጉት፣ "በኦሞ ወንዝ የሚገነባው ግድብ የጎርፍ አደጋውን ያስወግድላችኋል፣ ግዙፍ የሆነ የመስኖ ልማት ስርዓት ይዘረጋል፣ እናም ከቦታ ቦታ የምትዘዋወሩት የማህበረሰብ አባላት (pastoralists) ዘለቄታዊ የሆነ ገቢ ያስገኝላችኋል፣ እንዲሁም ደግሞ ዘመናዊ ህይወት ትኖራላችሁ"::

ለጊቤ ሦስት ግድብ ግንባታ ሂደት ጥንቃቄ እና ትኩረት በመስጠት እንዲከናወን እና ለዘመናት በኦሞ ሸለቆ ግራ እና ቀኝ ኑሮውን በመግፋት ላይ የሚገኘውን ህዝብ የህይወት ዘይቤ እና ባህል በጠበቀ መልኩ የልማት ስራው እንዲከናወን ተማፅኗቸውን ላቀረቡ ዓለም አቀፍ የአካባቢ ስነ-ምህዳር ጥበቃ እና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች አቶ መለስ በአጻፋው ጥላቻ በተሞላበት መልኩ ስራቸውን ስማቸውን በማጠልሸት እና በነገር በመሸንቆጥ የአቅማቸውን ያህል ተግትገዋቸዋል፡፡ እነዚህን ዓለም አቀፍ ድርጅቶች "ወንዞቻችንን የመጠቀም ነጻነታችንን ለመገደብ እና ህዝቦቻችንን ከድህነት እንዳናወጣ" ሁል ጊዜ ለተቃውሞ የተዘጋጁ እና እልቂት ናፋቂ ሟርተኞች ናቸው በማለት ፈርጀዋቸዋል፡፡ እንዲሁም አደገኛ የልማት አደናቃፊዎች የሚል ታርጋ ለጥፈውላቸዋል፡፡ እንዲህ በማለትም አክለውላቸዋል፣ "ግዙፍ የሆነ ፕሮፓጋንዳ በመፍጠር ላይ ናቸው… የልማት ፕሮጀክቶቻችንን እንዳናጠናቅቅ ከውጭ የገንዘብ ብድሮችን እንዳናገኝ መሰናክል በመፍጠር ላይ ናቸው፡፡" እንዲህ ሲሉም ተሳልቀውባቸዋል፣ "የኋላቀርነት እና የድህነት ሁነኛ ጓደኞች…በእርግጥ ምንም ዓይነት ተጨባጭነት ያለው ነገር የማይሰሩ" ብለዋቸዋል፡፡ ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ለእራሳቸው ጥቅም ብቻ የቆሙ ዘረኞች ብለዋቸዋል፣ ምክንያቱም ይላሉ፣ "ሁሉም እንዲሆን የሚፈልጉት ነገር እነዚህ ዘላኖች የቱሪስት መስህብ ሆነው እንዲቀሩ ነው፡፡" እናም የኦሞ ወንዝ ሸለቆ ህዝቦች፣ "ለሳይንቲስቶች እና ለተመራማሪዎች ለጥንታዊ የሰዎች የአኗኗር ዘይቤ የተናጠል ጥናት" ማድረጊያ ማዕከል ሆነው እንዲቀሩ ለማድረግ አስበው ነው ብለዋል፡፡

አቶ መለስ እና ሎሌዎቻቸው ከዚህ ቀደም የተደረገውን እና በአሁኑ ጊዜም በጊቤ ሦስት ግድብ እና ሸለቆውን "ለማልማት" በሚል ሰበብ እየተደረገ ያለውን የአካባቢ ውድመት ለመደበቅ ብዙ ርቀቶችን ተጉዘዋል፡፡ እ.ኤ.አ በጁላይ 2008 በግድቡ ላይ የግንባታ ስራ ከተጀመረ ከሁለት ዓመታት በኋላ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና የአካባቢ ስነ-ምህዳር ጥበቃ ድርጅቶች ዓለም እንዲገነዘብ ደወሉን ማሰማት ከጀመሩ በኋላ አቶ መለስ "የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መስሪያ ቤታቸው" የጊቤ ሦስትን ፕሮጀክት የአካባቢ ስነ-ምህዳር እና ማህበራዊ እንደምታ ጥናት አሳትመው እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ያ የጥናት ዘገባ ለማስመሰያነት የአቶ መለስን የማይቀየር ጽኑ ውሳኔ ህጋዊ በማስመሰል ወዲያውኑ በህገወጥ መልክ የፕሮጀክቱን የወደፊት ስራ ለማስቀጠል የተደረገ አሳፋሪ ክንውን ነበር፡፡ ያ ዘገባ ዓይን ያወጡ ቅጥፈቶች የታጨቁበት ነበር፡፡ የጊቤ ሦስት ግድብ የውኃ ማጠራቀሚያ አካባቢ ለሰው ልጅ መኖሪያነት ምቹ አይደለም፣ ምክንያቱም ገዳይ በሆኑት የወባ ትንኝ እና የቆላ ዝንቦች/tsetse flies ("ለእንቅልፍ በሽታ" የሚዳርጉ) ተህዋስያን የተወረረ አካባቢ መሆኑን ሀፍረተ-ቢስ በሆነ መልኩ ያ ቀረበ ዘገባ ነበር፡፡

ዘገባው እንዲህ ይላል፣ "ወደፊት በግድቡ የውኃ ማጠራቀሚያ አካባቢ ምንም ዓይነት ሰፈራ አይኖርም፣ እናም ሰፈራዎች የሚኖሩት በላይኛው ከፍታ ቦታዎች ከሸለቆው ውጭ በሆኑ አካባቢዎች ብቻ ነው… በታችኛው የኦሞ ወንዝ ሸለቆ የመጨረሻ ጠርዝ አካባቢ መሬቶች ላይ በጣም ውስን የሆነ የእርሻ ስራ አለ… በመርሀ ግበሩ በተያዘው ግድብ ዙሪያ የሚኖረው ህዝብ እና በውኃ ማጠራቀሚያው መካከል ያለው የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት/UNESCO ከያዘው የባህል ቅርስ ቦታ በቅርብ ርቀት የሚገኙ አይደሉም፡፡ በግድቡ እና በዙሪያው ባሉ አካባቢዎች ሳይንሳዊ፣ ባህላዊ፣ የዘር እና የታሪክ ጠቀሜታ ያላቸው በግልጽ የሚታዩ ቅሬተ-አካሎች የሉም፡፡"

የአቶ መለስ የኦሞ ወንዝ ሸለቆን "ኋላቀርነት" ወደ "ዘመናዊነት" ኑሮ የመቀየር ዘይቤ ሸለቆውን ለሳውዲ አረቢያ እና ለሌሎች የውጭ መዋዕለ ንዋይ አፍሳሾች እና ለጓደኞቻቸው ለማዛወር የታቀደ ነበር፡፡ አቶ መለስ በንግግራቸው በመቀጠል "መንግስት ዕቅድ ያወጣል፣ እናም 150,000 ሄክታር የስኳር አገዳ ልማት ከዚህ ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ያደርጋል" በማለት መንግስታቸው ጠንክሮ እንደሚሰራ ገልጸው ነበር፡፡ በእርግጠኝነት እንደ አይሲ/IC የተባለው መጽሔት ከሆነ "የሳውዲ አረቢያው ባለሀብት አልሙዲ በከፍተኛ ደረጃ ካሉት የመንግስት አመራሮች ጋር ጥብቅ የግንኙነት ትስስር ስላለው ለሩዝ ምርት የሚሆን 10,000 ሄክታር መሬት ተሸንሽኖ ተሰጥቶታል፡፡" የእርሱ ግዙፍ ፕሮጀክት በአካባቢው ስነ-ምህዳር ማለትም በብሄራዊ ፓርኩ እና በዱር እንስሳት መጠለያ ላይ እንዲሁም ለዘመናት በአካባቢው ሲኖሩ በነበሩ ትውልዶች ማህበረሰብ አባላት ላይ ታላቅ ጉዳትን አስከትሏል፡፡"

አቶ መለስ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ በኦሞ ኩራዝ የስኳር ልማት ፕሮጀክት ስር አምስት የስኳር ፋብሪካዎች ይቋቋማሉ በማለት ተናግረው ነበር፡፡ እንደ "ኢትዮጵያ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ድርጅት" ከሆነ "መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጅነሪንግ/Mesfin Industrial Industry (MIE) የተባለው ድርጅት በአማራ ክልል ከሚገኘው ጣና በለስ የተቀናጀ የስኳር ልማት ፕሮጀክት እና በኦሞ ሸለቆ ከሚገኘው ኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክት ከሚባሉ መንግስታዊ ድርጅቶች ጋር የብር 3 ቢሊዮን (162.2 ሚሊዮን ዶላር) የሚያወጣ ዋጋ ያላቸው ማሽነሪዎችን ለማቅረብ የስምምነት ውል ተፈራርሟል…" መስፍን ኢንዱስተሪያል ኢንጅነሪንግ "ከድሬዳዋ እስከ አዲስ አበባ ለሚዘረጋው የባቡር መስመር ግንባታ ፕሮጀክት እና በተመሳሳይ መልኩ ከጅቡቲ በአፋር በኩል አድርጎ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ለሚዘረጋው የባቡር መስመር አገልግሎት የሚውሉ የባቡር ሃዲዶችን የመዘርጋት የማጠናቀቅ ስራ ያከናውናል፡፡"

እ.ኤ.አ በጁን 2011 "የጊቤ ሦስት ግድብ በቱርካና ሐይቅ ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል አስተማማኝ ያልሆነ የውኃ መጠን በመልቀቅ በውኃ ውስጥ ያሉ ህይወት ያላቸው ዝርያዎችን እና ከእርሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የስነ-ሕይወት ስርዓቶች ለአደጋ እንደሚጥል" እናም "በኢትዮጵያ ያለው መንግስት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሌላ መንግስት ግዛት ውስጥ የተመለከተን ባህላዊ ቅርስ ከጉዳት ላይ ላለመጣል በጊቤ ሦስት ላይ የጀመረውን የግንባታ ስራ በአስቸኳይ እንዲያቆም" በማለት የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት/UNESCO ከድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በአቶ መለስ "የልማት" ዕቅዶች በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ግራ እና ቀኝ የሚኖረው በድህነት የሚማቅቀው እና ተከላካይ የሌለው ህዝብ ፍትሐዊነት በጎደለው መልኩ ግፍ የተፈጸመበት ሲሆን የእርሳቸው ሞራለ-ቢስ ጓደኞች ግን የናጠጡ ሞራለ-ቢስ ሀብታሞች ሆነዋል፡፡ እ.ኤ.አ በጃንዋሪ 2014 የታተመ አንድ የአካባቢ ምህዳር ጥናት ከሆነ "የኩራዝ ስኳር ልማት (161,285 ሄክታር መሬት ይሸፍናል ተብሎ ይገመታል) ግንባታ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ የመሰረተ ልማት ስራዎች የስኳር ማምረቻ መሳሪያዎችን ጨምሮ እና በመንደር የማሰባሰብ ስራዎች የጊቤ ሦስት ግድብ ከመጠናቀቁ በፊት ቀደም ሲል የተጀመሩ ስራዎች ናቸው፡፡ የኩራዝ ስኳር ልማት እና ሌላ ተጨማሪ ለሸንኮራ አገዳው ልማት እርሻ አገልግሎት ምቹ የሆነ የተጠና መሬት (47,370 ሄክታር) እንደ መስኖው ሀብትን በአግባቡ የመጠቀም ባህሪ በእርግጠኝነት የኦሞ ወንዝን 50 በመቶ የውኃ ፍሰት ይፈልጋል፡፡"

የአቶ መለስ የኦሞ ወንዝ ሸለቆ "ስልጣኔ" መርሀ ግብር ለጓደኞቻቸው ነፋስ አመጣሽ ዘረፋ ነው፣ ሆኖም ግን የኦሞ ወንዝ ሸለቆን ኗሪ ህዝቦች ያነጠፈ እና ያደረቀ ዕቅድ ነው፡፡ የአቶ መለስ ስለ ኦሞ ወንዝ ሸለቆ እና ህዝብ ራዕይ" ለሳውዲ አረቢያው ባለሀብት ለአላሙዲ እና ለመስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጅነሪንግ ጥሩ የሆነ ነገር ሁሉ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ህልውናቸውን መስርተው ለሚኖሩ ህዝቦችም ጥሩ ነው" በሚል ዕይታ ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ለዚህም ነው በኦሞ ወንዝ ሸለቆ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለስግብግብነት እና ከሀዲነት ዓላማ መጠቀሚያ እየሆኑ ያሉት!

(ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን እንጂ የኤዱቶሪያሉን አቋም አያንጸባርቅም፡፡)

**የአቶ መለስ የኦሞ ወንዝ ሸለቆ "ስልጣኔ" መርሀ ግብር ለጓደኞቻቸው ነፋስ አመጣሽ ዘረፋ ነው፣ ሆኖም ግን የኦሞ ወንዝ ሸለቆን ኗሪ ህዝቦች ያነጠፈ እና ያደረቀ ዕቅድ ነው፡፡ የአቶ መለስ ስለ ኦሞ ወንዝ ሸለቆ እና ህዝብ ራዕይ" ለሳውዲ አረቢያው ባለሀብት ለአላሙዲ እና ለመስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጅነሪንግ ጥሩ የሆነ ነገር ሁሉ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ህልውናቸውን መስርተው ለሚኖሩ ህዝቦችም ጥሩ ነው" በሚል ዕይታ ላይ ያነጣጠረ ነው: : ለዚህም ነው በኦሞ ወንዝ ሸለቆ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለስግብግብነት እና ከሀዲነት ዓላማ መጠቀሚያ እየሆኑ ያሉት!**

# የአስር ሳንቲም ኢኮኖሚ ወፖለቲካ



በላይ ማናዬ

ያስር በምዕራብ ጎጃም ዞን ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ነዋሪ ነበር፤ አሁን ጠቅልሎ የከተማ ነዋሪ ሆኗል፣ ባህር ዳር። አሁን ላይ ያስር እኔ ነኝ ያለ የናጠጠ ሃብታም ነጋዴ ነው። ያስር የሚለው ስሙም ተቀይሯል። ለዚህ ጽሑፍ ብቻ የድሮ ስሙን ተጠቅመን እንቀጥላለን።

ያስር የሚለውን ስም ያወጡለት በተወለደባት ትንሽ የገጠር ከተማ ከልጅነት ጊዜው ጀምሮ ይሰራው ከነበረው የንግድ (ችርቻሮ) ስራ ጋር በተያያዘ ነበር፤ አንዱን ጥሎ አንዱን ያነሳበት ከነበረው የችርቻሮ ገበያው። በለጋነቱ፣ ገና የችርቻሮ ንግድን ‹ሀ› ብሎ ሲጀምር ወላጅ እናቱን (አባቱ በህይወት የሉም) የጠየቃት ሀምሳ ሳንቲም ብቻ እንደነበር ያስር ዛሬ ላይ በትውስታ ይናገራል። ብላቴናው ያስር ከዕናቱ ባገኛት ሀምሳ ሳንቲም ትንንሽ የዕለት ከዕለት የህብረተሰቡ መገልገያዎችን እና የህጻናትን ጥያቄዎች ‹ማስቀየሻ› ጣፋጭ ነገሮችን እያዞረ በገበያ ግርግር መሐል ይሸጥ ጀመር፡፡ በተለይም መርፌ፣ ከረሚላ፣ ማስቲካ፣ ምላጭ፣ ክር፣ መርፌቁልፍ፣ አዝራር እና የመሳሰሉትን ሸቀጣ ሸቀጦች ለገበያተኛው እዚያው ባለበት ቦታ ይዞ ከተፍ በማለት ታወቀ። ትንሽ ጊዜ ሲዘዋወር ካልታዩ እንኳ ‹ያስር የት ሄደ› ባዩ ይበረክታል።

ይህ ፈጣንና ፍልቅልቅ ብላቴና ያለችውን ትንሽ ሳንቲም በፍጥነት እየተገለገለ መጠኗ ከዕለት ወደ ዕለት እንድትጨምር አደረጋት። በተለይ ቅዳሜ ዕለት ለያስር የሞት የሽረት ቀኑ ነበረች፤ ሞቅ ባለው ገበያ ውስጥ እየተሹለከለከ ችርቻሮውን የሚያቀላጥፍባት ቀን ቅዳሜ ናት። ወዲያው ከአንድ ደንበኛው ሱቅ ሸቀጦችን ይገዛል፤ ወዲያው በገበያተኛው መሀል እየተሹለከለከ ያጣራል። ማንም ይግዛው ማን፣ ምንም ይሸጥ ምን ያስር ጋር ያለው ዋጋ ያው አስር ሳንቲም ብቻ ነበር፤ መርፌ ባስር ሁለት ገዝቶ ከሆነ ባስር አንድ ይሸጣል። በቃ ይህ የያስር ገበያ ነው። ለያስር ከአስር ሳንቲም በላይ ወጭ አውጥቶ ዕቃ መግዛት ኪሳራ ነው፤ ምክንያቱም ሰዎች ካስር ሳንቲም ውጭ ባለ ዋጋ አይገዙትም ነበር።

እንዲህ እንዲህ እያለ ያስር ከአስር ሳንቲም ጋር ጋብቻ መሰረተ፤ ጋብቻውም ተመቸው፤ ብዙ ትርፍ ይዞለትም መጣ፡፡ የገንዘብ ትርፍ ብቻ ሳይሆን ያላሰበውን ዕውቅናም አተረፈለት፤ ይህም እናቱ ያወጣችለትን ስም እንኳ አስቀየረው፡፡ ሁሉም ሰው ከዕሱ ዕቃ ሲገዛ ባስር ሳንቲም ብቻ በመሆኑ የብላቴናውን ስም ያስር አሉት፣ ገበያተኞቹ። እሱም ስሙ ተመቸው፤ ድንገት ገበያተኛውን ጠጋ እያለ ‹ያስር!…ያስር!…ያስር አለ!› ይል ጀመር። ገበያተኛውም ‹ያስር መርፌ›፣ ‹ያስር ከረሚላ›፣ ‹ያስር አዝራር›፣ ‹ያስር መርፌቁልፍ›…እያለ ይሸምተው ነበር፡፡ ስሙ ያስር፣ የሚሸጣቸው ነገሮች ዋጋቸው አስር ሳንቲም፤ መልካምና ለያስር የተመቼው ስምሙ ጋብቻ ሆነ።

አሁን ያስርን በቀድሞ ስሙ የሚጠራው ሰው ጠፋ፤ ምናልባት እናቱም ብትሆን የምታስታውሰው አትመስልም፤ ‹ያስር› የሉታል ‹አቤት!› ይላል። ያስር ኑሮው፣ ገቢው ተሻሻለ። ከራሱ የትምህርት ቤት ወጭ አልፎ ለእናቱ ደራሽ ሆነ፤ ከነበሩበት የከፋ ድህነት ውስጥ አውጥቶ ማገገሚያ ክፍል ውስጥ ጨመራቸው። ቀስ በቀስ የያስር ግብይት ከአስር ሳንቲም ከፍ እያለ መሄዱ አልቀረም ነበር፤ ቢሆንም ግን ስሙ፣ መጠሪያው አሁንም ያው ያስር ነበር። ያስር በዚህ ስም እየተጠራ፣ ንግዱን ግን እያስፋፋ ለዓመታት ዘለቀ፤ በዓዕምሮም ሆነ በአካል እያደገና እየጎለበተም መጣ፤ ገቢውም ደረጀ።

የያስር ህይወት ከአስር ሳንቲም ጋር የተቆራኘች ሆና የዘለቀችው ለአጭር ጊዜ ብቻ አይደለም፤ ዛሬም ያስር እና አስር ሳንቲም ቁርኝታቸው ጥብቅ ነው፡፡ የዛሬው የናጠጠ ነጋዴነት፣ የዛሬው የተትረፈረፈ ሃብትና ንብረት ባለቤትነት፣ የዛሬው ክብርና ሞገስ፣ የዛሬው በተደላደለ ሁኔታ ህይወትን ቤተሰብን መምራት መሰረታቸው አስር ሳንቲም ናት። በአስር ሳንቲም ነግዶ አትርፏል፤ በአስር ሳንቲም ዕውቅናን አግኝቷል። የሚገርመው ያስር በደንበኞቹ ዘንድ ታማኝና ቅን ነበር፤ ዛሬም ድረስ እንዲያ እንደሆነ ይነገርለታል። በተተመነው ዋጋ ነግዶ ከማትረፍ ውጭ በሌላ ነገር አይታማም ይሉታል ደንበኞች።

አሁን ላይ ያስር ሀብታምና በርካታ ካፒታል የሚያንቀሳቅስ ነጋዴ ነው፤ ከዚህ ያደረሰችውን አስር ሳንቲም ግን አይንቃትም፡፡ አስር ሳንቲም ለማትረፍ ትናንት ብቻ ሳይሆን ዛሬም ከመነገድ ወደ ኋላ አይልም፡፡ አውቆ ካልሆነ በቀር አስር ሳንቲምን ንቆ መልስ ከመቀበል አይመለስም፤ ምክንያቱም ዋጋዋን ያውቃታል። ‹‹አስር ሳንቲም ትንሽ መስላ የምትታዬን ዋጋዋን በሚገባ ካልተረዳንና ህይወትን የመለወጥ አቅሟን ካላወቅን ነው፤ እኔ በአስር ሳንቲም በምሸጠው መርፌ አይደለም እንዴ የተቀደደ ልብስህን ሰፍተህ ገመናህን የምትሸፍነው? ባስር ሳንቲም በገዛኸው መርፌ አይደለም እንዴ ለስቃይ የዳረገህን እሾህ ከእግርህ ነቅሰህ የምታወጣው? ታዲያ አስር ሳንቲም ዋጋዋ ትልቅ አይደለም ወይ?›› በማለት ይጠይቃል ያስር።

ብዙዎቻችን ወደ አዲስ አበባ ታክሲዎች ዘው ብለን ገብተን የአስር ሳንቲምን ዋጋና ከሳንቲሟ ጋራ እያጣን ያለነውን ውድ ጸጋ ካየን ግን ያስር ለአስር ሳንቲም ካለው ግንዛቤ በእጅጉ የተለዬ ሆኖ እናገኘዋልን፡፡ በየጊዜው ዋጋው እየተከለሰ የሚገኘው የታክሲ የአንድ ፌርማታ ጉዞ ክፍያ ወይም ታሪፍ ብዙ ነገሮችን እያሳየን ይገኛል፡፡ ላለፉት ሁለት ወራት ስራ ላይ ባለው ታሪፍ መሰረት የሁለት ፌርማታ ዋጋ 2 ብር ከ90 ሳንቲም ነው። ለሶስት ብር አስር ሳንቲም የጎደለው ማለት ነው። ይህቺ አስር ሳንቲም ናት እንግዲህ መነጋገሪያችን።

ብዙ ተሳፋሪዎች 3 ብር ከፍለው መልስ አይቀበሉም፤ መልሳቸው ደግሞ አስር ሳንቲም ናት። ብዙ የታክሲ ረዳቶች (ወያላዎች) 3 ብር ተቀብለው መልስ አይሰጡም፤ መልሱ ደግሞ አስር ሳንቲም ናት። ግን ለምን? በጥናት ላይ የተመሰረተም ባይሆን ብዙዎቹ ተሳፋሪዎች አስር ሳንቲምን ከመናቅ የመነጨ ሊሆን ይችላል መልሳቸውን የማይጠይቁት። ብዙ የታክሲ ረዳቶች አስር ሳንቲምን ለማስቀረት ካላቸው ፍላጎት (በቀን ምን ያህል ገንዘብ ማስቀረት እንደሚችሉ ያውቃሉና) አሊያም ጠያቂ ከሌለ በማለት ሊሆን ይችላል መልስ የማይሰጡት። ሁለቱም ወገኖች ግን ተገቢ ያልሆነ አረዳድ ውስጥ የገቡ ናቸው። አስር ሳንቲም ዋጋ አላት፤ አስር ሳንቲም ገንዘብ ናት።

ቀደም ብለን ያነሳነው ያስር በአስር ሳንቲም ትልቅ ደቋና ደፍኖባታል፤ ትልቅ ቁምነገር ከውኖባታል። ስለዚህም አስር ሳንቲም ትንሽ አይደለችም። ተሳፋሪዎች ንቀዋትም ሆነ በሌላ ምክንያት ታክሲ ውስጥ ትተዋት የሚወርዱት አስር ሳንቲም ተጠራቅማ የጎጀን ቀዳዳ መድፈን ይቻላታል፤ ቢነግዱባት አትርፋ ቤት ለመስራት ትበቃለች (የያስርን እውነታ ልብ ይሏል)። አንድ ተሳፋሪ በቀን 20 ሳንቲም ታክሲ ውስጥ ትቶ ቢወርድ በወር ውስጥ 6 ብር ያጣል ማለት ነው። ይህ ስድስት ብር ለአንድ የኔ ቢጤ አራት ዳቦ ሊገዛለት የሚችል ገንዘብ ነው። ለተቸገሩት ወገኖች የሚውልን (ከእጅ ላይ ያለችን ሳንቲም መስጠት ታክሲ ላይ ጥሎ እንደመውረድ ባይቀልም) ገንዘብ እንዲሁ መተው አንጉል መቀናጣት ሊሆን ይችላል።

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ያጣነው ትልቅ ጸጋ አለ፤ መብትን አሳልፎ መስጠት፤ (የአስር ሳንቲም ፖለቲካ ልንለው እንችላለን)። ይህ ከገንዘቡም በላይ ነው፡፡ ባለታክሲዎች (ረዳቶች) በራሳቸው ጊዜ የታክሲን ታሪፍ 2 ብር ከ90 የነበረውን ዋጋ 3 ብር አድርገውታል። ከስንት አንድ ሰው መልስ ሲጠይቃቸው እንኳ ይገላምጡታል፤ በተጨማሪም ሳንቲሙን ያለአግባብና ስርዓት በጎደለው መልኩ ሲወረውሩለት ይታያል። ለምን ተጠየኩ እንደማለት! ይህም መጀመሪያ እኛው ራሳችን ያስለመድናቸው ነገር በመሆኑ ነው፤ ‹ቀድሞ ነበር እንጂ…› የሚሉት ብሂል መሆኑ ነው።

በእጃችን ያለን ነገር መልቀቅ በኋላ እንደማስመለስ ቀላል አይደለም። አሁን ላይ ንቀን የምንተዋት እያንዳንዷ ነገር ዘግይታ ብዙ ዋጋ ታስከፍለናለች። ካለመጠየቅ ደጃዝማችነት ይቀራል እንዲሉ አበው ስለመብታችን የመቆርቆር ንቃት፣ መብታችንን ማስከበር ላይ ድክመት ይታይብናል። ከተነጠቅን ወዲያ መጮህ ብቻ ሳይሆን ቀድሞውንም አሳልፎ ላለመስጠት መጣር ተገቢ ነው። ዛሬ አስር ሳንቲም የወሰደብን ሰው ነገ ቤታችንም ለመውሰድ ወደ ኋላ ሊል አይችልም፡፡ ይህ የአስር ሳንቲም ጉዳይ አይደለም፤ ይህ የክብር ጉዳይ ነው። ግለሰቦችም ሆነ መንግስታት በማናለብኝነት የሚነጥቁን የእኛ የሆኑ ነገሮች ሁሉ መነሻቸው የእኛ

ወደ ገፅ 13 ይዞራል